# AMAN FROM PARIS

# ኔ... ዘንደሴ

(ሠሡሚሚቴ)



ለዘርግ ሚያዝያ 2006

ማስታወሻ፡-

ይህ መፅሐፍ 70% ምናባዊ ፈጠራ ሲሆን 30% በ እውነተኛ ታሪክ ላይ የተመሠረተ ነው፡፡

# መ ሙ ሚ ማ ታ

# እ...

# ዘንደኪ

***"A man from Paris"***

አዘርግ

ሚያዚያ 2006

KALEB

ይህን አዝናኝ አስተማሪ መፅሐፍ መልሶ ለማሳተም ሆነ ወደ አስቂኝ አስተማሪ ፊልም ለመለወጥ የደራሲው መብት በህግ የተጠበቀ ነው።

ኮፒራይት © 2006 አዘርግ

## ቀደምት ስራዎች

1. የሆነ የሆነ ነገር ይሠማኛል 2003
2. ኢያሪኮ 777 2004
3. ኢያሪኮ 888 2004
4. ኢያሪኮ 999 2005
5. አዳምና ሄዋን 2005
6. FM66.6 (አቢሲኒያ 24) 2005

## ቀጣይ ስራዎች

... ጣጣቸውን ጨርሰው በወረፋ ላይ የሚገኙ ከአስራ ስምንት በላይ መፅሐፍት አሉ...

## ምዕራፍ ዜሮ

ለውድ ተደራሲያን

ከ አዘርግ

ይቺ አ ዘንደኪ /A man from Paris/ የተሰኘች መፅሐፍ መጀመሪያ የተፃፈችው የሁለተኛ ዓመት የዩኒቨርሲቲ ተማሪ እያለሁ ከረምት ላይ ነበር... በዚያው ከረምት ወደ ፊልም "ስክሪፕት" ተለወጠች::

- የመጀመሪያው ባለሙያ " 5 ሺ ብር" ... ልግዛህ!
- ሁለተኛው " 8 ሺ ብር"... ሸጥልኝ!
- ሶስተኛው "12 ሺ ብር" ... ያዋጣሀል?

የሚል ሀሳብ አቀረቡልኝ፣ በወቅቱ በሥነ ፅሁፍ ዘርፍ የሠራሁት ምንም አይነት ነገር አልነበረም:: በመጋቢት 2005 ዓ.ም እነ የሆነ የሆነ ነገር ይሠማኛል ፣ ኢያሪኮ 777... 888...999 ፣አዳምና ሄዋን ለአንባቢያን ከደረሱ በኋላ ግን ይቺው "ስክሪፕት" 36 ሺ ብር የሚገዛት ተገኘ ፣ ነገር ግን የፈረንሳይ ከተማ ውስጥ ያለው ትዕይንት /ታሪክ/ ብዙ ወጪ ስለሚያስወጣ ይቆረጣል ስባል ' በጭራሽ ገንዘቡ ይቅርብኝ በማለት እነሆ መጠነኛ ማሻሻያ በማድረግ ወደ መፅሐፍነት በመለወጥ ከአንባቢያን ዘንድ ለመድረስ ቻለች ...

" A Man from Paris part one" ውስጥ ሆነ " A Man from Paris part two" ውስጥ ያሉት ታሪኮች ያው ግነት ሲደመር ምናባዊ ፈጠራ ታሪኩን ይበልጥ ለማጣፈጥ እና ለማሳመር ተጠቀምኩበት እንጂ እውነትነቱ ጎልቶ ይወጣል ...

" አስተማሪውም" ... " ሊስትሮውም" " ሴተኛ አዳሪዋም" ... ከውጪ የመጣውም "ወጣትም" ... "ያቺ አስደናቂ ወጣትም" እውነተኛ ናቸው... ለታሪኩ ውበት መፍጠር ሲባል ግነት እና ምናባዊ ፈጠራ የጨመርኩበት ምክኒያት የምከተለው የሥነ ፅሁፍ መንገድ " 70/30 + ግነት" የሚለውን ራሴ የፈጠርኩትን የአፃፃፍ መንገድ ነውና...

ለማንኛውም ውድ ተደራሲያን ይቺን መፅሐፍ ካጣጣማችሁ በኋላ ከጓደኞችሁ ጋር

ይበልጥ ፍቅር የምትጨምሩበት ፣ የተቃረናችሁ ደግሞ ይቅርታ የምትለዋወጡበት፣ ስለ ጓደኞቻችሁ አንዳች ከንፁህ ልብ በመነጨ መልካም የሆነ ነገር የምትሰሩበት ... ከጓደኞቻችሁ ጋር በሀሳብ ያለመጣጣም ያለባችሁ ከፍተቱን የምታጠቡበት... እውነተኛ ጓደኝነት ማለት ከቤተሰብም በላይ ነው የምትባባሉበት ... የጓደኝነት ድንበራችሁ የትድረስ እንደሆነ የምትመዝኑበት ... ባጠቃላይ ከጓደኝነት ጋር በተያያዘ ራሳችሁን ጥያቄ የምትጠይቁበት መፅሐፍ እንድትሆን ከልብ እመኛለሁ!!

አዘርግ ነኝ

መጋቢት 2006

**<u>መታሰቢያነት</u>**

♡ ለመዓዛ ብሩ ... !! (ሸገር 102.1)

እና

♡ ለ ፍቃዱ ተ/ማሪያም ...!!

(አርቲስት)

# የምስጋና ጥግ

ለውድ ተደራሲያን

ከአዘርግ

ስድስቱንም መፅሐፍት በማንበብ ከኔ ጋር ለነበራችሁ እና ይቺን ሰባተኛ መፅሐፌንም ለማንበብ ለተዘጋጃችሁ ውድ ተደራሲያን ከልብ የመነጨ ከፍ ያለ ምስጋና እያቀረብኩ በዚህ መፅሐፍ ውስጥ ያሉት ቀናት ሁሉ በኢትዮጵያዊያን ዘመን አቆጣጠር ሲሆኑ ... ታሪኩን ከወቅቱ ጋር በማጣጣም እንድትዋጁት በማክበር እጠይቃለሁ::

በተረፈ በዚች "አ ዘንደኪ ዙሪያ" ሀሳብ ለመስጠት የምትሹ በ 0911 04 89 65 ላይ SMS ብቻ በመላክ መጠቀም የምትችሉ መሆኑን በአክብሮት እገልፃለሁ::

መጋቢት 2006

አዘርግ ::

## ልዩ ምስጋና

- ለመርዕድ ጥሩነህ ...! (አዲስ አበባ)
- ለ ሠርከዓለም ኃ/ሚካኤል ...!! (አዲስ አበባ)
- ለ ኪሩቤል ጌታቸው...!! (አዲስ አበባ)
- ለቪለኢቫን ኤድዋርድ ...!! (ፓሪስ)

1

# FRANCE

## Paris

## ፈረንሳይ – ፓሪስ

1998

ቦታው:- Paris Le Sheraton Hotel ከጠዋቱ 4:30 ደቂቃ ነው::

500ሚሊየን ዶላር በፈጀው ባለአምስት ኮከብ የአለማችን ምርጥ ሆቴል በሆነው Paris Le Sheraton Hotel እጅግ ዘመናዊ ግዙፍ አዳራሽ ውስጥ የሆቴሉ ሰራተኞች አጠር ላለ ድንገተኛ ስብሰባ ተጠርተው እየገቡ ነው::

ብልጣብልጥ ገፅታ የሚነበብበት የ42 ዓመቱ የሆቴሉ ባለንብረት ሚስተር ኤድዋርድ ወደ ጠራው ድንገተኛ ስብሰባ ሊወጣ ሲል የ17 ዓመቷ ውብ ልጁ ካትሪን እየሣቀች ገባች::

" በጣም እፈልግሀለሁ ኤድ"

(ውቧ ካትሪን አባቷን "ባቢ" አልያም "ኤድዋርድ" ሳይሆን "ኤድ" በማለት ነው የምትጠራው)

" ከይቅርታ ጋር እዚሁ ጠብቂኝ"

ሚስተር ኤድዋርድ ፈጠን ፈጠን እያለ ወደ ዘመናዊው አዳራሽ ገባ:: ከአንድ ሺ ሰስት መቶ በላይ ሰዎችን ያለ ማጨናነቅ ፈታ አድርጎ በሚይዘው እጅግ ዘመናዊው አዳራሽ ውስጥ በአሁኑ ሰዓት ፊት ወንበሮች ላይ ብቻ ጥቁር በጥቁር ሱፍ አልባሳትን የለበሱ ወደ 86 የሚጠጉ የሆቴሉ ዋና ዋና ሥራ አመራሮች በድንገት የተጠሩበትን ጉዳይ ለመስማት ቋምጠው ተቀምጠው ስለ ነበር ልክ ሚስተር ኤድዋርድ ዘው ብሎ ወደ አዳራሹ ሲገባ ከመቀመጫቸው ሁሉም ብድግ ብድግ አሉ::

" አመሠግናለሁ ተቀመጡ"

ሁሉም ተቀመጡ:: ሚስተር ኤድዋርድ በእጁ የያዘውን የታሸገ ኢንቨሎፕ የመነጋገሪያ ጠረጴዛው ላይ አስቀመጠና ሁሉንም ሰራተኞች ቃኘት ቃኘት አደረገ:: ካርቦንዳይ ኦክሳይድ አስወጣና ኦክስጅን አስገባ:: ሰማኒያ ስድስቱንም ወሳኝ ሠራተኞችን በአይኑ አማተራቸው::

"እስቲ አንድ ጥያቄ ልጠይቃችሁ? ሕይወታችሁን በስንት ብር ልትሸጡ ትችላላችሁ? አንድ ጊዜ ከወጣች ተመልሳ ልትገኝ የማትችለውን ብርቅ ሕይወታችሁን በምን ያህል ዋጋ ትሸጡዋታላችሁ? ... እርግጠኛ ነኝ መልስ የላችሁም:: የሌላውን ሕይወት ለማዳን የራሱን ሕይወት መስዋዕት የሚያደርግ ለእኔ ታላቅ ጀግና ሰው ነው:: አንድ ዝነኛ ፀሐፊ `አለም

የተጓዦች ማረፊያ ሆቴል ቤትናት' በማለት ይገልፃታል! በጣም ትልቅ አባባል ነው:: በዚች አለማችን ላይ ምንም እንሁን ምንም ሞት የግዴታ ነው:: ይቺ አለማችን በእርግጥም ጊዜያዊ ቤታችን ናት! ለሁላችንም ትበቃለች! ለህፃናት፣ ለአሮጊት፣ ለወጣት ለሽማግሌው፣ ለሀብታሙ፣ ለደሀው፣ለተማረው፣ ላልተማረው፣ ለጥቁር፣ ለነጩ ብቻ ለሁሉም የሚሆን ሀብት! የተፈጥሮ ፀጋ አላት... በዓለማችን ላይ በአሁኑ ወቅት ከስድስት ነጥብ አምስት ቢሊየን ህዝብ በላይ እንዳለ መረጃዎች ይጠቁማሉ:: አለማችን እስከ ሰባ አምስት ቢሊየን ህዝብ የመያዝ ችሎታ አላት! በሌላ በኩል በሰባቱም ታላላቅ አህጉራት በየቀኑ የሚሰማው ጦርነት ነው! ሽብር ነው! ግርግር ነው... ጥሩ ያልሆኑ አስቀያሚ ዜናዎች ናቸው:: ፀብ ነው! ሁካታ ነው ሀይማኖተኛ የሆናችሁ ሰዎች ይህ ሁሉ የሚሆነው አለም ልትጠፋ ነው የምፅዐት ቀን ደርሶ ነው ካላችሁ ለኔ ገና አልደረሰም!! አለማችን ሰፊ ናት! የሰው ልጅ ሆነ እንስሳት እንዳሻቸው መኖር ይችላሉ... ነገር ግን አለማችን እየደፈረሰች ነው! በየቦታው እየታወከች ነው! ለምን? ለዚህ ሁሉ ምክኒያቱ ምንድ ነው? ራስ ወዳድነት!! በእርግጠኝነት የምነግራችሁ ይቺ ውብ አለማችን ወደፊት በ2929 ዓ.ም የምትጠፋው አልያም ሶስተኛው የዓለም ጦርነት ተነስቶ መላው የዓለም ህዝብ ዶግ አመድ የሚሆነው አርማጌዲዮን የሚመጣው በራስ ወዳድነት ነው! እንግዲህ አለማችን የምትጠፋው በጣም ጥቂት ራስ ወዳዶች በሚያነሱት ሀሳብ ነው:: ራስ ወዳድነት እጅግ በጣም ግዙፍ በሽታ ነው:: ደግሜ የምነግራችሁ በዚች ምድር ላይ ለኔ በጣም አዋቂ! በጣም ትልቅ! በጣም ጠቢብ የምለው የራሱን ሕይወት ያለ አንዳች ራስ ወዳድነት አሳልፎ መስጠት የሚችል ነው! አንድ ታሪክ ልንገራችሁ..."

" 1958 ወርሃ መስከረም ላይ ስልሳ ትላልቅ ምሁራኖችን የጫነች አንዲት መርከብ ከማርሴይ ወደ ታሪካዊት ከተማ ሞናኮ እየተጓዘች ነበር:: በመሀከል እጅግ ከፍተኛ ማዕበል ተነስቶ መርከቢቱን ያናውጣት ገባ:: ይህን ያልታሰበ ድንገተኛ ማዕበል የተመለከተው የመርከቢቱ ካፒቴን በፍጥነት ሀሳብ አቀረበ::

"... 'ውዶች እንደምታዩት ታላቅ ማዕበል ተነስቷል! ስለዚህ ከዚች መርከብ ላይ በፍጥነት ግማሻችን መቀነስ አለብን! በሕይወት ለመትረፍ ያለን ብቸኛ አማራጭ ከዚህ

መርከብ ላይ ግማሽ ሰው መቀነስ ብቻ ነው!... ከብደቱ ሲቀንስላት ጥሩ ይሆናል አለያም ሁላችንም መሞት ነው!!'...በሀሳቡ ታላቅ ንትርክ ተጀመረ፣ ታላቅ ጭቅጭቅ ተፈጠረ... ከስንት ንትርክ በኋላ ሀሳቡ ተቀባይነት አገኘ፡፡ ቀጥሎ ግን ወሳኝ ጥያቄ ተነሳ 'እንዴት ነው ግማሽ ሰው የሚቀነሰው?' መላዎች ቀረቡ! ሽምግል ሽምግል ያሉት ብዙ ዘመናት ስለኖሩ ይውረዱ ተባለ... ስልሳ ነን አንድ አንድ እንያያዝና በትግል የተሸነፈ ወደ ወንዙ ይጣል ተባለ ... ስልሳ ዕጣ ይዘጋጅ ሰላሳው ባዶ ይሁን ከዚያ ባዶ የደረሰው ዘሎ ከባህሩ ይግባ ተባለ...ንትርኩ! ጭቅጭቁ! ቀጠለ! ሁሉም የራሱን ሕይወት አፈቀረ! ሁሉም ራሱን መረጠ! በዚህ ታሪክ ቦታ ሆናችሁ ራሳችሁን አስቀምጡና አስቡት... ምን ልታደርጉ እንደምትችሉ አስቡት.. እነዚያ ስልሳ ታላላቅ ምሁራኖች ሲጨቃጨቁ ... ሲነታረኩ... የማዕበሉ ሀይል ጨምሮ መርከቢቱ ሰጠመች! እነዚያ ታላላቅ ምሁራን እውቀታቸውን ይዘው ለዓለማችን ስንት ነገር መስራት ሲችሉ ሞቱ! ሁሉም ሰጠሙ!! ይህን ታሪክ የነገረኝ የመርከቢቱ ካፒቴን የሆነው አያቴ በተዓምር ተረፈ!! አያቴ ዘመኑን ሁሉ ያስተማረኝ ሁለት ነገሮችን ነው!"

"ልግመኛ ሳልሆን በሕይወት ፈተና! ውጣ ውረድ ተሸንፌ ወደኋላ ሳልል ጠንካራ ሰራተኛ እንድሆን እና በምንም ተዓምር ራስ ወዳድነት እንዳይጠናወተኝ ይነግረኝ ነበር፡፡ ለማንኛውም እንደምታውቁት ከሁለት ቀን በፊት የሩሲያው ባለሀብት ሚስተር ኢ.ዋላስ ብሮዘር ከቤተሰባቸው ጋር በዚህ ሆቴል ለሶስት ቀናት አርፈው ነበር፡፡ በሁለተኛው ቀን የአራት ዓመት ልጃቸው ማንም ሳያያት ከትልቁ ገንዳ ውስጥ ገብታ ሕይወቷ ለማለፍ ስታጣጥር ሚስተር ሚልክያስ የገዛ ሕይወቱን ለከፍተኛ አደጋ አጋልጦ ከ እግዚአብሔር እርዳታ ጋር የልጅቷንም ሆነ የእርሱንም ሕይወት አድኗል! አስቡት ልጅቷን ከሶስተኛ ፎቅ ላይ ድንገት በመስኮት ሲመለከታት ልቡ በሀዘን ተሞላ ... ይቺ ምኑንም የማታውቅ ንፁህ ልብ ያላት ህፃን በነብስ ግቢ በነብስ ውጪ እያጣጣረች ተመለከተ... ከሶስተኛ ፎቅ እስከሚወርድ የዚያች ሚስኪን ህፃን ሕይወት ሊያልፍ እንደሆነ ሲገነዘብ የህፃኑዋን ሕይወት ለማዳን ሲል ከሶስተኛው ፎቅ ላይ በመስኮት በመዝለል የመዋኛ ገንዳው ውስጥ ዘሎ በመግባት እያሰጠማት ከነበረው ውሃ ውስጥ አውጥቶ አዳናት!! በእውነት ይህ ትልቅ ጀግንነት ነው! እውነተኛ

ሰብዓዊነት ነው::"

ሞቅ ያለ ጭብጨባ ንግግሩን አቋረጠው:: "ሚስተር ኢ.ዋላስ ለሚስተር ሚልክያስ ከምስጋና ጋር የ200ሺ ዶላር እና እኔም ሚስተር ሚልክያስ ባለፉት አመታት ይህ ሆቴል ዝናውን ጠብቆ እንዲቆይ ባደረገው ጥረት፣ ባለው ታታሪነት ፣ ባለው ታማኝነት፣ ለሰው ልጆች ባለው ከፍተኛ አክብሮት ባጠቃላይ ባለው ምርጥ ሥነምግባር ለእናንተም አርአያ ስለሚሆን እኔም 100ሺ ዶላር ሽልማት ከምስጋና ጋር ሰጥቸዋለሁ!!"

የበለጠ ሞቅ ያለ ጭብጨባ አሁንም አቋረጠው:: "ነገር ግን አሳዛኝ ዜናው ይህን የድርጅታችንን መከታ የሆነውን እና አለቃችሁን ልናጣው ነው"

አዳራሹ ውስጥ ያሉት ሁሉ ክው ብለው አይናቸውን አንዴ ወደ ሚስተር ኤድዋርድ አንዴ ወደ ሚስተር ሚልክያስ ላኩ:: ተመለከቱ:: በዚህን ሰዓት መልከ መልካሙና ሸንቃጣው ሚስተር ሚልክያስ ከወንበሩ ብድግ አለና ወደ መድረኩ አመራ:: መድረኩ ላይ ወጣ:: በፈገግታ ተሞልቶ ከሚስተር ኤድዋርድ እጅ ላይ መነጋገሪያውን ተቀበለ::

" አመሠግናለሁ! ስለ እውነት ይህ ያላሰብኩት ትልቅ ነገር ነው:: አርአያ መሆን መቻል እጅግ ደስ ይላል! በጣም ነው የማመሠግነው ኤድዋርድ"

በሚስተር ኤድዋርድ እና ሚልክያስ መሀከል የአለቃና ምንዝር የመሰለ ግንኙነት የለም:: በጣም ስለሚቀራረቡ በሙሉ ስማቸው አይጠራሩም:: ከሁለቱም ላይ ፈገግታ እየዘነበ ... ተጨባበጡ.. ተቃቀፉ...

"ኤድዋርድ እንዳለው ለሚቀጥሉት ሰላሳ ስድስት ቀናት ስለማልኖር ማንኛውንም ግንኙነት ከኤድዋርድ ጋር የምታደርጉ ይሆናል:: መልካም የስራ ጊዜ ይሁንላችሁ! በጣም አመሠግናለሁ... በኔ በኩል ጨርሻለሁ ኤድዋርድ የምትጨምረው አለህ?" መነጋገሪያውን ኤድዋርድ በፈገግታ እንደተሞላ ተቀበለ::

"እንዴታ! አለቃችን ሄዷል ብላችሁ ደግሞ የደሞዝ ጭማሪ እንዳትጠይቁ!" አላቸው በፈገግታ ተሞልቶ፤ ሁሉም ከት ብለው ሣቁ::

"አመሠግናለሁ! ወደ ስራችሁ ተመለሱ በቃ!"

ሁሉም ፍጥነት በተሞላበት ሁኔታ ወደየስራ ክፍላቸው አመሩ:: ሚስተር ኤድዋርድ እና ሚልክያስም ወደየቢሮዋቸው አመሩ::

* * *

ውቧ ካትሪን እግሯን ጠረጴዛው ላይ ደራርባ ሰቅላቸው ተቀምጣለች:: ግርግዳው ላይ የተለጠፈውን ቴሌቪዥን ጣቢያውን እየቀያየረች እየተመለከተች ነበር:: ሚስተር ኤድዋርድ በሩን ከፍቶ ገባ::

" ዘገየሁ የኔ ውብ?"

" አንተ እንደ ሚልክያስ ንግግር ማሳጠር መቼ ታውቃለህ? ቢሆንም አልዘገየህም" አባቷን በነገር ጦር ወጋ ካደረገች በኋላ ጠረጴዛው ላይ የነበረውን እግሯን አውርዳ የቴሌቪዥኑን ድምፅ "Mute" አደረገችና ይበልጥ ወደ አባቷ ተጠጋች:: በትኩረት ተመለከተችው::

" እሺ ምን አዲስ ነገር መጣ የኔ ውብ?" አላት በፍቅር ዓይን እየተመለከታት::

" ገንዘብ እፈልጋለሁ"

" ለምን የሚሆን?"

"ትምህርት ሳይጀመር አፍሪካ ሄጄ መዝናናት እፈልጋለሁ"

አካፑልኮ... ሪዮደጀንሪዮ... ስድኒ... ካልካታ... ኒውዮርክ... ቤርሙዳ ...ቤልጂንግ... ስለምን አይስላንድ ... ስንት የዓለማችንን ምርጥ መዝናኛ ቦታዎች አብረው አይተው ይሆን? ... ትዝ አልል አለው:: ብቻ ብዙ ናቸው! ትኩር ብሎ ተመለከታት::

"መቼ?"

" ከሳምንት በኋላ"

"አልችልም"

" ለምን?"

"ሚልክያስ ለአንድ ወር ከሳምንት እንድሸፍንለት ፍቃድ ጠይቆኝ ሰጥቸዋለሁ:: እንደምታውቂው ያጋጣሚ ሆኖ የሚልክያስ ምክትል ቤተሰባዊ ችግር አጋጥሞት እሱም ለወር

ለወር እረፍት ላይ ነው:: ስለዚህ ሚልኪያስ ዛሬን ብቻ ነው የሚሠራው እና እሱ ሲመለስ እንሄዳለን ማለት ነው ካትሪ!"

"እ..." ብላ ሳትጨርስ የሚስተር ኤድዋርድ ሞባይል ድንገት ጮኸች አሰማ:: አባቷ በስልክ የማውራት ሱስ እንዳለበት ፀሐይ የሞቀው ሀቅ ነው:: ስልኩ እስከሚዘጋ ድረስ ከአባቷ በጣም ዘመናዊ ቢሮ አምስት ሜትር ያህል ርቆ ወደተሰራው የሚልኪያስ ዘመናዊ ቢሮ ለመሄድ ወሰነችና ወጣች::

* * *

ሚልኪያስ በጣም አስፈላጊ ፋይሎችን እያስተካከለ ነው:: በሩን ከፍታ ገባችና እንደ ሌላው ጊዜ በደማቅ ፈገግታ ተሞልታ ሳይሆን ኮስተር ብላ ምንም ሳትናገር ወንበሩ ላይ ቀስ ብላ ተቀመጠች:: ትኩር ብሎ አያት::

" ምን ገጠመሽ ካትሪን?"

በሚመረምር አስተያየት አየችው::

" በጣም ነው ያዘንኩብህ!! ያለፉትን አምስት ዓመታት አንዳች የምንደባበቀው ነገር አልነበረም!"

ካትሪን እውነቷን ነበር:: የዛሬ አምስት ዓመት እሷ የ12 ዓመት ልጅ ነበረች:: ለመጀመሪያ ጊዜ ሲተዋወቁ... ከሁሉም ሰራተኞች እሱን ስለምትወደው አብዛኛውን ሰዓቷን ከእርሱ ጋር ነበር የምታሳልፈው:: ኢንግሊዘኛ ቋንቋ ሲያስጠናት ካትሪን ደግሞ የሀገሯን ቋንቋ ፈረንሳይኛን ታስጠናው ነበር:: በልጅነት ፈጣን አዕምሮዋ ተገረመ:: ከሁሉም በጣም ያስደነቀው አንድ እሁድ ያደረገችው ነገር ነው:: እየሣቀች ወደ ቢሮው መጣች::

" ፕሮግራምህን ስመለከተው ዛሬ ከሰዓት ስራ አይበዛብህም?"

" ልክ ነሽ"

"ስለፈረንሳዊያን ብዙ ማወቅ ያለብህ ነገሮች አሉ:: የዚህ ባለአምስት ኮከብ ሆቴል ከፍተኛ አስተዳደር ሆነህ እስከ ዛሬ የፓሪስን ጉራንጉር በሚገባ አለማየትህ በጣም የሚገርም ነው፣ ስለዚህ ዛሬ ከኔ ጋር አብረህ ትዞራለህ እንቢ እንደማትለኝ ተስፋ አለኝ"

"ልታስንበኘን ነው?"

" በሚገባ"

" የፓሪስን ጉራንጉር ታውቂያታለሽ?"

" ምን ነካህ አስረኛ ዓመቴን ሳከብር የፓሪስን መውጫ እና መግቢያ አውቄ ጨርሻለሁ:: በዚያ ላይ ት/ት ቤትም ስለፈረንሳይ ሆነ ስለምንኖርባት ፓሪስ ከተማ እያንዳንዱን ነገር እንማራለን! በፊልም እና በጉዞ የታገዘ ማብራሪያ ይሰጠናል:: ማወቅ ግዴታችን ነበር! የሚገርምህ የታሪክ አስተማሪያችን ሁልጊዜ በእናንተ ይቀልድም ይበሳጭም ነበር"

" በእናንተ ማለት?"

" በአፍሪካዊያን"

" እንዴት?"

" የአፍሪካዊያን ተማሪዎች መጀመሪያ በወጣትነት ዘመናቸው የሚማሩት ስለ አውሮፓዊያን ታሪክ ነው:: በመቀጠል በእርጅና ዘመናቸው የሚማሩት ስለራሳቸው ታሪክ ነው ለዚያውም የተዛፈ ታሪክ ካላቸው! እኛ ፈረንሳዊያን ግን በልጅነት ሆነ በወጣትነት ዘመናችን የምንማረው ስለ ራሳችን ታሪክ ነው! ራሳችንን በሚገባ ማወቅ ነው ቀዳሚው ነገር ምክኒያቱም የትላንቱን መነሻውን ያላወቀ የነገ መድረሻውን አያውቅምና! አፍሪካዊ የሌላውን ታሪክ ያውቃል፤ የራሱን ግን አያውቅም! ልጆች የራስን ታሪክ አለማወቅ ደግሞ ለራስ ያለን ክብር ዝቅተኛ ያደርጋል! የውሸት ማንነት ይፈጥራል!"

" እውነቱን ነው" አላት በልቡ በጣም እያዘነ... 'ኢትዮጵያዊ ተማሪ ስለ አክሱም ስልጣኔ... ስለ ላሊበላ.. ጀጎል... ባሌተራራ ... ራስ ዳሽን... ፋሲል ግንብ ... አሞ ሸለቆ... ስለሚኒልክ... ስለ አፄ ቴዎድሮስ ... ስለማርታ ስለ... ቢጠየቅ አይመልስም ስለ አውሮፓዊያን ታሪክ፣ ሰዎች፣ የተፈጥሮ ሀብት፣ የቱሪስት መዳረሻዎች... ቢጠየቅ ግን በኩራት እየተጀነነ ይመልሳል...' ለራሱ ህሊና ተናገረ::

" ምነው አዘንክ ያልሆነ ርዕስ ነው ያነሳሁት?" አለችው

" አይ ምንም ... ደስተኛ ነኝ አብረን እንሄዳለን" አላት:: ጣጣቸውን ጨርሰው

ወጡ:: የካትሪን የግል ሹፌር የሆነው እና በካራቴ ባለጥቁር ቀበቶው ወጣቱ ማክቬን ሚልኪያስ እና ካትሪንን አሳፍሮ ወጣ::

" ልጀምር?" አለችው ትንሿ የ12 ዓመት ውብ ልጅ ካትሪን

" ጀምሪ" አላት በግርምት እየተመለከታት:: አነጋገሯ... አርጋታዋ... እይታዋ...የ12ዓመት ከምናምን ወራት ልጅ ብቻ ነች ብሎ ለማመን እጅግ በጣም ያስቸግራል::

" እመሠግናለሁ! የፈረንሳይ ዋና ከተማ ወደ ሆነችው ፓሪስ ስትመጣ ቢያንስ የግዴታ አራት ማወቅ ያሉብህ ቃላት አሉ

- Bonjour Madame
- Bonjour Monsieur
- Merci Madame
- Merci Monsieur

እየህ ትልቅ ይሁን ትንሽ ፈረንሳዊያን ሱቅ ገብተህ ውድ ዕቃ ሆነ ተራ ዕቃ ልትገዛቸው ብትፈልግ...ታክሲ ለመያዝ... ብቻ ማንኛውንም ፈረንሲያዊ መንገድ ላይ ስታገኘው ቀድመህ የእግዚአብሔር ሰላምታ ካልሰጠህ ምላሽ አይሰጡህም:: ወርቅ ቤት ገብተህ ለመስተናገድ .. ሆቴል ቤት ገብተህ ለመስተናገድ... ቀድመህ Bonjour Madame አልያም Bonjour Monsieur ማለት ግዴታ ነው ስትጨርስ ደግሞ Merci ... ማለትም ግዴታህ ነው እስተማሪያችን እንደነገረን ይቺን ውብ ከተማ ፓሪስን በየዓመቱ እስከ 30 ሚሊየን ቱሪስቶች ይመለከቱዋታል! በተለይ የነሀሴ ወር የጉብኝት ወር እየተባለ ይጠራል! እጅግ በርካታ ቱሪስቶች በነሀሴ ወር በዚች ከተማ ውስጥ ይርመሰመሳሉ! ፓሪስ ከዓለማችን አስር ምርጥ ከተሞች መሀከል አንደኛዋ ናት ...በዚህች ከተማ ውስጥ የሥነ ውበት የሥነ ጥበብ ሥነ ህንፃ ከፍተኛ ጥበቃ የሚደረግላቸው ሙዚየሞች... ምርጥ ዩኒቨርሲቲዎች ጥንታዊ ቤቶች ጥንታዊ ቤተመቅደሶች... ዘመናዊ አውሮፕላን ማረፊያዎች አስገራሚ ግንባታዎች ...እጅግ ግዙፍ የሆነ የዓለማችን ሆቴሎች ... መዝናኛዎች እጅግ አስገራሚ ጥንታዊ የትያትር ቤቶች ...

የበርካታ ግዙፍ ድርጅቶች መቀመጫ የጥንታዊ የነገስታት ቤተመንግስቶች ... ውብ የመንገድ ግንባታዎች ... ጭፈራ ቤቶች... ዳንስ ቤቶች የጥንቁልና ቤቶች... የማንበቢያ ላይብረሪዎች... ባጠቃላይ የሸርሙጥና ንግድ አገልግሎት መስጫ ቤቶች የሰው ልጅን የትላንት ... ጥንታዊውን መካከለኛውን... የወደፊቱንም ሕይወት ገፅታ ... ስልጣኔ የምታሳይ ውብ ከተማ ናት! አንዳንዶች መንፈስን የምታድስ ናት ይሏታል... ሌሎች ደግሞ የፍቅር ከተማናት ይሏታል... የተቀሩት ደግሞ City of Lights ይሏታል ከአባቴ ጋር ብዙ የዓለማችንን ውብ ከተሞችን አይቻለሁ እንደ ፓሪስ የሚሆን ግን እስካሁን አላጋጠመኝም"

ሚልክያስ በካትሪን ማብራሪያ እየተገረመ ሁለት ሰዓት ከግማሽ የፈጀ ጉዞ አደረጉ:: በፓሪስ ከተማ ውበት ይበልጥ ፈዘዘ ... ካትሪን በብዛት ያሳየቸው ሚልክያስ ከዚህ በፊት በደንብ ያልተመለከታቸውን ሰፍራዎች ነበር ...

በትምህርት ቤቷም በመድረክ ላይ አስገራሚ ንግግር በማድረግ ከአንድም ሁለት ጊዜ የተሸለመችው ትንሿ ካትሪን ማስረዳቷን ቀጠለች "በዚች ከተማችን ውስጥ ብቻ ከ1760 በላይ ሆቴሎች አሉ:: እጅግ ምርጥ ከሆኑት The westin Paris hotel, saint James & Albany Hotel, Le Meridien Etoile, New Hotel, Roblin, Sheraton Paris Airport Hotel ከፍተኛ ደንበኛ አላቸው:: ከምርጦቹ ሳንወጣ Hotel Le Birstoi አንደኛው ነው በዚህ ባለ አምስት ኮከብ ሆቴል አንድ ቀን ለማደር ምግብን ጨምሮ 1720 ዶላር ያስከፍላል Jays Paris ... Hotel Fouquet's Barriear ... Hotel Luxemborg Paris ... Hotel Le Six ... ይጠቀሳሉ ከእነዚህ ቀጥሎ የሚጠቀሰው የኛው Paris Le Sheraton ነው አንድ ቀን ለማደር እንደምታውቀው ምግብን ጨምሮ 645 ዶላር ነው የሚከፈለው ከHotel Le Birstol አንፃር ርካሽ ነው:: በነገራችን ላይ የሆቴላችን የድሮ ስሙ Le citizen Hotel ይባል ነበር..." ሚልክያስን ካትሪን በመጨረሻ ያሳየችው 80,000ሺ ህዝብ አጭቆ የሚይዘውን ከዓለማችን ውብ ስታዲየሞች መሀከል አንደኛው የሆነውን

Stade de France– ስታዲየውም ዲ ፍራንስን ነው “ በዚህ ታሪካዊ ስታዲየውም በዘነዲዚዳን ድንቅ ጎሎች ፈረንሳይ በ1998 የዓለም ዋንጫን አሸንፋ ከብራዚል እጅ ላይ ዋንጫውን ተቀብላለች! ለዛሬ እዚህ ላይ ይብቃን ሌላውን ሌላ ጊዜ አስጎበኝሀለሁ”

“ በጣም ነው የማመሠግነው የዚህን ሁሉ ቦታ እና ታሪክ በዝርዝር ማወቅሽ በጣም ያስደንቃል” አላት ሚልክያስ በግርምት እያጤናት... የ12 ዓመት ልጅ መሆኑዋን እየተጠራጠረ፡፡

“ምንም አይደንቅም! የታሪክ አስተማሪያችን ዳቪንቺ የራስን ማንነት ከማወቅ የበለጠ ታላቅነት የለም ይላል! ታሪክ አስተማሪያችን እያንዳንዱን ነገር ያስተምረናል፣ ካስተማረን በኋላ ደግሞ በህብረት እየወሰደ ያስጎበኝናል! ሲያወራ ደግሞ በጣም ደስ ስለሚል ሁላችንም በፍቅር ነው የምንከታተለው! በዚያ ላይ ደግሞ መፅሐፍትን በጥንቃቄ አነባለሁ፡፡ ውይ እንደማንበብ ምን ደስ የሚል ነገር አለ? አንተ ስለ አገርህ ብጠይቅህ እያንዳንዱን ነገር አትነግረኝም እንዴ ሚኪ?”

ፈገግ አለና ዝም አላት፡፡

* * *

ካትሪን ት/ቤት የገጠማትን ሁሉ ለሚልክያስ ነበር የምታጫውተው፡፡ እንደውም የ13ተኛ ዓመቷ ላይ ለእናቷም ሆነ ለአባቷም ሳትናገር እየሳቀች ሚልክያስ ቢሮ መጣች፡፡ “ምን ገጠመሽ ካትሪን ... በጣም ደስተኛ ነሽ ዛሬ”

“ የወር አበባዬ መጣ! አሁን የራሴን ልጅ ለመውለድ ዝግጁ ነኝ ማለት ነው” በጣም ነበር ሚልክያስ በወቅቱ ከልቡ የሳቀው፡፡

“ ያስቃል ሚኪ?”

“ በጣም እንጂ ካትሪን ! አንቺ ራስሽ እንክብካቤ የምትፈልጊ ልጅ ነሽ እና ... አባባልሽ አስቆኝ ነው፡፡ ይህን አሳብ ከአዕምሮሽ ማውጣት አለብሽ”

“ጓደኛዬ ሱዛን እኮ ልጅ አላት... ወልደሽ ስታይው ነው የእናትን ፍቅር የምታውቂው ብላኛለች”

ሚልክያስ እየተገረመ በትኩረት ተመለከታት፡፡ ፈጣን ጭንቅላት አላት፡፡ ፈገግታዋ የልብ ምትን ያዘበራርቃል... ከወንበሩ ተነስቶ እጅግ ለስላሳ የሆነውን እና የሚያምረውን እጇን ያዘው፡፡

" የኔ ውብ ካትሪን" አላት በእርጋታ፡፡ ' የኔ ውብ ' ስላላት በጣም ተደስታ በትኩረት እያጤነችው

" አቤት" አለችው

" ወደ ፊት ምን መሆን ትፈልጊያለሽ?"

" የመጀመሪያ ዲግሪዬን በስነሰብ መመረቅ ሲሆን ሁለተኛ ዲግሪዬን በአስተዳደር መመረቅ እፈልጋለሁ"

" አ! በጣም ምርጥ ነው! አየሽ ነገ ትልቅ ደረጃ ለመድረስ ሆነ አላማሽን ለማሳካት ዛሬ ላይ የምታደርጊው እያንዳንዱ ውሳኔ በጣም ወሳኝ ነው! ጓደኛሽ ወሲብ ስላደረገች አንቺም ወሲብ ማድረግ አለብሽ ማለት አይደለም! ጓደኛሽ በዚህ በልጅነት እድሜዋ ልጅ ወለደች ማለት አንቺም ልጅ መውለድ አለብሽ ማለት አይደለም! ጓደኛሽ ሙሉ ለሙሉ ተሳስታለች አንቺ ከሷ ስህተት መማር እንጂ ያን መድገም የለብሽም! በዓለም ላይ ትልቁ ብልህ የሚባለው ግለሰብ ከሰው ስህተት የሚማር ነው፡፡ በጣም የምወደውን አንድ ግዙፍ አባባል ልንገርሽ? ለሁሉም ነገር ጊዜ አለው የሚለውን ነው በዚያ ላይ ወደ ፊት የቢሊየነር አባትሽን ንብረቶች የምታንቀሳቅሺው አንቺ መሆንሽን እንዳትረሺው! ስኬታማ ለመሆን ስሜታዊነት ሳይሆን ምክኒያታዊ መሆን አለብሽ! አንቺ የአንዲት ተራ ሴት ሕይወት አኗኗርን ሳይሆን አንዲት ትልቅ ሀላፊነት የተሸከመች ሴትን ሕይወት ነው የምትኖሪው..."

መከራት ፡፡ ሀሳቧን አስቀየራት፡፡

* * *

አስራ አራት ዓመት ሲሆናት ደግሞ ትክዝ ብላ ቢሮው ገባች፡፡

" ምን ገጠመሽ ካትሪን"

" እናቴ ግን ጥሩ ሴት አይደለችም"

"ለምን... አስቀየመችሽ እንዴ?"

" በጣም! በጣም ደደብ ናት!"

" ካትሪን እናት ደደብ ተብሎ በፍፁም አይሰደብም እሺ! እናትን አለማክበር ራሱን የቻለ ግዙፍ ሀጢያት ነው:: እናት ማለት ግማሽ እግዚአብሔር ማለት ናት! የወለደችሽን እናትሽን ካላከበርሽ እንዴት በአይንሽ ያላየሽውን ፈጣሪ አከብረዋለሁ ብትይ ማመን ይቻላል?"

" ምን ላድርግ ታዲያ ሚኪ የሰራችው ስራ እኮ አናዶኝ ነው"

"ምን አጠፋች?"

" የሳውዳረቢያውን ባለሀብት ስትበዳው አየው! ከላይ ሆና እየጮኸች ነበር" አስራ አምስት ዓመት ሲሆናት እንዲሁ በቅድሚያ ሚልከያስ ጋር መጣች::

" እባክህ ዳርዊን ትምህርት ቤት ሽጉጥ ይዞ ገብቶ ታስሯል... አባቴ ሳይሰማ መላ አምጣ..."

ብቻ ካትሪን ለደስታዋም ሆነ ለሀዘኑዋም ጊዜ በፍጥነት የምትመጣው ሚልከያስ ጋር ነው:: እሱም ከካትሪን ግልፅነት የተነሳ የሚደብቃት ነገር አልነበረም:: ሳያስበው የእርሱን አመለካከት ፣ የሕይወት ልምድ ሆነ የሕይወት ፍልስፍና እየመገባት ቀረፃት:: አስራ ስድስተኛ የልደት ቀኑዋን ስታከብር ያለችውን ግን መቼም አይረሳውም::

" ሚኪ አንድ ጥያቄ ልጠይቅህ?"

" ደስ ይለኛል"

" ደስተኛ ነህ?"

" እጅግ በጣም"

" ከጠዋት እስከ ማታ በሩጫ ነው የምታሳልፈው ቀን ቀን ሥራ፣ ምሽት ት/ት፣ ከዚያ ንባብ ... የራስህ ጊዜ የለህም ፍቅረኛ የለችህም ወሲብ አታደርግም... እንዴት ደስተኛ ሆንክ ከዚህ ሁሉ ነገር ራስህን አግልለህ?"

" ካትሪን እኔን የሚያስደስተኝ ሰዎች ሲደሰቱ ማየት ነው:: በእነሱ ደስታ እኔ እጥፍ አደሰታለሁ!! በስራዬ እጅግ በጣም እደሰታለሁ:: በዚያ ላይ ለሁሉም ጊዜ አለው የሚለውን

አባባል አምንበታለሁ"

" እ... ግብረሰዶም ነህ እንዴ?"

" ምን ካትሪን?... ይህን አስቀያሚ ነገር ለኔ ትመኛለሽ? በጣም አዝናለሁ ካትሪን!!"

" Pardon! ስላበሳጩሁ በጣም ይቅርታ! ምን ላድርግ ከምንም አይነት ሴት ጋር አላየሁህም ... ስለ ሴቶች ጥሩ ነገር ሆነ አጉል ነገር ስታወራም ሰምቼም አላውቅም:: ወይስ ኢየሱስን መሆን ፈልገህ ነው? ኢየሱስ ብቻ ነው ፍቅረኛ ያልነበረው:: የሚገርምህ ግን ዳቪንቼ የሚባለው የታሪክ አስተማሪያችን ኢየሱስ በምድር ላይ 33 ዓመታት እንደሰው ሲኖር እንደማንኛውም ወጣት ፍቅረኛ ነበረው... ወሲብም አድርጓል... ከመግደላዊት ማርያም ጋር ብሎናል! በዚያ ላይ ደግሞ በአፍሪካዊያን ላይ እየሳቀ እንዲህ አለን "ልጆች ምን እንደሚገርመኝ ታውቃላችሁ አፍሪካዊያን የቆዳ ቀለማቸው ጥላሸት የመሰለ ጥቁር ነው:: ልክ እንደ ፈረንሳዊያን በኢየሱስ ያምናሉ! ኢየሱሳቸው ግን መልኩ ልክ እንደኛ ፈረንጆች ነጭ ነው አስቡት እኔ አፍሪካዊ ብሆን እኔ ጥላሸት መልክ ካለኝ የኔም ኢየሱስ ነጭ ሳይሆን እኔን የመሰለ ጥላሸት የመሰለ መልክ አለው እል ነበር:: አፍሪካዊያን ኢየሱስ ጥቁር መልክ ፣ ትላልቅ ደፍጣጣ አፍንጫ፣ ፈርጣማ ጡንቻ... ኪንኪ ፀጉር አለው ብለው ለማሰብ አይፈልጉም! የነጭ የፊልም አክተር ፎቶ ቤታቸው ግርግዳዎች ላይ ሰቅለው ጠዋት እና ማታ ይሰግዱለታል አያስቁም ታዲያ? አንድ ጊዜ ምን ሆነ መሰላችሁ ከአንድ አዋቂ የሚባል የአፍሪካዊ የሀይማኖት አስተማሪ ጋር ወሬ ተጀመረ

' አንተ ቆዳህ ጥቁር ነው ስለዚህ ኢየሱስ እንዳንተ ሻንቅላ መልክ ሊኖረው አይችልም? በዚያ ላይ እግዜር ሰውን በመልካችን እንደምሳሌያችን እንፍጠር ነው ያለው' አልኩት አፍሪካዊው ግን የኢየሱስ መልክ ቀይ ነው ሲል ራሱን አሳንሶ ተከራከረ ... እኔ ሌላ ጥያቄ ወዲያው አነሳሁለት ::

' እሺ ኢየሱስ በምድር ላይ ሰላሳ ምናምን ዓመት ሲኖር እንደ ሰው ልጅ ነበር አይደለም'

'ልክ ነህ እንደሰውም እንደ መላዕክም ኖሯል ምነው?'

'እንደ ሰው ልጅ ከኖረ እንደማንኛውም ሰው ይበላ... ይጠጣ... ይሸና ... ያራም ነበር ?' እያልኩ ተናግሬ ሳልጨርስ ጥሎኝ ጠፋ! አስቡት እንግዲህ ልጆች እርሱ ራሱ በደንብ ስለማያውቀው ኢየሱስ ነው የሀይማኖት አስተማሪ ተብሎ የሚያስተምረው... ብቻ ልጆች አፍሪካዊያን ከፍተኛ የአስተሳሰብ ችግር ሰለባዎች ናቸው:: በጣም ሲበዛ ደደብ ህዝቦች ናቸው:: በዚህ አጋጣሚ ልጆች ስለ ኢየሱስ ከተነሳ ስለ ኢየሱስ ወንበር ልንገራችሁ:: ይቺ የኢየሱስ ወንበር የምትባለው በከፍተኛ ጥንቃቄ እና ጥበቃ በአሁኑ ወቅት ኢትዮጵያ ውስጥ ትገኛለች:: በተለምዶ የኢየሱስ አባት ነው እየተባለ የሚጠራው የማርያም ፍቅረኛ ዮሴፍ በጣም የታወቀ አናጢ ነበር:: በወቅቱ የተጨበጨበለት የወንበር፣ የአልጋ፣ ሆነ የቤት ቁሳቁስ በመስራት የሚያክለው አልነበረም:: ታዲያ የአባቱን የአናጢነት ጥበብ እየቀሰመ ያደገው ኢየሱስም የ14 ዓመት ልጅ እያለ አንዲት ረዘም ያለች ወንበር ሰራ:: ያቺ ወንበር ተዓምራትን መስራት ጀመረች:: ወንበሯ ላይ የተቀመጡ ሽባዎች ዳኑ... አይናቸው የማያይ ተመለከቱ... በከባድ ህመም የታመሙ ተፈወሱ ... ልባቸው በሀዘን የተሰበረ ልባቸው በሀሴት ተሞላች ... ወንበሯ ብዙ ተዓምራትን መስራት ጀመረች:: ወንበሯ ላይ የተቀመጠ ሰው ሁሉ የሚመኘው ነገር በፍጥነት ይከናወንለት ጀመር... አባቱ ዮሴፍ በሁኔታው ተደነቀ... በመሀከል የዚያችን ወንበር ተዓምር መስራት የተመለከቱ በወቅቱ የነበሩ ነዥዎች በሚስጢር ያቺን ወንበር በድብቅ አስቀመጧት... ያቺ ወንበር በምን ተዓምር ወደ ኢትዮጵያ እንደደረሰች ባይታወቅም በአሁኑ ወቅት በከፍተኛ ጥንቃቄ ኢትዮጵያ ውስጥ ትገኛለች ... ያቺን ድንቅ ወንበር ከኢትዮጵያ ውስጥ ለመዝረፍ ኢንግሊዞች ፈረንሳይ ... ጣሊያን ... ከፍተኛ ጥረት ቢያደርጉም ለማግኘት አልቻሉም:: "ሲል ነገረን "

በግርምት ተመለከታት:: ውበቷ ያስደንቃል! አወራሯ ያስደንቃል! እርጋታዋ ያስደንቃል! የማስታወስ ችሎታዋ ያስደንቃል...

" ማፍቀር የጤንነት ምልክት ነው:: አንድ ቀን አፈቅራለሁ:: Love and death comes uninvited የሚል አነጋገር አለ ካትሪን በዚያ አምናለሁ"

" እሺ የምትመኛት ሴት ምን አይነት ነች?"

" ካትሪ ይህ ጥያቄ ለኔ በጣም ከባድ ነው:: እርግጠኛ አይደለሁም ቢሆንም በሀሳቤ የሳልኳት ሴት አለች:: ስለመልኳ ብዙም ግድ የለኝም እውነቱን ለመናገር ግን ውብ ብትሆን አልጠላም! እንደራሷ ሰዎችን የምትወድ፣ ተግባቢ የሆነች፣ ትልቅ ተስፋ ያላት፣ በስራ የምታምን፣ የዊግ ፀጉር ለሴቶች ብዙ ጥቅም እንዳለው ብገነዘብም የኔ ሚስት የምትሆነው ግን ከምንም በላይ ዊግ ፀጉር የማትጠቀም! በራሷ ኪንኪ ፀጉር እንኳ የምትኮራ! ከሁሉም በላይ እግዚአብሔርን ከልብ የምታምን እና በገንዘብ ሆነ በማንኛውም ነገር ላይ ቆንቋና ያልሆነች ለራሷ ክብር ያላት ሴት የማገባ ይመስለኛል ይህ እንዳለ ሆኖ የማግባት ፍላጎቴ ግን 45% ብቻ ነው :: በዚያ ላይ ማግባት ግዴታ አይደለም ምርጫ ነው:: ዘር መተካት ምናምን የሚባለውን ፈሊጥ አላምንበትም ወደፊት የልጅ ፍቅር ካለኝ ያለፍላጎት ሆነ በፍላጎት ተወልደው በስቃይ የሚኖሩ ብዙ ህፃናት አሉ እነሱን መርዳቱ ይቀላል:: ካትሪ የኛ አገር ትልቁ ችግር ምን እንደሆነ ታውቂያለሽ አንድ ልጅ ማሳደግ ያቃታቸው ባለትዳሮች እግዜር የከፈተውን ጉሮሮ እግዜር ይዘጋዋል እያሉ በአጉል ተራ እምነት ደርዘን ልጅ ይፈለፍላሉ... ትልቅ የአመለካከት ችግር አለ!"

" እህ ... ሀሳብህን እደግፈዋለሁ ግን አንተ የምትወልደው ልጅ ቢሆንስ ለአገርህ ትልቅ ነገር የሚሠራው? 55% እኮ በብቸኝነት መኖርን ነው የመረጥከው?"

" ይህን አስተሳሰቤን የምታስቀይረኝ ሴት ትመጣ ይሆናል..."

" ታዲያ እኔን ለምን አታገባኝም!"

በጣም አሳቀችው:: ጥያቄው ቀልድ ስለመሰለው በሳቅ ብቻ አሳለፈው:: በጣም ከመላመዳቸው የተነሳ ከአባቷ ጋር ታላላቅ መዝናኛ ቦታዎች እና ከተማ ስትሄድ ቢያንስ በቀን 4 ጊዜ ትደውልለታለች:: ከሚልክያስ ጋር ማውራት ሀሴቷ ነው:: ተበሳጭታ እንኳ ከሚልክስ ጋር ስታወራ ሁሉ ነገርን ትረሳለች:: ከእርሱ ጋር ስትሆን የመኖር ጉጉቷ ይበልጥ ይንራል ... ሕይወት ደስ ይላታል... ልቧ በቃላት ለመግለፅ በሚያስቸግር ሁኔታ በታላቅ ሀሴት ትወጠራለች...

* * *

እዚሁ ቢሮ ውስጥ ከሁለት ቀናት በፊት አብረው ነበሩ::

" እስቸኳይ ፍቃድ ሳልጠይቅ አልቀርም ካትሪ" አላት:: ለስለስ ባለ አነጋገር የሚያስደንቀውን ዓይኑዋን እየቃኘ...

" ለምን ሚኪ" አለችው በመደንገጥ:: አይ ጊዜ ከንቱ!... ግርግዳው ላይ ከዛሬ አስራ ስድስት ዓመት በፊት 1982 ዓ.ም ላይ የስድስተኛ ክፍል ተማሪ ሳለ ከሶስት ጓደኞቹ ጋር የተነሱት ታሪካዊ ፎቶ ግራፍ ተሰቅሏል:: ትኩር ብሎ ተመለከተው::

" ምን መሰለሽ ካትሪ... ስለ ጓደኞቼ እንደነገርኩሽ" ተናግሮ ሳይጨርስ የሩሲያ ዝርያ ያለው ሳይስቅ የሣቀ የሚመስለው የደህንነት አላፊው ፈጠን ፈጠን እያለ ገባ::

"ይቅርታ ጌታዬ አንድ ችግር ገጥሞኛል"

" ይቅርታ ካትሪን በኋላ እንጫወታለን" ሁለቱም ተከታትለው ወጡ:: ካትሪን ከሚልክያስ ጋር የነበረው ወሬያቸው ስለተቋረጠ በመጠኑም ብስጭት ብላ ወደ አባቷ ቢሮ አመራች:: ከላይ ታች ሲሯሯጥ እስከ አሁኑዋ ደቂቃ ድረስ ግዜ አግኝተው ለማውራት ስላልቻሉ እንጂ ሊነግራት አስቦ ነበር::

" ምን ደበኩሽ ካትሪ" አላት በመጠኑ ግርብሎት

" ፍቃድ መቀበልህን"

" አ! ከትላንት ወዲያ ጀምሬልሽ እኮ ነበር ካትሪ..."

በማስታወስ ራሷን ነቀነቀች::

" እሺ ለምንድ ነው ፍቃድ የፈለከው?"

" ወደ ትውልድ አገሬ ኢትዮጵያ መጓዝ አስቤያለሁ"

" አፍሪካ" አለች በጣም ተደስታ::

" ትክክል! ምነው ተደሰትሽ?"

" አፍሪካ እኔም መሄድ እፈልጋለሁ! በተለይ የአንተን አገር ለማየት በጣም እፈልጋለሁ! ከቤተሰቦችህ ጋር ነው የምትሄደው ወይስ ብቻህን?"

" ብቻዬን ነው"

"ዋው እንግዳውስ አብረን ነው የምንሄደው"

ያላሰበው ነገር ስለ ነበር ሲያስተካክል የነበረውን ወረቀት አስቀመጠና ቀና ብሎ ተመለከታት:: ለመጀመሪያ ጊዜ ፈራ:: ይቺን ውብ ወጣት በጣም ከሚወዳት አባቷ አደራ ተቀብሎ ለአንድ ወር ከስድስት ቀናት በጥንቃቄ ሊይዛት ይችላል? ... ምን አስፈራው ግን በቢሊየን ዶላሮች የሚገመተውን የአባቷን ምርጥ ሆቴል Paris Le Sheraton ንን እንኳ የበላይ ሆኖ እያስተዳደረ አይደለም እንዴ?

" ለኤድዋርድ ንገሪው እሺ" አላት ቀዝቀዝ ባለ አነጋገር:: ሳያስበው ተቀምጣበት ከነበረችበት ወንበር ላይ ብድግ አለችና እቅፍ አደረገችው::

" አባቴ ከማንም በላይ በአንተ እንደሚተማመን ታውቃለህ? ይልቅ መቼ ነው የምንጓዘው?"

" እሁድ ጥሩ ቀን ይመስለኛል!"

" በቃ ለኤድዋርድ ልንገረው በእርግጠኝነት እሺ እንደሚለኝ ግን አትጠራጠር!" አለችውና በደማቅ ፈገግታ እንደ ተሞላች ወጣች:: ከሚልክያስ ቢሮ ትንሽ ራቅ እንዳለች ሞባይሏን አውጥታ ደወለች:: ሱዛን በመጀመሪያው ጥሪ አነሳችው::

" እንዳሰብኩት እየሆነ ነው"

" ዋው ... ቀናሁብሽ"

" እሁድ እንጓዛለን! የሚገርምሽ ለወር ከስድስት ቀናት ነው የምንቆየው"

" ድንግልናሽን አጥተሽ እንደምትመጪ ተስፋ አለኝ"

" ወስኛለሁ!"

# 2

# ሊሊያና ሳንቶስ

ሚስተር ኤድዋርድ ኢጋጣሚው ከብራዚላዊቷ ቅምጡ ጋር ለመዝናናት አሪፍ ስለሚሆንለት ጉዞውን በደስታ ተቀበለ:: አርብ አዲስ አበባ ለሚገኘው ሸራተን ሆቴል መኝታ " አንደኛ ማዕረግ" እንዲያዝላቸው... አየር መንገድ እንደ ደረሱ እንዲቀበሏቸው እና መኪና እንዲዘጋጅላቸው ፋክስ አደረጉ:: የመልዕክቱም ምላሽ በፍጥነት መጣ::

* * *

የሶፍትዌር ጠቢቡ አሜሪካዊው ቢሊጌት የአለምን ሁሉ ሀብት በ 55 ቢሊየን ዶላር በግንባር ቀደም ሲመራ ሚስተር ኤድዋርድ በፈረንሳይ ባለው ዝነኛ ሆቴልን ጨምሮ በዴንማርክ ፣በቱርክ ፣ በአውስትራሊያ ባለው የግል ድርጅቶች በሳውዲረቢያ ባለው የጨርቃጨርቅ ፋብሪካ እና የነዳጅ ማውጫ ፋብሪካዎች ከዓለም ሀብታሞች ተርታ በ45ተኛነት ተቀምጧል:: ከአምስት ሺ ሰራተኞች በላይ የሚያስተዳድረው ወጣቱ ባለሀብት ኤድዋርድ በብዙ ነገሮች ይታወቃል:: ሚስተር ኤድዋርድ ለታዳጊ ሀገራት ለልብ ህሙማን ፣ ለት/ቤቶች፣ ለውሃ ቁፋሮ፣ ለምግብ ፣ ቤትግንባታ... ረጠብ ያለ ዶላር ይሰጣል:: በዓለም ላይ እንደ ኤድዋርድ ድርጅት ያለ ለሠራተኞች ከፍተኛ ደሞዝ የሚከፍል የለም! በራሱ ፍቃድ እንጂ በኤድዋርድ ትዕዛዝ አንድም ሠራተኛ እስካሁን ተባሮ አያውቅም...እንደ ጠቢቡ ሰለሞን 700 ሚስቶች እና 300 ዕቁባቶች ባይኖረውም...የሴት ነገር አይሆንለትም... አንድ

ሚስት እና ብዛት ያላቸው ዕቁባቶች ግን አለው...

የመጀመሪያ ንብረቱ የሆነውን Paris Le Sheraton ፣ የመጀመሪያ ልጁ የሆነችውን ካትሪንን፣ የመጀመሪያ ሚስቱን ... የመጀመሪያ መኪናውን የመጀመሪያ የግል አውሮፕላኑን ... ብቻ የመጀመሪያ የሆኑ ነገሮቹን በጣም ይወዳል ... ከሁሉም በላይ ግን ኤድዋርድ ካትሪንን ያስቀድማል:: ሁሉን ነገር ቢያጣ ምንም አይመስለውም! ካትሪንን ማጣት ግን ለኤድዋርድ የማይታሰብ ነው::

*　　*　　*

ውቧ! ፈጣኑዋ! ሳቂታዋ! ተግባቢዋ! የፈጣን አዕምሮ ባለቤት የሆነችው ካትሪን ከአባቷ የግል አውሮፕላን ውጪ ለመጀመሪያ ጊዜ በዝነኛው AIR-FRANCE 404 ለመጓዝ ሰዓታት ብቻ ቀራት:: መኝታ ቤቷ ውስጥ እየተራወጠች ነው:: ' ማንበብ የጥበብ ሁሉ ሁለተኛ ነው' የሚል መርህ አላት ካትሪን:: የማንበብ ልምድን ያዳበረችው ከዝነኛ ደራሲ እናቷ ነው:: አሁንም የምታነባቸውን መፅሐፍቶች ቦርሳዋ ውስጥ እያስገባች ሳለ ሚልከያስ መጣ::

" አልጨረሽም ካትሪ?"

"ጨረስኩ! መሄድ እንችላለን ለሹፌሩ ደውል"

ሻንጣዋን ይዛ ወጣች:: ሚስተር ኤድዋርድ በር ላይ ዘና ብሎ ቆሟል :: ለዘመናት እንደ ሚለያዩ ልባቸው ፍርሀት ፍርሀት አለው:: ካትሪን በፍፁም ፈገግታ ተሞልታ ቀረበችው:: እቅፍ አደረጋትና ግንባሯ ላይ ሳማት::

" በዓለም ላይ ካንቺ በላይ የምወደው እንደሌለ ታውቂያለሽ አይደለም? ተጠንቀቂ እሺ የኔ ውብ!!"

" አንተም ተጠንቀቅ!!"

ተለያዩ:: መኪናዋ በፍጥነት መብረር ጀመረች

*　　*　　*

"why not to day" በሚል ድንቅ መፅሐፍ በመላው ዓለም ለመታወቅ በቻለችው ዝነኛ

ደራሲ ከሆነችው ከካትሪን እናት ቀጥሎ የኤድዋርድን ልብ ያሸፈተች ቆንጆ ብትኖር ብራዚላዊቷ ሞዴሊስት ሊሊያና ሳንቶስ ብቻ ናት:: ከካትሪን ጋር ሳዎፖሎ እየተዝናኑ ሳለ ነበር ጓደኛው በጠራው ግብዣ ላይ የተዋወቁት:: እድሜ ለዝናው እና ለገንዘቡ ምንም ሳይቸገር ከተዋወቁ ካንድ ሰዓት በኋላ አንሶላ ለመጋፈፍ ችሎ ነበር... ሊሊያና የአልጋ ላይ ንግስት ስለሆነችበት ከዚያ ወዲያ ሹልክ እያለ ... ብራዚል እየሄደ ... ወይም ሊሊያና እየመጣች... ድብቅ ወሲባቸውን ይፈፅማሉ:: ሞባይሉን አነሳና ደወለ::

* * *

"ኤድዋርድ! እንዴት ናፍቀኸኛል መሰለህ የኔ ጌታ?"

" ዛሬ ለምን አትመጪም ጣፋጯ?"

"ካትሪንስ?"

"ኢትዮጵያ ሄዳለች"

" የት ነው ደግሞ ኢትዮጵያ?"

" አፍሪካ ውስጥ ነው ለአንድ ወር ከስድስት ቀናት አትመለስም"

" እንዴ ፍቅሬ ! ያቺን ውብ ልጅህን እነዚያ ያልሰለጠኑ አውሬ! አስተሳሰባቸው የዘቀጠ! እርስ በርሳቸው ከሚገዳደሉት ኋላቀር ህዝቦች ጋር አምነህ ያለምንም ጠባቂ ትልካታለህ? ቢበሏትስ? ቢደፍሯትስ? አፍሪካ የሚለው ቃል ራሱ እንዴት ይቀፈኛል መሰለህ??"

"አትጨነቂ ! አፍሪካ አሁን የከፍታ ዘመን ላይ ነች! በዚያ ላይ የሄደችው ደግሞ አንቺ እንደምታስቢው ሳይሆን ጣሊያንን አርበድብደው ካሸነፉ ህዝቦች ኢትዮጵያ ምድር ነው! የኢትዮጵያ ህዝቦች ደግሞ ለገዛ ወገናቸው ክብር ባይኖራቸውም ለኛ ለነጮች ያላቸውን ከበሬታ ተይው! ለካትሪን ስለተጨነቅሽ ግን በጣም አመሠግናለሁ:: ይልቅ መቼ ነው የምትመጪው የኔ ማር?"

" ከነገ ወዲያ ጠዋት አንተ ጋር ነኝ ፍቅሬ"

" በጉጉት እጠብቅሻለሁ"

# 3

# 1979

# ኢትዮጵያ

መ...

...ሙ

ሚ...

...ማ

ታ...

# 3

መሀከል አራት ኪሎ በሚገኘው በኢትዮጵያ የት/ቤት ታሪኮች ምስረታ የመጀመሪያ ከሆነው ዳግማዊ ሚኒሊክ ትምህርት ቤት ውስጥ ነው:: የFREE TALK መምህር ገብቶ ለተማሪዎች ሁሉ ሠላምታ ሰጣቸው::

" ይህ ክፍለ ጊዜ እየተዝናናን የምንማርበት በተለይ የመናገር ችሎታችንን የምናዳብርበት ግልፅነትን የምንማርበት፣ የምንረዳዳበት... ባጠቃላይ ስለራሳችን ማንነት የምናውቅበት ይሆናል:: ትምህርታችንን ዛሬ እንጀምራለን ከዚያ በፊት ግን ስሜ መምህር ካሱ ይማም ይባላል:: እናተም ተራ በተራ ስማችሁን ታስተዋውቁኛላችሁ::"

ሁሉም እየተነሳ ስሙን ከነአባቱ አስተዋወቀ::

" ጥሩ! አብዛኛውን ስራ በህብረት ነው የምንሠራው ስለዚህ እስቲ አራት አራት እየሆናችሁ ቡድን መስርቱና ለቡድናችሁ ስያሜ ስጡት ከዚያ ትዕዛዝ ሁለት ይቀጥላል"

ተማሪዎቹ የታዘዙትን በቡድን በመሆን በፍጥነት ፈፀሙ:: ዘጠኝ ወረቀቶች ደረሰው::ሁሉንም ቃኘት ቃኘት አደረጋቸው:: አቢሲኒያ፣ ነፃነት ፣ ፍቅር፣ ሰላም... መሙሚማታ ... ይላሉ አንብቦ ጨረሰና ቀና አለ::

" የማን ቡድን ነው መሙሚማታ?" ከኋላ መቀመጫ አራት በጣም የሚያምሩ ልጆች ተቀምጠዋል:: አራቱም ተያዩና ክፍሉ ውስጥ ካሉት በቁንጅና ሁሉንም የምትበልጣቸው ውቧ ተማሪ ብድግ አለች::

" የኛ ነው መምህር"

" ምን ማለት ነው?"

" ያጋጣሚ ሆኖ ሁላችንም የተወለድነው በአንድ ቀን ፣ በአንድ ዓመተምህረት ...የሁላችንም ስም መነሻ "መ" ፊደል ነው:: የሁላችንም የአባቶቻችን መነሻ "ታ" ፊደል ነው እናም አዋህደን ፈጥረን ነው::"

መምህሩ እየተደነቀ ተመለከታት::

"ማነው ስማችሁ?"

"እኔ ማርያማዊት ታሪኩ፣ እሱ መኑ ታምራት ፣ የሱ ሙሉጌታ ታመነ... የሱ ደግሞ ሚልከያስ ታምሩ ነው"

" ግሩም ፈጠራ ነው! ተቀመጪ!"

ተቀመጠች::

" ጥሩ! የዛሬ ውይይታችን ስለ ወደፊት ሕልማችሁ መናገር ነው:: ውድ ተማሪዎች እያንዳንዱ ሰው የተፈጠረበት ታላቅ ምክኒያት አለው:: ተማሪዎች የተፈጠራችሁት በሕይወት ዘመናችሁ አንድ ትልቅ ቁምነገር ለመስራት እንጂ እንዲሁ አይደለም ስለዚህ ህልም ሊኖራችሁ ይገባል! እናም የመጀመሪያ እድል ለመሙሚማታ ሰጠሁ:: ተራ በተራ እየተነሳችሁ የወደፊት ሕልማችሁ ምን እንደሆነ እና ለምን እንደመረጣችሁት ከነምክኒያቱ ትናገራላችሁ" መኑ ታምራት ብድግ አለ::

" እኔ ወደፊት ነጋዴ ነው መሆን የምፈልገው ይህን የተመኘሁበት ምክኒያት የሞተው አባቴ ነጋዴ ስለነበር እሱን በማየት ነው"

ሙሉጌታ ታመነ ተነሳ::

"እኔ እንደርስዎ መምህር ነው መሆን የምፈልገው ምክኒያቴ ደግሞ መምህርነት ደስ ስለሚለኝ ነው"

ማርያማዊት ተነሳች::

" እኔ የግል መፅሔት እንዲኖረኝ ነው የምፈልገው ወይም ጋዜጠኛ ምክኒያቴ ደግሞ ለሥነፅሁፍ ካለኝ ፍቅር የተነሳ ነው አመሠግናለሁ"

በመጨረሻ ሚልከያስ ተነሳ::

"አመሰግናለሁ:: ሳይኮሎጂስት ነው መሆን የምፈልገው ምክኒያቴ ደግሞ ሰዎችን መርዳት ደስ ስለሚለኝ ነው ይህ ካልተሳካ የሆቴል አስተዳደር ወይም ሠባኪ እሆናለሁ"

በዓመቱ መጨረሻ በትምህርት ቤቱ ውስጥ ሳርቅጠሉ ሁሉ መሙሚማታን ያውቅ ነበር:: በጣም እንዲታወቁ ያደረጋቸው በሁለት በሁለት ነጥብ ተበላልጠው ከአንድ እስከ

አራተኛ ተከታትለው መውጣታቸው ነበር:: አንደኛ መኑ፣ ሁለተኛ ማርያማዊት፣ ሶስተኛ ሚልክያስ አራተኛ ሙሉጌታ... አብረው ያጠናሉ:: አብረው ይዝናናሉ:: ከመሀከላቸው አንዱ ከተጣላ ተባብረው ለአራት ቅጥቅጥ ያደርጉታል!

* * *

አስራ ዘጠኝ ሰማኒያ አለፈ:: አስራ ዘጠኝ ሰማኒያ አንድም አለፈ:: 1982 ጓደኝነታቸው ጠበቀ:: ዝናቸው ከዕለት ዕለት እየጨመረ መጣ:: በዚህን ወቅት የስድስተኛ ክፍል ተማሪ ነበሩ:: ለተከታታይ ዓመታት ያስተማራቸው ሁሉም የሚወዱት እና የሚያከብሩት የFREE TALK መምህራቸው ገብቶ እንደተለመደው ሰላምታ ሰጣቸው::

" ዛሬ የምንወያየው በጓደኝነት ዙሪያ ነው:: ጥሩ ጓደኛ የምንለው እንዴት ያለ ነው? የጓደኛ ጥቅም ምንድ ነው? ጓደኝነት ራሱ ምን ማለት ነው? እያልን የራሳችንን ሀሳብ እያነሳን እንወያያለን በፍቃደኝነት ማን ይጀምራል? እንዲሁም የምትወዱት አባባል ካለም ትናገራላችሁ"

ተማሪው ሁሉ እነ መሙሚማታን ተመለከታቸው:: ውቧ ማርያማዊት ሳትግደረደር ብድግ አለች:: ወደ ጥቁር ሰሌዳው ወጣችና መናገር ጀመረች::

" ለኔ ጓደኛ ማለት እናቴ ሁሌ እንደምትነግረኝ ግማሽ አካል ማለት ነው:: ምክኒያቱም እውነተኛ ጓደኛ ከሆነ በችግራችን ሰዓት ሆነ በደስታችን ሰዓት ከእኛ ጋር ነው:: የሚስጢራችን ተካፋይ ነው:: ያስብልናል:: እናስብለታለን... አላማችን እንዲሳካ ይደግፈናል ... ጥሩ ጥሩ የሆነውን ለኔ ይመኛል:: ለምሳሌ እኛ መሙሚመታ አሁን በጣም ስለምንዋደድ አብረን እናጠናለን፣ ያልገባንን እንጠያየቃለን፣ ችግር ካጋጠመን እንወያያለን ፣ ምቀኝነት የሚባል ነገር በመሀከላችን የለብንም ባጠቃላይ ጓደኛ ማለት አስቀድሜ እንዳልኩት ግማሽ አካል ማለት ነው" አለችና አየር ወስዳ መናገር ቀጠለች::

"የምወደው አባባል ደግሞ ትንሽ አይደለህምና ትልቅ መስለህ ለመታየት አትሞክር የሚለውን ነው::

ማርያማዊት ስትገባ መምህሩ ጥቁር ሰሌዳው ላይ ከንግግሯ የወሰደውን 'ጓደኛ

ማለት ግማሽ አካል ማለት ነው የሚለውን ፃፈና ከስሩ ማርያማዊት አለበት::

ማርያማዊት ስትቀመጥ መኑ ተነሳና ሄደ:: ማርያማዊት ቆማ የነበረችበት ቦታ ዘና ብሎ ቆመ::

" ለኔ እውነተኛ ጓደኛ ማለት መፅሐፍ ላይ እንዳነበብኩት ደካማ ጎኔን የሚነግረኝ ስሳሳት የሚያርመኝ ስቸገር የሚረዳኝ ማለት ነው:: የምወደው አባባል ... ያለ ምክኒያት የተፈጠረ ማንም የለም የሚል ነው::"

መምህሩ አሁንም መኑ ከተናገረው መሀከል መርጦ ሰሌዳው ላይ ጥቅስ ፃፈ::

ሙሉጌታ ወጣ::

" አባቴ ሁሌ እንደሚነግረኝ እውነተኛ ጓደኛ ማለት እኔ ውስጥ ያለውን ተሰጥኦ ወይም የተፈጥሮ ችሎታ እንዳወጣ የሚረዳኝ እና በራሴ እንድተማመን የሚያደርገኝ ነው::

" የምትወደው አባባል?"

"እ... አለማወቅን ማወቅ ትልቅ እውቀት ነው" በማለት ተቀመጠ:: ሁሌም መጨረሻ የሚናገረው ሚልክያስ ነው:: አሁንም በመጨረሻ ወጣ:: ተማሪውን ሁሉ ተመለከተ::

" ጓደኞቼ ጥሩ ጥሩ ሀሳብ ተናግረዋል:: ለኔ ጓደኛ ማለት ሀሳቤን ሊረዳኝ የሚችል ፣ የሚያበረታታኝ፣ ከምንም በላይ ችግር በወደቀብኝ ሰዓት ከአጠገቤ የሚሆን ብቻ ሳይሆን በደስታዬም አጠገቤ የሚገኝ ነው ፤ ባይገኝም ግን ጓደኛዬ ነውና በግድ መገኘት አለበት ብዬ አልወስንም! በሀሳብ ከኔ ጋር ከሆነ ራሱ እንደተገኘ እቆጥረዋለሁ:: ባጠቃላይ ጓደኝነት ማለት ልብ ለልብ መናበብ መቻል ነው"

" የምትወደው አባባል?" አለው መምህር ካሱ ከሚልክያስ ንግግር የመረጠውን አባባል እየፃፈ::

" በነፃነት ልንኖር ክርስቶስ ነፃ አወጣን የሚለውን ከልቤ እወደዋለሁ"

* * *

በዕረፍት ሰዓት ላይከዳዱ፣ አንዱ አንዱን ሊረዳ ፍቅራቸው እንደሚዘልቅ ቃል

ተገባቡ፡፡ ይህችን ቀን ለማስታወስም አራቱም አንድ ላይ ሆነው ከትምህርት ቤት ሲወጡ ፎቶግራፍ ተነሱ፡፡ ነገር ግን በ1983 ዓ.ም ወያኔ በአፍሪካ ሀገራት ታሪክ እጅግ ዘመናዊ እና ግዙፍ ሠራዊት ገንብቶ ሲመፃደቅ የነበረውን ደርግን በሚደንቅ ሁኔታ ቅዘን በቅዘን አድርጎት ታሪካዊት ከተማ የሆነችውን አዲስ አበባን ተቆጣጠረ፡፡ ኢትዮጵያ በመንግስት ስርዓት ለውጥ ውስጥ ተዘፈቀች፡፡ አባቱ የመንግስቱ ኃይለማርያም ቀንደኛ ደጋፊ እና ባለ ስልጣን ስለ ነበሩ ቤተሰባቸውን ይዘው ወደ ራሺያ ሀገር ሊወጡ እንደሆነ እና እንዲዘጋጅ ድንገት ተነገረው፡፡

ለመጀመሪያ ጊዜ በሕይወቱ ስቅስቅ ብሎ አለቀሰ፡፡ እሱ ሲያለቅስ ሁሉም አለቀሱ፡፡ በተለይ ማርያማዊት ስቅስቅ ብላ አለቀሰች፡፡ እንደምንም ብሎ ግን ለቅሶውን ገቶ ተናገረ፡፡

" እግዚሐብሔር ከፈቀደ አንድ ቀን በእርግጠኝነት ተመልሰን አንድ ላይ እንሆናለን፡፡"

ሁሉም ተፅናኑ፡፡ አንድ ቀን ማለት መቼ እንደሆነ የሚያውቅ ከመሀከላቸው በእርግጠኝነት ባይኖርም ተስፋ ግን አደረጉ፡፡ ለሰው ልጅ ምርጥ ምግቡ ደግሞ ተስፋ ነው፡፡ ማርያማዊት እናቷ የሰጠቻትን የአንገት ብር አውልቃ አንገቱ ላይ አጠለቀችለት፡፡ መኑ እና ሙሉጌታም ያመጡለትን ስጦታ ሰጡት፡፡ በረኸርም ለቅሶ ተለያዩ፡፡ ማርያማዊት ብቻዋን ቤቱ ምሽት ላይ መጣች፡፡

" ምነው ማርያማዊት?"

"እፈልግሀለሁ!"

"በሠላም?"

" ውጪ ነው የምነግርህ ና!"

በራቸው ጋር ደረሱ፡፡ ምንም ሳትናገር አካባቢውን አማተረች፡፡ ሚልክያስ ግራ ገብቶት ያያታል፡፡ ዝምታዋ ሲቆይበት ጊዜ ተናገረ፡፡

" ምን ሆንሽ ማርያማዊት?" አላት እንደዚህ ሆና አይቷት ስለማያውቅ ደንግጦ፡፡ ምንም ሳትናገር ከንፈሩን ግጥም አድርጋ ሳመችውና ከግቢው ሮጣ አመለጠች፡፡ በግርምት

ፍዝዝ ብሎ ባለበት ቆሞ ተመለከታት:: አ...ለ...ቀ... ይህ ኢትዮጵያ ላይ የሚያስታውሰው የመጨረሻው ትዕይንት ነው :: ከዚህ በኋላ ስለ አንዳቸውም ሰምቶ አያውቅም:: ሁሌ ግን በህሊናው እንዳስታወሳቸው ነበር:: ከዛሬ ነገ... እጠይቃቸዋለሁ እያለ ሳይታወቅ አስራ ስድስት ዓመት ቀለጠ:: አሁን መምጣቱን ያፋጠነው ሚስተር ኤድዋርድ እና የሩሲያው ባለሀብት ኋጡት 300ሺ. ዶላር ነው:: በእቅዱ መሠረት ከራሱ ሂሳብ ተቀማጭም 100ሺ. ዶላር ጨምሮበት ለሶስቱ ጓደኞቹም እኩል 133,000 ሺ...133,000 ሺ. ዶላር ሊያካፍላቸው ነው ያቀደው::

አንድ ቀን ማለት አሁን መቼ እንደሆነ ገባው:: ከሰዓቶች በኋላ እትብቱ የተቀበረባትን መሬት ለመርገጥ ተዘጋጀ፤ ሚልክያስ ትምህርቱን በከፍተኛ ውጤት ራሺያ እስከሚመረቅ ሞስኮ ለዘመናት ቢኖርም! ለስራ ጉዳይ ፈረንሳይ ኑሮውን ቢያደርግም...በፈረንሳይ ውብ ከተማ ፓሪስ ቢኖርም... ከቶ አንድም ቀን አገሩን ኢትዮጵያን ሊረሳት ግን አልቻለም:: ልቡ ውስጥ ኢትዮጵያ በትልቁ ታትማለች! እናም ለአስራ ስድስት ዓመት የተለያቸውን የልጅነት ጓደኞቹን ሊያገኝ መሆኑ ሲገባው ፊቱ በራ! የመኖር ጉጉቱ ናረ...!!

እንዴ አስራስድስት ዓመት ማለት እኮ በጣም ብዙ ጊዜ ነው! አስራ ስድስት ዓመት ማለት እኮ ጳጉሜን ሳይጨምር 5840 ቀናት! 8,409,600 ደቂቃዎች ማለት ነው...ወደ ሴከንድ ቢለወጥማ የትየለሌ ይሆናል... እናም ከዚህ ሁሉ ጊዜ በኋላ ወደ ተስፋይቷ ምድር ኢትዮጵያ በመመለሱ እጅግ በጣም ልዩ በሆነ በታላቅ ሀሴት ተሞላ!! ዳግም የመወለድ ያህል ተሰማው...

# 4

# ሄላሪ

ከ9/11 ያልታሰበ አጅግ አሰቃቂ ክስተት በኋላ በመላው አለም ያሉት አገራት ሁሉ በአውሮፕላን መንገደኞች ላይ በቀጥታ ይሁን በተዘዋዋሪ ጥብቅ ቁጥጥር እንዲያደርጉ ከአለም አቀፍ ደህንነት ድርጅት መረጃ ስለተሰጣቸው በመጠኑም ቢሆን በአየርመንገዶች አካባቢ ግርግር፣ ትርምስምስ እና ፍተሻው የጠነከረ ነው::

አየር መንገዱ ውስጠኛ ክፍል ገና እንደዘለቁ በፈገግታ የተሞላች ወጣት ወደነሱ መጣች::

" ባልሳሳት ሚስተር ሚልክያስ እና ካትሪን?"

"ልክ ነሽ" አላት ሚልክያስ በወጣቷ መሳጭ ቁመና እየተደመመ::

" ከይቅርታ ጋር ተከተሉኝ!"

ተከትለዋት ሄዱ:: "VIP ROOM" ይዛቸው ገባች:: ተቀመጡ:: ጥላቸው ሄደች:: ከአምስት ደቂቃ በኋላ ተመልሳ በፈገግታ እንደተሞላች መጣች:: አብሮዋት ሌላ ሰውም መጣ::

" ዕቃቸውን ያዝላቸው" አለችው አብሮዋት የመጣውን ግለሰብ:: ሚልክያስ እና ካትሪን ሻንጣቸውን ሰጡት:: ወጣቷ እየመራቻቸው ከአየር መንገዱ ክፍል ዝነኛ እና ሀብታሞች ብቻ ከሚቀመጡበት "VIP ROOM" አስገብታቸው እና መልካም ጉዞ እንዲሆንላቸው ተመኝታ ሄደች::

በአውሮፕላን መጓዝ ለሁለቱም ብርቅ አይደለም፤ ቢሆንም ግን "VIP ROOM"

መቀመጣቸውን ወደውታል:: በተለይ ካትሪን! ብዙም ሳይቆይ ለእነርሱ የተመደበችው ውበት የፈሰሰባት ሸንቃጣ ፍልቅልቅ ኢጣሊያናዊት ሆስቴስ መጣችና ራሷን አስተዋወቀች::

"ስለተገናኘን በጣም ደስ ብሎኛል:: ሄላሪ ፒርሎ እባላለሁ የተሳፈራችሁበት ዝነኛው AIR LUFTHANSA ነው... ከፈረንሳዩ ፓርለስ ዴጎል አለም አቀፍ አየር መንገድ እስከ ኢትዮጵያ አዲስ አበባ ቦሌ አለም አቀፍ አየር መንገድ 3471 ማይልስ ወይም 5586 ኪሎ ሜትር የአየር ላይ ርቀት ሲኖረው አዲስ አበባ ለመድረስ ስምንት ሰዓት ከሀያ አንድ ደቂቃ ገደማ ይፈጃል በአዲስ አበባ እና በፓሪስ ከተማ መሀከል የአንድ ሰዓት ልዩነት ሲኖር አዲስ አበባ ከፓሪስ አንድ ሰዓት ትቀድማለች ለምሳሌ ፓሪስ ላይ 6 ሰዓት ሲሆን አዲስ አበባ ላይ ሰዓቱ 7 ሰዓት ይሆናል ማለት ነው:: ማንኛውም ጥያቄ ሲኖራችሁ መጠየቅ ይቻላል አሁን የመጀመሪያ ትዕዛዜ ምንድ ነው?"

" እናመሰግናለን! እኔ ለጊዜው ምንም አልፈልግም... ምን ይምጣልሽ ካትሪን?" አላት ሚልክያስ ካትሪንን እየተመለከተ::

" ቀለል ያለ ምግብ ባገኝ ደስ ይለኛል" ማስታወሻዋ ላይ እያሰፈረች በፈገግታ ተመለከተቻትና

" ሌላስ ካትሪን?" አለቻት ::

" ለጊዜው አመሠግናለሁ!"

ወጣች:: ውበት የፈሰሰባት ሸንቃጣዋ ሄላሪ::

* * *

በሚያምረውና ለመቀመጫነትም ለአልጋነትም በሚያገለግለው በጣም ምቹ ሶፋ ላይ ጫማውን አውልቆ ጋደም አለበት:: ካትሪንም ተቀምጣበት የነበረችበት ሶፋ ላይ እንደሚልክያስ አደረገች:: በመሀከላቸው ጠረጴዛው ላይ የነበረውን አበባ ሙሉ ለሙሉ እንዳታየው ስለከለከላት ተነስታ አወረደችው::

" ምነው አበባው ያስጠላል?"

" አበባማ የታደለ ፍጡር ነው፤ አበባን የሚጠላው ሰው የለም ግን አንተን እንዳላይ

ስለከለከለኝ ነው ያነሳውት" አለችው በፈገግታ ተሞልታ ከዚያ በቄንጠኛ ሁኔታ በመዝለል ተመልሳ ሶፋው ላይ ወጣች::

_ ነገረ ስራዋ ሁሉ ይገርመዋል:: የ17 ዓመት ውብ ወጣት መሆኑዋን እንኳ አታውቅም... ከምንም በላይ በትምህርት ቤት ውስጥ ጎበዝ ሣለች ራሷን የምትቆጥረው እንደ አንዲት ገና እውቀትን የሚጠማት ወጣት ነው... ከምንም በላይ የሚወድላት ራሷን እንደ ቢሊየነር ልጆች አለማየቷን ነው... ከማንም በላይ ስሜቱን በፍጥነት የምትረዳለት እሷ ናት:: አንዳንዴ የሚደንቀው ደግሞ ድንገት የምታነሳቸው ጥያቄዎች ናቸው::

* * *

"ሚኪ"

" አቤት"

" በልጅነት ዘመንህ ልክ ነው ብለህ አምነህ የተቀበልከው እና አሁን በወጣትነት ዘመንህ ልክ ሆኖ ያላገኘሽው ጉዳይ አለ?"

" እንዴታ... በጣም ብዙ ናቸው በዓሉ ግርማ የተባለ የአገራችን ምርጥ ደራሲ በሕይወት ውስጥ ከለውጥ በስተቀር ምንም ቋሚ ነገር የለም ይላል:: ዛሬ ትልቅ ነው የምትይው ነገር ነገ ተራ ሊሆን ይችላል በተቃራኒውም ዛሬ ተራ ነው የምትይው ጉዳይ ነገ ግዙፍ ሆኖ ሊገኝ ይችላል::"

"... የዛሬ አስተሳሰብሽ ነገ ይለወጣል ... ከፀሐይ በታች ምንም ቋሚ የሆነ ጉዳይ የለም!! እናልሽ ወደ ጥያቄሽ ሳመራ ኢትዮጵያ ውስጥ እያለሁ ኑሮ በዘዴ የሚባል ትምህርት እንማር ነበር:: አስተማሪያችን ሁልጊዜ የሚላት አንዲት ንግግር ነበረች:: 'ለሰው ልጅ እጅግ አስፈላጊ አራት ወሳኝ ነገሮች አሉ:: የሰው ልጅ ያለ እነዚህ ነገሮች ውጪ ከቶ ሊኖር አይችልም! እነዚህ ነገሮች አየር፣ ውሃ፣ ምግብ፣ ቤት ናቸው' ይለን ነበር... እንዳልሽው ዛሬ ላይ በልጅነት አዕምሮ ሳይሆን በወጣትነት አዕምሮ ሳውጠነጥን ሀሳቡ ፍፁም ስህተት ነው:: ለሰው ልጅ በሕይወት ዘመኑ እጅግ በጣም የሚያስፈልጉት ወሳኝ ነገሮች ዓላማ፣ ተስፋ፣ ፍቅር፣ እምነት

እና ሥራ ናቸው፡፡ በተለይ በሕይወት ውስጥ ለሰው ልጅ እጅግ በጣም ወሳኝ ነገር በዚች ምድር ላይ ለምን እንደተፈጠረ ራሱን ሲጠይቅ ለጥያቄው ምላሽ ሲያገኝ ምላሹንም ሲተገብር ነው! ብዙዎች ብንለፋም! ብንጥርም! ብንታትርም... በፅናት ለዘመናት ብንኖርም ለዚች ምድራችን ከራሳችንም አልፎ የሌሎችን ሕይወት የሚለውጥ ታላቅ ሥራ ብንሠራም የተሰራነው ከአፈር ነውና መሞት አይቀርም እንሞታለን በሚል ቀሽም ሰበብ በመደርደር በተስፋ መቁረጥ ባህር ውስጥ ይዘፈቃሉ... በምድር ላይ ያለው ሕይወት ሁሉ ከንቱ ነው! ንፋስን የመጨበጥ ያክል ነው ይላሉ አንቺ የ-Protagonist አመለካከት ተከታይ መሆን አለብሽ" "ምን ማለት ነው Protagonist?"

"ሁለት ግዙፍ የሕይወት አመለካከት ግንባሮች አሉ፡፡ Protagonist እና Antagonist በሚል ይጠራሉ፡፡ የፕሮታጎኒስት ተከታዮች የሰው ልጅ እያንዳንዱን ቀን በታላቅ ትጋት መስራት አለባቸው! በቻሉት መጠን ከራሳቸውም አልፈው ለሌላው የሚጠቅም አንዳች ቀና የሆነ ነገር መፈፀም አለባቸው! በህይወት ለሚያጋጥማቸው እያንዳንዱ መልካም ሆነ አሳዛኝ ገጠመኝ ሳይገበሩ ሕይወትን ወደፊት መቀጠል አለባቸው ምክኒያቱም እያንዳንዱ የሰው ልጅ በምድር ላይ የተፈጠረበት ትልቁ ምክኒያት በሕይወት ዘመኑ አንዳች መልካም ነገር ለመስራት እንጂ ኖሮ ኖሮ ለመሞት አይደለም ሲሉ አንታጎኒስቶች ደግሞ የሰው ልጅ ሞትን ማሸነፍ ካልቻለ አልያም የሰው ልጅ መጨረሻው ሞት ከሆነ ሕይወት ማለት ነገ ሳትሆን ዛሬ ብቻ ናት! ስለዚህ የሰው ልጅ መኖር ያለበት ዛሬን ብቻ ባሻው መንገድ መሆን አለበት ሥራ! አላማ! ፅናት! ግብ ... ራዕይ... ወዘተ የሚባል ኮተት ሁሉ ከንቱ ነው! እጅግ መናጢ የሆነው ግለሰብ መጨረሻው ሞት ነው! እጅግ የናጠጠው ሀብታም መጨረሻው ሞት ነው! ጠቅላይ ሚኒስቴሩ ይሞታል! ኩሊውም ይሞታል! የተማረውም ይሞታል! ያልተማረውም ይሞታል! ... ስኬታማውም ይሞታል! ስኬት አልባውም ይሞታል... ታዲያ ምን አስለፋን ...ሞት የማይቀር ከሆነ የሰው ልጅ ነገን እያሰበ ሳይሆን ዛሬን ብቻ መኖር አለበት! ምክኒያቱም የሰው ልጅ ምንም ይሁን ምንም መጨረሻው ሞት ነውና የሚል ጨለምተኝነት ያለው አመለካከት ያራምዳሉ! በጣም የሚደንቅሽ ምድራችን ላይ ካሉት በቢሊዮን የሚቆጠሩ

ህዝቦች መሀከል 75% የAntagonist አመለካከትን አሰበውት ይሁን ሳያስቡት ያራምዳሉ:: 25% ብቻ የ Protagonist አመለካከት ተከታዮች ናቸው:: ደስ የሚለው ነገር ግን ይቺ አለማችንን የሚያሽከረከሩዋት እነዚህ 25% ብቻ የሆኑት ጥቂቶች ናቸው!እነዚህ ጥቂቶች ፕሮታጎኒስቶች ባይኖሩ ይቺ ዓለማችን በጨለማ ትዋጥ ነበር:: ከእነዚህ 25% ጥቂቶች አንደኛዋ አንቺ መሆን አለብሽ! አንቺም የ protagonist ተከታይ መሆን አለብሽ! protagonist ከሆንሽ ደግሞ እያንዳንዱዋ የሕይወት እንቅስቃሴሽን በማስተዋል እና በጥንቃቄ መምረጥ መቻል አለብሽ:: መወላወል የለብሽም! በሕይወት ጉዞ ላይ የምትወላውይ ከሆነ ደስታ ካንቺ ትርቃለች! ከምንም በላይ ማወቅ ያለብሽ አንድ ትልቅ ሀቅ ቢሊየነር አባትሽ እጅግ ግዙፍ የሆነውን ሀብቱን ሆነ በተለያዩ ሀገራት የሚገኙትን ድርጅቶቹን ከማማው ላይ ሆነሽ እንድትመሪያቸው ትልቅ ኃላፊነት የሚሰጠው ላንቺ ለበኩር ልጁ ነው! ስለዚህ ለዚያ የሚሆን ታላቅ አስተዋይነት ካንቺ ይጠበቃል! ያንቺ እኩያዎች ሊጠጡ፣ ሊያጨሱ፣ሊወልዱ፣ማድረግ የሌለባቸውን ነገሮች እንዳሻቸው ሊከውኑ ይችላሉ አንቺ ግን እነርሱ ያደረጉትን ሁሉ ማድረግ አትችይም! ምክኒያቱም አንቺ ከ75% ቶቹ ውስጥ ሳትሆኚ ከምርጦቹ ከ 25% ከሆኑት protagonist ምድብ ነሽና! አንቺ ወደፊት ግዙፍ ሃላፊነት ያለብሽ ነሽና! መራመድ ያለብሽ በማስተዋል መሆን አለበት በዚያ ላይ ለኔ ትልቅ ጀግና የሚባለው ለዓላማው ስኬት ሲል ስሜቱን መቆጣጠር የሚችል ግለሰብ ነው... እንደዚያ ስልሽ ደግሞ protagonist የሆኑ ሰዎች የሚዝናኑበት ጊዜ የላቸውም አልያም አያስፈልጋቸውም ማለቴ ግን ጨርሶ አይደለም"

* * *

"ሚኪ"

"አቤት"

" ለበርካታ ጊዜያት ያሰብከው እና አሁንም የምታስበው ወይም ለበርካታ ጊዜያት ራስህን የጠየከው ጥያቄ ምንድ ነው?"

"እህ... ለበርካታ ዘመናት ራሴን ስጠይቅ የነበረው ጥያቄ ፍቅር ምንድ ነው

የሚለውን ነበር? መፅሐፍ ቅዱስ ስለ ፍቅር ምን ይላል? ቁራዐን ስለ ፍቅር ምን ይላል? ሰዎች ስለ ፍቅር ምን ይላሉ? ፈላስፎች ስለ ፍቅር ምን ይላሉ? አፍቃሪዎች ስለ ፍቅር ምን ይላሉ?... በመጨረሻ ስለ ፍቅር ያገኘሁት ትልቅ እውነታ ይቺ ምድር ያለ ፍቅር ከንቱ መሆኑዋን ነው:: ታዲያ በዚህች ምድር ላይ ለሚኖር ሰው እጅግ አስፈላጊ የሆነው ፍቅር መገኛው የት ነው ስል ራሴን ለዘመናት ጠየኩ! ምላሹ ፍቅር ያለው በውስጣችን እንጂ ከሌላ የምንቀበለው ነገር አለመሆኑን ነው:: ፍቅር መቀበል ሳይሆን መስጠት ነው! ፍቅር ደግ፣ ሩህሩህ፣ ቸር መሆን ነው! ፍቅር ለራስ ሆነ ለሌሎች ሰዎች መልካም ነገር ማድረግ ነው! ፍቅር በቅንነት መሞላት ነው! ፍቅር ከክፋት፣ ከስግብግብነት ፣ ከራስ ወዳድነት ፣ ከተስፋ መቁረጥ ፣ ከዓላማ ቢስነት መሸሽ ነው... ፍቅር መልካም ነገር በተግባር መከወን ነው! ፍቅር በልበ ሙሉነት መሞላት ነው! ፍቅር በአሸናፊነት መሞላት ነው! ፍቅር በራስ መተማመን ነው! ፍቅር ለራስ ሆነ ለሌሎች ትልቅ ግምት መስጠት ነው! ፍቅር በጠማማው ጎዳና ሳይሆን በቀናው መንገድ መራመድ ነው! Love is choosing to do kind, unselfish deeds for the other. Love is not just a feeling. Love is what we do. Love is Action. ፍቅር ቃል ሳይሆን፣ ፍቅር ስሜት ሳይሆን፣ ፍቅር ድርጊት ነው! ፍቅር ጨለማ ውስጥ ብርሃን እንዳለ ማመን ነው! ፍቅር ታላቅ ሀዘንን በደስታ መለወጥ ነው! ፍቅር ራስን በሌሎች ሰዎች ቦታ አስቀምጦ ማሰብ የመቻል ጥበብ ነው::... በጣም አሳዛኙ ነገር በጣም በርካቶች ፍቅር ማለት የሆነ ሱፐር ማርኬት ውስጥ ገብተን እንደምንገዛው ሸቀጥ አድርገው ይቆጥሩታል! ፍቅር ከሌላ ወገን የሚመጣ እንጂ ውስጣቸው ያለ አንቃቂ ረቂቅ ነገር አይመስላቸውም!! በዚያ ላይ ትልቁ ችግር አብዛኛው ሰው ፍቅር እና መውደድን አንድ በማድረግ ይፈታቸዋል!

ፍቅር ድርጊት ነው! መውደድ ስሜት ነው!

ፍቅር ቋሚ ነው! መውደድ ይለዋወጣል!

ፍቅር ይፀናል! መውደድ አይፀናም!

ፍቅር ይታገሳል ! መውደድ ይወላውላል!

ፍቅር ምክኒያት የለውም! አንድን ሰው ለመውደድ ግን ምክኒያት ያስፈልጋል... መውደድ እንደ አየር ንብረቱ ይለዋወጣል... ፍቅር ግን አይታበይም ... ስለ ፍቅር እና ስለ መውደድ በርካታ ጊዜያት ራሴን ጠይቄያለሁ ወደፊትም የምጠይቅ ይመስለኛል::"

"ሚኪ"

"አቤት"

*　　*　　*

"እግዚአብሔር ሰውን የፈጠረው ብቻውን መሆን ስለፈራ ነው ወይስ ስልጣን ስለሚወድ ነው?"... በትምህርት ቤትም የመፅሐፍ ቅዱስ አስተማሪዋ ዘወትር ሊያስተምራቸው ሲገባ ካትሪን አንድ አስቸጋሪ ጥያቄ እንደምትጠይቀው ሁሌ በእርግጠኝነት ነበር የሚገባው:: ከማይረሳቸው ጥያቄዎች አንደኛው

"Professor" /መምህር/

" አቤት ካትሪን"

" እግዚአብሔር ሚስት ቢኖረው የአለም ቅርፅ በተሻለ መልኩ አይለወጥም ነበር?"

*　　*　　*

ሚልክያስ አተኛኘቷን አይቶ ሰዓሊ ቢሆን በጣም ተመኘ:: እንዴት ለስዕል ትመች ነበር ?"

" የሆነ ነገር እያሰብክ ነው?"

" በምን አወቅሽ?"

"የሚገርምህ የምታስበው ስለ እኔ ነው"

"ለምን ሳይካትሪስት አትሆኚም ግን?"

" እሱ ያንተ የልጅነት ህልም ነው"

ልብ የምታሸብረው ኢጣሊያናዊት ሆስቴስ ሄላሪ በፈገግታ አሸብርቃ ጠረጴዛ እየገፋች መጣች::

" ይኸው ውድ ካትሪን"

" አመሠግናለሁ! ከይቅርታ ጋር ቴሌቪዥኑን ድምፁ ሳይበዛ ከፈትው..." ሄላሪ የታዘዘችውን

ፈፀመች:: ካትሪን ለመመገብ ተስተካከላ ተቀመጠች:: ለሚልክያስ አልፈልግም ማለት አልፈልግም ስለሆነ እንብላ አላለችውም:: በልታ ስትጨርስ አይኑን እንደከደነ ስትመለከት አንቅልፍ እንዳሸለበው አወቀች:: ጠረጴዛው ላይ ከነበሩት "Buttons" ቀዩን ተጫነችው:: ኢጣሊያናዊቷ ሆስቴስ ሄላሪ አሁንም በፈገግታ ታጅባ መጣች:: ሲያወሩ እንዳይነቃ በምልክት ልብስ አንድትደርብለት ነገረቻት:: ሄላሪ የታዘዘችውን ፈፀመች::

* * *

ከግማሽ ሰዓት በኋላ ካትሪንም አሸልባ ነበር:: ሄላሪ መጥታ ካትሪንንም ካለበሰች በኋላ ቴሌቪዥኑን "Mute" አድርጋው በሩን ዘግታ ወጣች:: ቀጣዩ ስራዋ መንገደኞቹ መሬት እስከሚደርሱ በየአስር ደቂቃው ልዩነት እየመጣች መመልከት ... ከእንቅልፋቸው ሲነቁ የሚያስፈልጋቸውን ነገር ማምጣት እንደሆነ ታውቃለች:: ስራዋ ተመሳሳይ ነው፤ ግን ትወደዋለች:: ሄላሪ "ከመንገደኞቿ" ሁሉ መቼም የማትረሳው ዳንት ቴሪ የተባለውን ደቡብ ፈረንሳያዊ ወጣት ነው:: እዚሁ VIP room ብቻውን ነበር የተመደበው:: የሰውነት ቅርፁ በጣም የሚያስጎመጅ ነበር::

" የመጀመሪያ ትዕዛዜ ምንድ ነው ጌታዬ?" አለች ውብ ፈገግታዋን እየመገበችው::

" ይሄን ውብ ፈገግታሽን ማስወገድ!" ደንግጣ ከው አለች:: ስንቶች ሲያገኙዋት የሚሰጧት የመጀመሪያ ትልቅ ሽልማት "ፈገግታሽ ገዳይ ነው" ነበር የሚሏት::

" ሌ...ላስ?"

" አመሠግናለሁ! Merci" ወጣች:: ከአስር ደቂቃ በኋላ ተመልሳ ስትመጣ ከላይ ራቁቱን ሆኖ ጠረጴዛው ላይ ሽራ ዘርግቶ እየተጠበበ ነበር:: ከው ብላ ስሙን ለማስታወስ ስትሞክር ለካ! አጠገቧ ያለው ከዝናው የተነሳ 'ትንሹ ሊዮናርዶ ዳቪንቺ' እያሉ የሚጠሩት ዝነኛ ወጣት ሰዓሊ መሆኑን አወቀች:: እንዳትረብሸው በዝምታ ተመልሳ ወጣች:: ከአስር ደቂቃ በኋላ ተመልሳ መጣች:: እየሰራ ነው... ተመልሳ ወጣች ... ከአስር ደቂቃ በኋላ ተመልሳ መጣች::

... ጨርሶ ስዕሉን እየተመለከተ አገኘችው:: ፈገግ ልትል አሰበችና ቅድም ያላት ንግግር ትዝ

ብሏት...በመተው...

"የሚያስፈልግ ነገር አለ ጌታዬ" አለችው

" ነይ እስቲ ተቀመጪ የኔ ውብ፡፡" አላት፡፡

ያለማቅማማት ተቀመጠች፡፡

" ሕይወት ያለ ፈገግታ ምን እንደምትመስል አየሽ?" ከው አለች! የራሷን ምስል ነበር የምታየው! ለቅፅበት ደንግጣ ከው ባለችበት አፍታ አዕምሮው ውስጥ የቀረፀውን ምስል ነበር ነድፎ የሰጣት...

" ጠቢብ ነህ ማለት ነው?"

" ሰዓሊ ነኝ"

" ሰዓሊ ማለት እኮ ጠቢብ ማለት ነው"

" አንድ ስዕል ስለሳልኩ? አንድ ሰዓሊ ቀለም እና ሸራን አገናኝቶ ምስል ስለፈጠረ ጠቢብ ሊሆን ይችላል? በጭራሽ! አለምን ከነግሳንግሷ የፈጠረው እግዜር ብቻ ነው ጠቢብ የሚባለው ቆንጂት... እንጂ አንድ ሰዓሊ ራሱን ልዩ አድርጎ የሚያይ ከሆነ ወይም አንድ ሰዓሊ በስራው ልቡ በኩራት ካበጠች አለቀለት! እሱ ምኝ ነው በምድር ላይ ማንም የተለየ ፍጡር የለም፡፡ ማንኛውም ሰው ፀጋ አለው፡፡ ትልቁ ችግር ያን የሚረዱት ጥቂቶች ብቻ ናቸው፡፡ አያሌዎች ፀጋ እንዳላቸው ሳይረዱት ሆነ ሳያውቁት በጨለማ ውስጥ እንዳስቀመጡት ይሞታሉ!!..."ብዙ ነበር የነገራት ... በእርግጥ በመጨረሻ ትዝ የሚላት ነገር እንዴት እንደሆነ ባታውቀውም በአውሮፕላን ውስጥ የመጀመሪያዋን ወሲብ ፈፀመች፡፡ አለቀ፡፡ ከዚያ በኋላ የተፈጠረውን አታውቀውም ብታውቀውም መናገር አትፈልግም፡፡ በአውሮፕላን ውስጥ "ከደንበኛ" ጋር ወሲብ ማድረጓ ቢታወቅ ኖሮ ያለ አንዳች ድርድር ትባረር ነበር፡፡ አጋጣሚ ትረፊ ሲላት የዛንዕለት የአውሮፕላኑ ድብቅ ካሜራ አይሰራም ነበር፡፡

... ሄላሪ ማግባት አትፈልግም! በመሬት ላይ መኖርም አትፈልግም... በቃ ሕይወት ለሷ በአውሮፕላን ከሀገር ወደ ሀገር መዞር ብቻ ናት...ከአስር ደቂቃ በኋላ ተመልሳ መጣች፡፡ ሁለቱም ተኝተዋል፡፡

* * *

ሚልክያስ በስንት አንድ ጊዜ በሚያገኘው ይህን መሰል እንቅልፍ የቀሰቀሰው የሞባይል ጩኸት ነበር፡፡ እንዳልዘጋው አሁን ነው ያወቀው፡፡ ብዛት ያላቸው ደንበኞች እረፍት ላይ መሆኑን ስለማያውቁ በየትኛውም ቦታ ሆነ አገር ያለ አንዳች ችግር ጥሪ በሚቀበለው ዘመናዊ ሞባይሉ ላይ ይደውሉለታል፡፡ አሁን ነው ትዝ ያለው፡፡ እንዳለው ገና ሀሎ ሲል ገባው፤

"ሚስተር ሚልክያስ! ቫንቬዝ ነኝ ከሆላንድ የ..." አጠር አድርጎ ነገረውና ስልኩን ጨርሶ ከአገልግሎት ውጪ አደረገው፡፡ ከፍሉን ሲቃኝ ካትሪን እንደተኛች ተረዳ፡፡ ሰውነቱ ዝሎ እንደ ነበር አሁን ነው የገባው፡፡ ተነስቶ ሽንት ቤት ሄደ፡፡ ከሽንት ቤት ሲመለስ በሩ ላይ ኢጣሊያናዊቷ ውብ ሄላሪ ቆማ አያት፡፡ በውበቷ እጅግ ተደነቀ፡፡

"መኝታው እንዴት ነበር ጌታዬ?"

"ሳላስበው አሸለበኝ በጣም አሪፍ ነበር" ብዙ ወንድ "ደንበኛ" የሚሰጣት መልስ ግን ተመሳሳይ ነበር፡፡ ተኝተው ሲነሱ ጠብቃ 'መኝታው እንዴት ነበር...' ትላለች የልምድ ነገር ሆኖባት፡፡ የደንበኞቿን ምቾት የመጠበቅ ሀላፊነት የሥራ ግዴታዋ ጭምር ነው፡፡

' ጥሩ አልነበረም '

' ምነው ጌታዬ'

'ፈገግታሽ እየመጣ እየረበሸኝ እንዴት ይተኛል..."

" ምን ላምጣልህ " አለችው ሚልክያስን፡፡

" ምግብ እና ቀዝቀዝ ያለ ነገር ካላስቸገርኩሽ ብታመጪልኝ እደሰታለሁ"

" ግዴታዬ እናተን ማስደሰት ነው" አለችው ፍፁም ትህትና ባዘለው አነጋገሩ እየተደሰተች፡፡ ሚልክያስ ወደ ክፍሉ ሲገባ ሄላሪ ወደ ምግብ ቤት አመራች፡፡ ቀለል ያለ አልባሳትን በፍጥነት ቀያየረና ዘና ብሎ ተቀመጠ፡፡ አፍታም ሳትቆይ ምግቡ መጣለት፡፡ ተመገበ፡፡ ሲጨርስ መጥሪያውን ተጫነው፡፡ ሄላሪ መጥታ ወሰደችው፡፡ ተመልሳ መጣች፡፡

" መንቀሳቀስ ከፈለክ..."

" ችግር የለውም እመሠግናለሁ ይልቅ ቁጭ በይ እስቲ" ተቀመጠች፡፡

"ኢትዮጵያ ስንት ጊዜ ሄድሽ?"

" ስድስት .. ሰባት .. ጊዜ ይመስለኛል በደንብ አላስታውሰውም አይዞህ በጣም የምትመች አገር ናት! ለጉብኝት እየሄዳችሁ ነው?"

እርግጥ ለማያውቀው ሰው ኢትዮጵያዊ ነኝ ቢል አያምኑትም የአፍሪካ ዝርያ ያለበት ጠይም ፈረንሳያዊ ወይም ብራዚሊያዊ ነኝ ቢል ያምኑታል:: መልከመልካም ፈረንሲያዊ እንደሆነ ብዙዎች ነግረውታል ስለዚህም ነው ሄላሪም ኢትዮጵያዊ በፍፁም ይሆናል ብላ ስላልገመተች ለጉብኝት ነው ወይ ያለችው::

" ኢትዮጵያዊ ነኝ"

"እየቀለድክብኝ መሆን አለበት?"

"በጭራሽ! ንፁህ ኢትዮጵያዊ ነኝ"

"ለየት ያለ የቆዳ ቀለም ነው ያለህ? አትመስልም! የኢትዮጵያዊያንን መልካቸውን በጣም ነው የማውቀው በጭራሽ ግን አትመስላቸውም::"

"ልክ ነሽ! ግን እኔ ኢትዮጵያዊ ነኝ ኢትዮጵያዊነቴን ደግሞ መቼም አልረሳም በጣም እኮራበታለሁ! እንደዚያ ስልሽ ዘረኝነት ግን የለብኝም!!"

"እረዳሀለሁ! ኢጣሊያዊ ነኝ! ኢትዮጵያን በደንብ አውቃታለሁ! የአባቴ አባት አባት ወታደር ነበር የሞተው ኢትዮጵያ ውስጥ ነበር... አሁን ኢትዮጵያ ናፈቀችህ?"

"ማንም የተወለደበትን አገር ምንም ትሁን ምንም ከልቡ መዝገብ ላይ ሊፍቅ አይችልም!በተለይ ኢትዮጵያኖች አይችሉም! 'ኢትዮጵያዊ ኢትዮጵያዊነቱን ነብር ዥጉርጉርነቱን ...' መፅሐፍ ቅዱስ እንኳን ይላል:: እርግጥ ሀገሬም ናፍቃኛለች ግን ከሁሉም በላይ ጓደኞቼ ናቸው የናፈቁኝ! በዚያ ላይ ቃል ገብቻለሁ ያን ደግሞ መፈፀም አለብኝ በእነዚህ ምክኒያቶች ነው ወደ ሀገሬ የማመራው"

ጓደኛ! ጓደኛ ማለት ምንድ ነው? ለመሆኑ የጓደኝነት መሰፈርቱ ምንድ ነው? ዘር..? ሀይማኖት? ብሔር? ገንዘብ? ጥቅም ... እከክልኝ ልከክልህ? አጋጣሚ ... አብሮ ማደግ? በዓላማ መመሳሰል? የልብ ጥምረት መፍጠር?... ጓደኝነት መነሻ አለው? ካለውስ

መነሻው ምንድ ነው? ጓደኝነት ድንበር አለው? ካለውስ ምንድ ነው? እውነተኛ ጓደኝነት አብሮ መብላት አብሮ መጠጣት አብሮ መዝናናት ... አብሮ ጊዜን ማጥፋት ነው አልያስ ከዚያ በላይ የዘለለ?... ብዙ ጊዜ አስባበታለች ምላሽ ግን የላትም -ለውቧ ኢጣሊያናዊት ሄላሪ ... ምናልባት ግን ለሄላሪ ጓደኛ ማለት አብሮዋት ጊዜውን የሚያሳልፍ ነው:: ጓደኛ ስለሌላት አይደለም እንጂ መሬት ላይ መኖር የሚያስጠላት... ርዕሱ ስለማይገባት ዝም አለችው:: እናት የላትም! አባት የላትም! ወንድም የላትም! እህትም የላትም... ፍቅረኛ የላትም.. በቃ ፍፁም ብቸኛ ነች:: አባቷ በዘመነ እርጅናው እናቷን አገባ:: በስንት ጥረት ሄላሪ ተወለደች፡ ብቸኛ ልጃቸውን በሚገባ ሳያሳድጉዋት ሁለቱም ብካንሰር ህመም ሞቱ:: ሄላሪ በራሷ ታላቅ ጥረት ለስኬት በቃች... ውበቷን እና ብዙ የቋንቋ መናገር ብቃቷን ተጠቅማ በኢጣሊያ ዝነኛ ከሆነው አየር መንገድ ለመቀጠር ተወዳደረች:: በብቃት  አለፈች:: አብዛኛውን ሰዓት ስራ ፣ የተቀረውን ንባብ እያለች ሕይወቷን መምራት ያዘች... በውበቷ የተነሳ ብዙ ወንዶች ጠጋ ጠጋ ማለት ጀመሩ:: ማንኛዋም ሴት ልጅ ያለ ፍቅር መኖር አይቻላትምና በመጨረሻ ተሸነፈች:: መቼም ከብቸኝነት አለችና የተሻለ ነው የምትለውን ፍቅረኛ መረጠች ...ለተወሰነ ወራት አዲስ ደስ የሚል ሕይወት አየች:: በሀሴት ተሞላች፤ ቅሉ ግን ፍቅረኛዋ በጣም ቅናተኛ ስለነበር እጅግ ጭቅጭቅ እና ንዝንዝ ሲያበዛባት የትወጣሽ? የትገባሽ?" ከማን ጋር ነበርሽ? አንዳንዴም ቡጢ ሲያበዛባት... ፍቅሩን ቅናቱን በዱላ ሲገልፅላት አህያህን ፈልግ በማለት ሳይቃጠል በቅጠል ብላ የትውልድ ሀገሯን ኢጣሊያን በመተው ወደ ፈረንሳይ ሉፍታንዛ አየር መንገድ ተወዳድራ በብቃት በማለፍ ሕይወቷን በመሬት ላይ ሳይሆን በአየር ላይ ለማድረግ ወሰነች:: በተለይ ለዚህ ውሳኔ ያበቃት ለንዴት ማብረጃ ብላ የተዋወቀችው ሁለተኛዋ ፍቅረኛዋ ለሁለት ወር ያህል እስከሚበቃው ወሲብ ከፈፀመባት በኋላ 'አንቺ ውብ ሴት ነሽ ውብ ሴት ደግሞ ለወሲብ እንጂ ለትዳር አትሆንም' ብሏት በጠፋ በማግሰቱ ነበር::

... ከጉዞ በተረፋት ሰዓት የታሪክ መፅሐፍትን ብቻ ታነባለች፤ ከፍቅር ውጪ ይዘት ያላቸውን ፊልሞች ታያለች... በተለይ ሳይንሳዊ ይዘት ያላቸው ፊልሞች ግንባር ቀደም ምርጫዋ ናቸው::

"በነገራችን ላይ አሁን ለሶስተኛ ጊዜ ሳይሽ ነው ጓደኛ የሚባል ለምንድነው የሌለሽ?"

በጣም በትኩረት ተመለከተችው:: ይህ ውብ ወጣት ስለምን እያወራ ነው? እሷ አታውቀውም እሱ አውቅሻለሁ እያላት ነው... የት? አውሮፕላን ውስጥ ? በጭራሽ... ሁሉንም ታስታውሳቸዋለች ... ታዲያ የት?

" አልገባኝም?"

"Paris Le Sheraton ሁለቴ ለሁለት ቀናት አርፈሽ ነበር:: በሁለቱም ጊዜዎች ለረጅም ሰዓታት የታሪክ መፅሐፍ እያነበብሽ ብቻሽን ነበርሽ:: ያኔ ጓደኛ ባይኖራት ነው ስል ደመደምኩ!"

"እ! አምላኬ! አንተም እዛ አርፈህ ነበርህ ማለት ነው?"

" እዛው ሰራተኛ ነገር ነኝ"

" በጣም የምወደው ሆቴል ነው:: መሬት ላይ ካሉት መዝናኛዎች Paris Le Sheraton ደስ ይለኛል:: ገነት ውስጥ የገባሁ ያህል ይሰማኛል:: ንፁህ አየር ያለው እዛ ብቻ ይመስለኛል:: እንዳልከው ምናልባት የታደልኩ አይደለሁም! ጓደኛ የለኝም! ስለ ጓደኛ ራሱ ግልፅ የሆነ ትርጉም የለኝም! አላውቀውም ይልቅ የሆቴሉ ወጣት አስተዳደር በጣም ጥሩ ሰው እንደሆነ ይወራል:: የሚገርምህ ከኢትዮጵያ መልስ አሁንም ለሁለት ቀናት እዛው ለመሆን እቅድ አለኝ"

"መልካም ጊዜ እንዲሆንልሽ እመኛለሁ"

" እንዴት ግን አስታወስከኝ?"

እሷን እንዴ የተመለከታት ሁሉ ያስታወሳታል እናም መልሱ 'አንቺን የመሰለች ቆንጆ ማን አይቶ ይረሳል'እንደሚሆን ገመተች:: ሁሉም ወንዶች የሚሏት ንግግር ያን ነውና::

" ፀሐፊዬ ጋር ሁለቴ ገብተሽ ነበር"

"ፀሐፊዬ? አንተ ማለት አስ... ተዳደሩ ነህ?"አለችው በጣም ተገርማ::

"ልክ ነሽ"

አብዛኛውን ጊዜ VIP Room የሚመጡ ሰዎች መግለጫ ቀደም ነው

የሚመጣላቸው:: ታዋቂው ዘፋኝ ነው... ዝነኛው ሰዓሊ ነው ... ዝነኛው ደራሲ ነው... ስመጥሩ እግር ኳስ አንከባላይ ነው... ታዋቂው ዲዛይነር ነው/ነች... ወዘተ ይልና የመጨረሻው ዐረፍተ ነገር " በደንብ ይስተናገዱ" የሚል ይሆናል፤ ባንጻሩ ግን ለሚልከያስና ካትሪን የመጣው መግለጫ አጭር ነበረች::

`ካትሪን እና ሚልከያስ አስፈላጊው እንክብካቤ ይደረግላቸው ፲ኛ ማዕረግ` አለቀ:: እሷም ስራቸው ምንድ ነው እያለች ስትገረም ነበር:: አሁን እስከሰማችበት ደቂቃ ድረስ::

" ታድለህ! ያን የሚያክል ግዙፍ ሆቴል ማስተዳደር ግን አያስቸግርህም? እኔ የምገምተው አርባዎቹ መጀመሪያ የሚገኝ ሰው ነበር እንጂ አንተን የመሰለ ..." ብላ ዝም አለች::

ካትሪን የተቀባችው ሽቶ እጅግ ደስ ይላል:: ለነገሩ ከፓሪስ አይደለም የተነሳችው? ፓሪስና ሽቶ የሳንቲም ገፅታዎች ናቸው፡፡ ፈረንሳዮችም በምርጥ ሽቶ አምራችነት እና ፒዛን በመብላት አለምን በቁጥር አንድ ይመራሉ::

"በነገራችን ላይ ሽቶሽ በጣም ደስ ይላል"

"አመሠግናለሁ!" አለችና ድንገት ተነሳች:: ይቅርታ ጠይቃው ሄደች:: አፍታም ሳትቆይ ተመልሳ መጣች:: ሾንገፑር 407የሚል እጅግ በጣም ውድ ሽቶ ይዛለት ተመለሰች::

" ስጦታ አመጣሁልህ"

" እጅግ በጣም አመሠግናለሁ"

" ምንም አይደለም" አለችው::

"ጥያቄዬን ግን አልመለስሽልኝም"

"በመጠኑ መልሻለሁ! ጓደኛ የለኝም የኔ ሕይወት በብቸኝነት የተሞላ ነው" ብላ በመጀመር ስለ ቤተሰቧ እና በተለይ ስለ መጀመሪያ የፍቅር ሕይወቷ ነገረችው:: ምክኒያቱ ባይገባትም በግልፅነት ደስ እያላት የስራዋን ባህሪ እና የእረፍት ጊዜዋን እንዴት እንደምታጠፋ ጭምር ነገረችው:: ስለነገረችውም ልቧ በሀሴት ተሞላች::

ሚልከያስ በሀዘን ራሱን ነቀነቀ:: በሕይወቱ ፍፁም ብቸኛ የሆነ ሰው በጣም

ያሳዝነዋል።

" በዚች ውጥንቅጥ በሆነች ዓለም ውስጥ ሰው ብቻውን ይሆን ዘንድ መልካም አይደለም! ሕይወትን ያለ ጓደኛ በብቸኝነት ለመምራት መሞከር በጣም አስቸጋሪ ነው በሀዘንም በደስታም ያን ሀዘን ሆነ ደስታ የሚጋራ የሆነ ሰው አስፈላጊ ነው በተለይ መታመም አለ በዚያን ሰዓት ደግሞ አጠገብሽ ሊሆን የሚገባ የሆነ ሰው ግዴታ ነው! ደስተኛ ሆነሽ እንኳ ያን ደስታሽን የምታካፊይው ሰው አጠገብሽ ከሌለ ደስታሽ ከንቱ ይሆናል!! የሰው ልጅ ማህበራዊ እንስሳ ነው! በሰዎች መሀከል ተፈጥረን በሰዎች መሀከል ብቸኛ ሆነን መኖር አስቸጋሪ ነው! ስለዚህ ለጊዜው ምንም ላይመስልሽ ይችል ይሆናል! የግድ ግን ጓደኛ መያዝ ያለብሽ ይመስለኛል። ጓደኛ ስልሽ ፍቅረኛ ወይም ትዳር ማለቴ አይደለም! ስለ አንቺ እርግጠኛ በመሆን መናገር አልችልም ለኔ ግን ሕይወት ያለ ጓደኛ እጅግ በጣም አስቸጋሪ የምትሆን ይመስለኛል! ብቸኝነት በጣም አስቸጋሪ ነገር ይመስለኛል! አንድ መፅሐፍ ላይ ምንም ጓደኛ ከሌለው ቢያንስ ዝርክርክ የማይረባ ጓደኛ ያለው የተሻለ ነው ምክኒያቱም እውነተኛ ጓደኝነት ማለት መቀበል ሳይሆን መስጠት ነው! ጥሩ ጓደኛ መፈለግ ሳይሆን ጠማማውን ማቃናት ነው! ሱሰኛ ያልሆነን ጓደኛ መፈለግ ሳይሆን ሱሰኛውን ከሱሱ ማላቀቅ ነው! መልካምነትን መጠበቅ ሳይሆን መልካምነትን መስጠት ነው! ቀናነትን መጠበቅ ሳይሆን ቀና መሆን ነው! ጓደኝነት ማለት In every thing, do to others as you would have them do to you, for this is the Law and the prophets` የሚለውን ወርቅማ ህግ መሠረት አድርጎ የሚገነባ ከራስ ወዳድነት እጥር ያልታጠረ ግንብ ነው! በምድር ላይ ስለራስ ስኬት እና ደስታ ብቻ እያሰቡ መኖር ኑሮ አይባልም። ስለዚህ እንደኔ ሀሳብ ቢያንስ በጣት የሚቆጠሩ ጓደኞች ሊኖሩሽ ይገባል ባይ ነኝ" አላት በዝምታ ራሷን ነቀነቀች። ምንም ሳትናገር በዝምታ ትቃኘው ገባች። እርጋታው ደስ አላት። ሲያወራ ደሞ የድምፁ ቃና ደስ ማለቱ... ምክኒያቱን ባታውቀውም ስለ እሱ ብዙ ለማወቅ ፈለገች። ቀስብላ አስሩንም ጣቶቹን ተመለከተች። ምንም ቀለበት የሚባል ነገር የለም... 'እሰይ ሚስት የለውም ማለት ነው' አለች ለራሷ። አስሩን ጣቶቹን ስትቃኝ በአይኑ

ድንገት ስለያዛት ከው አለች:: ለዘመናት ያህል የምታውቀው ሰው መሰላት... አይኑዋን ወደተኛችው ካትሪን ላከች:: ምኑ ትሆን? በዘዴ ለመጠየቅ ወሰነች::

" እህትህ እንቅልፍ እንደወሰዳት ..." ብላ ሳትጨርስ ልክ እስካሁን ሲያወሩ የነበሩትን ስታዳምጥ እንደነበረች ድንገት

" እህቱ አይደለሁም!!" ብላ ሁለቱንም ከው አደረገቻቸው::

" በጣም ይቅርታ ካትሪን ስናወራ ረበሽንሽ ..."

" ችግር የለውም! ካላስቸገርኩሽ የሚጠጣ ነገር አምጪልኝ"

" ምንም ችግር የለም! የሚቀመስስ?"

" ሚኪ አንተ በላህ እንዴ?"

" በላሁ ካትሪ"

ካትሪን ትንሽ ካሸለበች አልያም ከመኝታ መልስ አሪፍ ሱስ አላት:: ማንበብ!! ፀባዩዋን ስለሚያውቅ ብድግ ብላ ሽንት ቤት ደርሳ ስትመለስ ቀጥታ ቦርሳዋን ማውረድ እንደሆነ ስለሚያውቅ እሱ ቀድሞ አውርዶ ጠበቃት:: ጠረጴዛው ላይ አስቀመጠው::

" ሽንት ቤት ወጣች?" አለች ሄላሪ ድንገት ካትሪን ካሸለበችበት ነቅታ የሞቀ ወሬያቸውን ስላቋረፈደችባት ተበሳጭታባታለች...

" አ! አመጣሽላት"

" ምግብ ብትወስድም ጥሩ ነው ቅድምም በጣም ትንሽ ነው የወሰደችው" አለችው በፈገግታ አሸብርቃ::

" እንግዳውስ ካላስቸገርኩሽ ለሁለታችንም አምጭልን እሷ የምግብ ነገር አይሆንላትም! ሰው ሲበላ ስታይ ነው ፍላጎቷ የሚቀሰቀሰው"

ሄላሪ ወጣች::

ትንሽ ቆይታ ካትሪን ሰውነቷን ለማነቃቃት እየተንጠራራች መጣች:: ሚልክያስ ያደረገውን ስትመለከት " በጣም ነው የማመሰግነው ሚኪ!" አለችው::

እቅፍ አደረገችው:: ቦርሳዋን ከፍታ በSUSAN NAPIER የተፃፈውን

SECRET ADMIRER የተባለውን ሁለት አነስ አነስ ያሉ መፅሐፍትን መርጣ አወጣች:: ሁሌ መፅሐፍ ስትገዛ ሆነ ስታስገዛ ሁለት ሁለት ነው:: አንድ ለሚልክያስ ሌላውን ለራሷ:: ሚልክያስ አሁን አሁን በጣም ማንበብ ቢወድም ለማንበቢያ ግዜ ግን የለውም ፤ ቢሆንም ባለችው አነስተኛ ሰዓት ከማንበብ ወደ ኋላ ብሎ አያውቅም:: ወደደም ጠላም ግን ዘታይምስ የተባለውን ጋዜጣ ሳያነብ አያመልጠውም::

" አንድ ላንተ ... አንድ ለኔ!" አለችው አንደኛውን መፅሐፍ እየዘረጋችለት::

" አመሠግናለሁ ካትሪ! በቅድሚያ ግን መብላት አለብን"

" በላሁ አላልከም እንዴ?"

"ራበኛ!"

"ከበላህማ እኔም እበላለሁ!" ብላ መጥሪያውን ልትጫነው ስልት ሚልክያስ በፍጥነት "ታዛለች" አላት::

ከሚያምሩት አይኖቹ ውስጥ የሆነ ነገር ለማንበብ በትኩረት አይን አይኑን ተመለከተችው::

" ስለምን እያወራችሁ ነበር ግን?"

" በቀን ብዙ ሰዓት የሚያወራው ሴት ወይስ ወንድ ምናምን..."

" ይሄ ምን አዲስ ነው እንዴ? በቀን ውስጥ ማንኛዋም ሴት ወደ 16ሺ ቃላት ወይም የወንዱን ሰስት እጥፍ እንደምናወራ ፀሐይ የሞቀው ሀቅ ነው:: ጨዋታን ጨዋታ አይደለም የሚያነሳው እንደውም አንድ ያነበብኩትን ታሪክ ልንገርህ:: አንድ በጣም ቸር የሆነ ንጉስ ነበር:: ያ ንጉስ እጅግ በጣም የወሬ ልክፍት ያለባት፣ ለአንድ ሴኮንድም ዝም ማለት የማትችል ሚስት ነበረችው:: አንድ ቀን ማለዳ ተነስቶ ለዚች ወሬኛ ሚስቱ

'የኔ ፍቅር ዛሬ ከማንም ሰው ጋር ሳትነጋገሪ ከዋልሽ የአልማዝ ስጦታ እሰጥሻለሁ ይህን ማድረግ የምትችይ ይመስልሻል?'

' እንዴት የኔባል! ከማንም ጋር አላወራም አፌን እንደቀለፍኩት ባልዋል እኔ ያንተ

ሚስት አይደለሁም!' ብላ ዛተች:: እስከ እኩለ ቀን ድረስ ማንንም ላለማናገር ተደበቀች:: የምሳ ሰዓት እንዳለፈ አላስችል አላትና ከዋናው እልፍኝ ወጥታ ጓሮ በመሄድ አንድ ዛፍ ስር ተጠግታ 'አንተ ዛፍ ትሰማኛለህ ይህ ሚስኪን ባሌ አልማዝ ሊሸልመኝ እኮ ነው! ይህ ግማታም ባሌ እኔ ወሬኛ እመስለዋለሁ! ሊፈትነኝ ፈልጎ እኮ ነው እኔ እስከምመጣ ድረስ ካላወራሽ የሚለኝ አይገርምህም' እያለች ውስጧ ያመቀችውን ሁሉ ለዛፉ ነገረችው:: ተመልሳ ቤት ገባች:: እነሆ ምሽት ላይ ባለቤቷ መጣ አቅፎ ሳማት... ልክ እንደተቀመጠ

'የኔ ውድ ባል በል ሽልማቴን ስጠኝ ከማንም ሰው ጋር አላወራሁም አፌ እንደተከረቸመ ነው የዋልኩት' አለችው:: ልክ ይህን ተናግራ እንደጨረሰች ከግቢው ውስጥ 'አንተ ዛፍ ትሰማኛለህ ይህ ሚስኪን ባሌ አልማዝ ...' የሚል ታላቅ ድምፅ ተሰማ::

'አይ ሚስኪኗ ሚስቴ ወሬ ከአልማዝ በለጠብሽ?'ሲል አላገጠባት ይባላል:: ይልቅ አታረሳሳ ምን አወራችሁ?"

ጥያቄውን ሳይመልስ የታዘዘችውን በጠረጴዛ እየገፋች ሄላሪ መጣች:: አስቀምጣ ወጣች:: መብላት ጀመሩ:: እየበሉም ቀና ብላ በትኩረት ተመለከተችው::

" ምን አወራችሁ ግን?" አለችው ለሶስተኛ ጊዜ::

" የሆቴላችን ደንበኛ ነች... ስለ ሆቴሉ አወራን ስለ ራሷም በመጠኑ ነገረችኝ"

" እኔ ደግሞ ድንግል ነኝ ድንግልናዬን ላስረክብሽ ያልካት መሰሎኝ" ብላ ፈገግ አለች::

" አ! እሱንም አውርተናል!" ተሳሳቁ:: በልተው ሲጨርሱ ሄላሪ የተበላበትን ዕቃ ይዛ ወጣች:: ማንበብ ጀምረው ብዙም ሳይቆዩ ካትሪን ድንገት ተነስታ አነስ ያለችውን ሻንጣ አወጣች:: 8569ሺ ዶላር የገዛችውን አነስተኛ ነገር ግን እጅግ በጣም ዘመናዊ ልዩ ብቃት ያላትን የዘመኑን የሳይንስ እና ቴክኖሎጂ እድገት የምታሳይ በቀን ሆነ በጨለማ መቅረፅ የምትችል ከድምፅ ሆነ ከምስል ጥራት እነ 7D Cameraን የምታስንቅ Video camera አወጣች::

" ስታነብ መቅረፅ እፈልጋለሁ ፈገግ በል

… ማንበብ ትወዳለህ ሚስተር ሚልክያስ?"

* * *

" ጥሩ .. አንቺ ደግሞ አንብቢ እኔ ልቅረፅሽ" ለሁለት ደቂቃዎች ያህል እሷንም የአውሮፕላኑን ክፍሉንም ለማስታወሻነት ከቀረፀ በኋላ ካሜራዋን አጥፍቶ አስቀመጣት:: ሁለቱም ንባባቸውን ቀጠሉ:: በደመናዎች ውስጥ አውሮፕላኑ ጉዞውን ቀጥሏል..

* * *

ሄላሪ ለስንተኛ ጊዜ እንደተመላለሰች ባታስታውሰውም ሁለቱም ሳያስቡት እያነበቡ እንቅልፍ እንዳሸለባቸው ነው:: እስከ ዛሬ እንደካትሪን እና ሚልክያስ ያለ ፀባየኛ መንገደኞች አላጋጠማትም:: ከአውሮፕላኑ ምቾች የተነሳ ይሁን ባላወቀችው ምክኒያት ሁለቱም ተኝተዋል:: በአውሮፕላን ጉዞ መንገደኞች ቢተኙ ደግሞ ለእነ ሄላሪ በጣም ተመራጭ ነው:: የኢትዮጵያን መሬት ሊነኩ የቀራቸው 20 ደቂቃ እንደሆነ እንኳ የሚያውቁ አይመስልም፤ እናም ቀስ ብላ ወደሚልክያስ ሄደች::

በልስላሴም ሆነ በውበት ከራሷ እጅ የማይተናነሰውን እጁን ይዛ አሸት አሸት አደረገችው:: መርፌ እንደወጉት ወዲያው ባነነ:: አይኑን ሲገልጥ ውቧ ሄላሪ በታላቅ ፈገግታ ተሞልታ ቆማለች:: ምክኒያቱን ባያውቀውም ልቡ ለሁለት ስንጥቅ አለች:: እንዲህ ያለ መደንገጥ ከዚህ በፊት አጋጥሞት አያውቅም::

"ም... ነው ሄላሪ" አላት ድንጋጤውን ለመደበቅ እየጣረ::

" ኢትዮጵያ ከ20 ደቂቃ በኋላ እንደርሳለን" ኢትዮጵያ የሚለውን ቃል ሲሰማ ሳያስበው በደስታ ተስፈንጥሮ ተነሳ:: ሄላሪ እንዳለችው ከሀያ ደቂቃ በኋላ አዲስ አበባ ቦሌ ኢንተርናሽናል አውሮፕላን ተርሚናል ደረሱ:: የአውሮፕላኑ ጎማ መሬት ረገጠ:: የስምንት ሰዓት ከሀያ አንድ ደቂቃ የፈጀው ጉዞ አሰልችቶዋቸው መሬት ቶሎ መርገጥ የናፈቃቸው መንገደኞች በፍጥነት መውረድ ጀመሩ:: በግርግሩ መሀከል ሄላሪ መጣች::

"መልካም ጊዜ ይሁንላችሁ"

" በጣም ነው የምናመሰግነው ላንቺም መልካም ጊዜ ይሁንልሽ"

ካትሪን በቪዲዮ ካሜራዋ ትዝታ እያስቀረች ነው:: ሄላሪ ምን አይነት መግነጢሳዊ ሀይል እንደገፈተራት ባታውቀውም ጥምጥም ብላበት አቀፈችው::

"ስትመለስ አደውልልሀና እንገናኛለን! ተጠንቀቅ! መልካም ጊዜ!" ብላው ካትሪንንም ጨብጣ ተሰወረች:: የውስጠኛውን ክፍል ጨርሰው እንደወጡ ሙሉ ጥቁር ሱፍ የለበሰ ስማይን ሊነካ ትንሽ የቀረው ቀልጣፋ ሹፌር ደረቱ ላይ በኢንግሊዝኛ ቋንቋ "እንኳን በሠላም መጣችሁ ሚልከያስ እና ካትሪን" የሚል ስማቸውን ፅፎ ቆሟል፤ እነሱም ስማቸውን ሲያነቡ ወደሱው አመሩ::

" የፈጣሪ ያለህ! እንዴት አይነት ረጅም ሰው ነው" አለች ካትሪን ተገርማ:: በሕይወት ዘመኑዋ እንዲህ ያለ ረጅም ሰው እስከ ዛሬ በፍፁም አላየችም:: በውስጧ ሳቀች::

"Nice to meet you..."

" Nice to meet you.."

ከተባባሉ በኋላ የሸራተን ሆቴል ንብረት በሆነችው ዘመናዊ መርቸዲስ መኪና ውስጥ አስገባቸው:: ሚልከያስ እና ካትሪን ተመቻችተው ተቀመጡ::

" ጉዞ እንዴት ነበር ጌታዬ" አላቸው በመስታወቱ ውስጥ እየተመለከታቸው... መኪናዋን እያስነሳት::

"አስደሳች ነበር" አሉት ሁለቱም በአንድነት የተማከሩ ይመስል:-

* * *

ዘመናዊዋ መርቸዲስ መኪና ጉዞዋን ጀመረች:: ከመኪናዋ ውስጥ የታላቁ የምንግዜም የኢትዮጵያ ሙዚቃ ንጉስ የሆነው የጥላሁን ገሰሰ ሙዚቃ እየተንቆረቆረ ነው::

ፍቅር ከኛ እንዳይለየን እንዲቃናልን ስራችን
መጨቃጨቅ ይወገድና ሠላምይሁን ለሁላችን
ኑሮ ለሰው ልጆች በእውነት ቀላል ስላልሆነች ዋዛ
በሆነው ባልሆነው ይቅር ጭቅጭቃችን አይብዛ
ገንዘብ ፍቅር ከሌለበት የማይጠቅም ከንቱ ነው
ለጊዜው ያስደስት እንጂ ሲረግፍ እንደ ጤዛ ነው::

# 5

# ኢትዮጵያ

## አዲስ አበባ

## 1998

# 5

# ቀን ሶስት...

ሁለቱም ወደውታል:: ያለፉትን ሁለት ቀናት አዲስ አበባ እስከምትበቃቸው ተዘዋወሩ፤ በተለይ አዲስ አበባ ሙዚየምን፣ ብሔራዊ ሙዚየምን ፣ እንጦጦን፣ መርካቶን ፣ በኢትዮጵያ የፈረንሳይ ኢንባሲን እና ከፈረንሳይ ጋር ግንኙነት ያላቸውን የተመረጡ በታዎችን... በሚገባ ተመለከቱ::

ሚልከያስ ሰዓቱን ሲመለከት ከጠዋቱ 3:30 ደቂቃ ይላል:: ከአልጋው ላይ በፍጥነት ወረደ:: ፍለጋውን ዛሬ መጀመር እንዳለበት ወስኗል::

ተኝታ መቆየት የማትወደው ካትሪንም ተነስታ ልብስ እየቀያየረች የራሷንም ምስል በረጅሙ የቁመት ማሳያ መስታወት እያየች ትዘናናለች:: ድንገት ወደ ሚልከያስ ክፍል ዘው ብላ ገባችና "ቆይ እዛው እንዳትነሳ" አለችው:: ባለበት ተቀምጦ ቆያት::

"ልብሴ ያምራል?"

" ጥሩ ነው"

ሌላ ቀይራ መጣች::

"ይሄስ?"

"በጣም ጥሩ ነው!"

ደሞ ሌላ ቀይራ መጣች::

" ይሄስ?"

"ምርጥ ነው!"

ራቁቷን በውስጥ ልብስ /ፓንት/ እና ጡት ማስያዣ ብቻ መጣች::

"ይሄስ?"

"አንቺ ዱሪዬ..."

"እህ ያምራል አያምርም?"

" አያምርም?"

" አያምርም!? ያምራል እስከምትል አለብስም" ግትር ብላ ቆመች:: አሳቀችው::

"እሺ ካትሪ በጣም ያምራል"

"ትክክል! በዚያ ላይ እንኳን የኔን አይነቷን ውብ ቀርቶ ማንኛዋም መልከጥፉ እያላችሁ የምትጠሯት ሴት ራሷ ራቁቷን ውብ ናት! አታስጠላም ገባህ?" ብላው በቁንጠኛ ሁኔታ ሄደች:: ልብስ ለብሳ ተመለሰች:: ጠረጴዛው ላይ የነበረውን ታሪካዊ የህብረት ፎቶ ግራፍ አነሳችና ተመለከተችው::

" ፍለጋችንን ከማን ነው የምንጀምረው?" ፎቶውን በቀስታ ተቀበላትና ተመለከተ:: ከግራ መጀመሪያ የተቀመጠው መኑ ስለ ነበር

" ከዚህ እንጀምራለን መኑ ይባላል" አላት::

" ነጋዴ ለመሆን የተመኘው?"

ካትሪን አንዴ የተነገራትን ነገር ልብ በማለት ስለምትሰማ በጣም ነው የምታስታውሰው:: በዚህ ፀባዩዋ የማያደንቃት አባቷ ብቻ ነው:: 'ሁሉንም ማስታወስ ልጄ ጥሩ አይደለም! አለማስታወስ! መርሳት! ራሱን የቻለ ፀጋ ነው! በህይወትሽ ላይ የሚፈጠሩትን መልካም ሆኑ አሉታዊ ነገሮች ሁሉ ማስታወስ የለብሽም! ሁሉንም ነገር ማስታወስ ራሱ ትልቅ በሽታ ሊሆን ይችላል' ይላታል::

" በቃ እኔ ቪዲዮ ካሜራዋን ቻርጅ ልሙላ አንተ ቀለል እንዲልህ ሰውነትህን ተለቃለቅ... ልብስ ቀይርና እንውጣ"

ካትሪን ያለችው ሁሉ ልክ ስለ ነበር ተነሳ:: ሰውነቱን ተለቃለቀ:: ልብስ ቀይሮ ተመለሰ::

" ዋው አብርተሃል!!"

" ሜርሲ ካትሪ... አመሠግናለሁ"

እያወሩ ከመኝታ ክፍላቸው ወጡ:: የተመደበላቸው ሹፌር ቀልጠፍ ብሎ መጣና

"እንደምን አደሩ ጌታዬ" አለ እጅ እየነሳ:: በደንብ እንዲከባከባቸው በጥብቅ ነው የተነገረው:: ሆቴሉ ውስጥ ካሉት ምርጥ ሹፌሮች አንዱ እሱ ነው:: ኢትዮጵያን በመወከል ኢጣሊያ ድረስ በሚሄድ ከፍተኛ ልምድ ካላቸው ተወዳዳሪዎች ጋር ከፍተኛ ትግል በማድረግ በመኪና እሽቅድድም ሁለቴ ወርቅ እንዳገኘ ይነገርለታል::

" እንደምን አደርክ ይዲድያ" አለው ሚልክያስ የነገረውን ስም እያስታወሰ:: ይዲድያ በእግዚአብሔር የተወደደ የሚል ፍቺ አለው:: የሚደንቀው ስሙን አስተካክለው የሚጠሩት ከአስር ሰዎች አንዱ ብቻ ነው:: አሁን ሚልክያስም በትክክል ስለጠራው ደስ አለው::

"እግዜር ይመስገን የት ልውሰዳችሁ ጌታዬ?"

"እህ... በሚገባ አላስታውስም ብቻ በፊት ቀበና የሚባል ስያሜ ነበረው ቀጎስ ወይም ቀዳማዊ ኃይለስላሴ ትምህርት ቤት ፊት ለፊት መሆኑ ትዝ ይለኛል"

" ምንም ችግር የለም አውቀዋለሁ ጌታዬ"

" መልካም እንግዳውስ እዛ ስፍራ ውሰደን ካላስቸገርኩህ ደግሞ ጌታዬ የምትለዋን ቃል ባትጠቀም ደስ ይለኛል"

" ምንም ችግር የለም!!" አለ ይዲድያ:: መኪናዋ ሽራተንን ለቃ ወጣች::

# 6

የቀበና ነዋሪዎች ሁሉ መኑ ታምራትን ያውቁታል:: መኑ ታምራት ማነው? ቢባሉ... ሁሉም የሸመደዱ ይመስል መልሳቸው አንድ ነው::

"አ! ከዓመታት በፊት እሱም ቤተሰቡም በድሎት የሚኖሩ በጣም ጎበዝ ነጋዴ ነበር፤በጣም ታታሪ ሰራተኛ ነበር፤ ግን በማይታወቅ እሳት አደጋ ፋብሪካው ተቃጥሎበት አሁን እናቱ እንጀራ በመሸጥ የሚተዳደሩ እሱ ሊስትሮ የሚሠራ ከዓመታት በፊት ከሰው በላይ የነበረ አሁን ከሰው እግር ስር የሚውል ወጣት ነው" ይላሉ:: ይህ ደግሞ ፀሐይ የሞቀው ትልቅ እውነታ ነው::

እማማ አለምነሽ በጭስ ከመጥቆሩ የተነሳ ለማየት ከሚያስፈራው ማድቤት እንጀራቸውን መጋገር ጨርሰው ወደ ዋናው ቤት እያመሩ ሳለ የጎረቤት ልጃቸው አየሮጠች መጣች:: በር ላይ ተቀምጣ ከጓደኛዋ ጋር ሰኞ ማክሰኞ ... እየተጫወተች ነበር:: በሕይወቷም ሆነ በሰፈራቸው አይታ የማታውቀው መርቸዲስ መኪና መጥታ የቆመችው::

"ሚሚ... ሚሚ... ነይ እስቲ" አላት ይዲድያ:: ሁለቱም ጨዋታቸውን ትተው አየሮጡ ወደ መርቸዲስዋ መጡ::

" አቤት... አቤት..." አሉ መኪናዋ ውስጥ ሁለት ፈረንጆችን ሲያዩ ብር እንደሚያገኙ ተማምነው:: ብር ሸተታቸው

" የእነ መኑ ቤት የቱ ነው?"

" ይኸው ... ይኸው ..."

የአዲስ አበባ የመኪና ጭልፊቶችን ስለሚያውቅ ይዲድያ መኪናው ውስጥ ለመቀመጥ ወስኖ ተቀመጠ:: ካትሪን ቪዲዮ ካሜራዋን ይዛ ወረደች:: እንደ ሚልክያስ ሁሉ እሷም መኑን እስከምታየው ቸኩላለች:: ከሁለቱ ተለቅ የምትለዋ እና ቁርጥ ዝንጀሮ የመሰለችው ፈልፈላ ቀድማ ደርሳ ስለ ነበር" እማማ... እማማ... አለም ፈረንጅ ... ፈረንጅ..." አለቻቸው:: የምታየውን ባለማመን ካትሪን ትቀርፃለች:: በሕይወቷ እንዲህ የጨረጨሰ ቤት አይታ ስለማታውቅ ደንቆዋታል:: እሷ ድህነትን ሳይሆን ቃሉን ራሱ አታውቀውም! በእርግጥ ከዚያች ውብ የዓለማችን ከተማ ፓሪስ ! ከዚያች መንገዶቿ ጠዋት ከሚታጠቡላት የፍቅር ውብ ከተማ የኖረች ለዚያውም የቢሊየነር ልጅ የሆነች የድህነት ህይወትን አይታ ባትገረም ነው የሚያስደንቀው::

እማማ አለምነሽ ግራ ገብቶዋቸው ዝም ብለው ይመለከታሉ:: ሚልክያስ እንባው ስለመጣ በዝምታ ሄዶ እቅፍ ሊያደርጋቸው ሲል እሳቸው ደግሞ የሚያምረው ውድ ልብሱ እንዳይቆሸሽ ሸሸት አሉት::

" እማማ አለምነሽ አይፍሩኝ ልጅዎት እኮ ነኝ"

ግራ እንደገባቸው ሲመለከት ከኪሱ ውስጥ የነበረውን ፎቶ አወጣና ሰጣቸው:: እየተንቀጠቀጡ ተቀበሉት:: በደንብ አዩት:: ግን ምንም አልተናገሩም::

" እማማ... ሚልክያስ ነኝ... አቡሻ ነበር እያሉ የሚጠሩኝ የመኑ ጓደኛ ... እዚህ ፎቶ ላይ ያለሁት ነኝ አላስታወሱኝም"

" እናቴ ማርያም!!"

የሚያወሩት ስለማይገባት ካትሪን ዝም ብላ ትቀርፃለች:: ጥምጥም አሉበት:: እያገላበጡ ሳሙት:: ቤት ውስጥ ገብተው ተቀመጡ::

* * *

" ሁሌ ያንተን ስም ያነሳል ፤ በእርግጠኝነት አንድ ቀን ይመጣል ይለኝ ነበር:: ወደ ዩኒቨርሲቲ ሳይገባ ሲቀር እና የመስሪያ ቤት ስራ ሲያጣ ስራ ሳይንቅ ሊስትሮነት ጀመረ:: በሊስትሮነት እየታተረ ጠዋት እና ማታ እየሰራ ብር አጠራቀመ፤ በዚያ ላይ እኔም እንቁላል

አቀቅልለትና እሱ ማታ ማታ በየቡና ቤቱ በራፍ ላይ እያዞረ ይሸጣል! በጭራሽ ደከመኝ የማይል ሰው ነው፡፡ እግዚ.ሐብሔር ይመስገንና ከብዙ ዓመት ጥረት በኋላ ብዙ ብር ተጠራቀመ! በብሩ ሕይወታችንን ለመለወጥ ከአንድ ሰው ጋር ወደ ዱባይ አገር ሄደ፡፡ ተመልሶ የራሱን አነስተኛ ድርጅት ከፈተ... ከዚያ ባልታወቀ ምክኒያት ድርጅቱ በእሳት ተቃጠለ፡፡ መልሶ ለመቋቋም የገንዘብ እርዳታ የሚሰጠው አጣ፡፡ ከባንክ ለመበደር ምክሮ የሚያሲዘው ነገር ስላጣ ተከለከለ፡፡ ይህን ቤት እንዳያሲዘው የቀበሌ ቤት ነው፡፡ ችግር ሲመጣ ተደራርቦ ነው ደስታም ሲመጣ ተደራርቦ ነው ሕይወቱ በሀዘን ተሞላ... ሁሉ ነገር ጠመመበት፡፡ ሁልጊዜ ቀደም ሲል የነበረውን ሕይወቱን እያስታወሰ ይበሳጫል! በዚህ ግራ መጋባት መሀከል እያለ ምርጫ 97 መጣ፡፡ ከጠዋት እስከ ማታ ወሬው ሁሉ ስለ ምርጫው ሆነ

'እማ አይዞሽ በቅርብ ጊዜ ሕይወታችን ይለወጣል! እንደ ቀድሞው ሳይሆን ከዚያ የበለጠ ጥሩ ሕይወት እንኖራለን አዲስ አበባ ላይ ፍትህ የለም! ነፃነት የለም! ሁሉም ሰው እኩል አይደለም! አዲስ አበባ ከግራ ቀኝ ተወጥራለች! አይዞሽ እማማ ቅንጅት በምርጫው ሲያሸንፍ ሁሉ ነገር መልካም ይሆናል! አዲስ አበባ ሳትሆን ኢትዮጵያ በስልጣኔ ትገሰግሳለች' ይለኛል፡፡ ስለ ቅንጅቶች ብዙ ይነግረኛል፡፡ ቅንጅትን ምረጡ እያለ ወረቀት ይለጥፋል! ይቀሰቅሳል!... አንዳንዴ በማለዳ ቁርሱን ሳይበላ ወጥቶ ከምሽቱ አምስት ሠዓት ላይ ይመጣል፡፡ በጣም ተለወጠብኝ! እንዲህ ሆኖ አይቼው ስለማላውቅ ፈራሁ! ልቤ በፍርሀት ተሞላ፡፡ አንድ ምሽት ሲብስብኝ

' ልጄ ላናግርህ እፈልጋለሁ' አልኩት

'አዳምጥሻለሁ እማ '

' ሰሞኑን ቁርስ ሆነ ምሳ መብላት ትተሃል?'

'እማ ቁርስ ሆነ ምሳ ይደርሳል! አሁን እኔን የራበኝ ምግብ ሳይሆን ነፃነት ነው ዶ/ር ብርሃኑ ነጋ ያለውን አልሰማሽም እውነተኛ ምግብ የአዕምሮ ነፃነት ነው፡፡ ነፃነት ከሌለበት ምርጥ ክትፎ ነፃነት ያለበት ቂጣ ይሻላል ብሏል! ትክክል እኮ ነው፡፡ እማ አሁን ለዘመናት ሲጫወትብን የነበረው ኢህአዴግ ወደ መቃብር የሚሄድበት ጊዜው እየቀረበ ነው! እማ ሙች

በእርግጠኝነት ቅንጅት በምርጫው ያሸንፋል! አሁን መላው የአዲስ አበባ ነዋሪ የኢህአዴግን ሴራ! ደባ! መሰሪነትን አውቋል:: ኢህአዴግ አገልግሎት የሚሠጠው ለኢትዮጵያ ህዝቦች ሳይሆን ለተወሰኑ ግለሰቦች ነው:: ኢህአዴግ የኢትዮጵያን ህዝብ በአንድነት ሳይሆን በዘር፣ በቋንቋ፣ በብሔር... እየከፋፈለ እየሰነጣጠቀ አንዱን ካንዱ እያምታታ ቁርሾ እየዘራ ባጠቃላይ ኢትዮጵያዊ አንድነታችንን ለመጠበቅ ሳይሆን የተወሰኑ ግለሰቦችን ለመጥቀም ብቻ የተመሰረተ ድርጅት ነው:: በዚያ ላይ አስተሳሰባቸው ሁሉ የጫካ ነው:: ቅንጅት ውስጥ ያሉት ሁሉ እኮ የምሁራን ስብስብ ናቸው:: ኢንጂነር ግዛቸው ሽፈራው... ዶ/ር አድማሱ አያሌው... ዶ/ር ኃይሉ አርአያ... ፐ/ር መስፍን ወ/ማርያም ... ዶ/ር ብርሃኑ ነጋ... ዶ/ር በፈቃዱ ደግፌ ... ዶ/ር ሺመልስ ተ/ፃዲቅ ... አቶ ልደቱ አያሌው ... ወ/ሮ ለኔሲል አስፋው ... የመሰሉ በርካታ ምሁራንን ያቀፈ ነው! እማማ ሙች ነው የምለው እነዚህ ምሁራን ታላቅ ለውጥ ያመጣሉ! ወያኔ በቂጡ መሬት ላይ ዘጭ የሚልበት ጊዜው አሁን ነው:: የአዲስ አበባ ህዝብ በምግብም! በአህምሮም ነፃ የሚሆንበት ቀኑ ቅርብ ነው! ኢትዮጵያን ለዘመናት የገዛው እና ለውጥ ያላመጣው ውሸታሙ አስመሳዩ ሁሉን ነገር ለፖለቲካ ፍጆታ ብቻ የሚያውለው የኢትዮጵያ ህዝብ ዶሮ ነው ዶሮን በረጅም ገመድ ሲያስሩዋት የፈቷት ይመስላታል! የኢትዮጵያ ህዝብ ውሻ ነው ውሻው ይጮሀል ግመሉ ይሄዳል እያሉ የሚያፌዙብን ወያኔዎች መቃብራቸው ደርሷል! ስለዚህ ቅንጅት እንዲያሸንፍ ከጠዋት እስከ ማታ ወረቀት መለጠፍ፣ የወያኔን ሴራ መጋለጥ ፣ ህዝቡን መቀስቀስ አለብኝ! ስለዚህ እማ አትፍሪ! ለኔ አታስቢ ምንም አልሆንም! ደግሞ አንቺ ራስሽ ነፃነት እና ፍትህን ቤት ውስጥ ተቀምጠን አይመጣም ትይኝ አልነበረም እንዴ?'

'ብያለሁ'

'እና እያደረኩ ያለሁት ልክ አይደለም?' ዝም አልኩት:: ሩጫውን ቀጠለ... በተለይ ምርጫው ሊከናወን ሁለት ሳምንት ሲቀር ቤት መምጣት ሁሉ ተወ... ምርጫው ግንቦት ሰባት ላይ ተከናወነ :: ልጄ ሲናገር እንደነበረው የአዲስ አበባ ነዋሪ ኢህአዴግን አፈረጠው:: ኢህአዴግ ዜሮ ድምፅ አገኘ! ቅንጅት በታላቅ ዝረራ አሸነፈ! የአዲስ አበባ ህዝብ ለኢህአዴግ

ያለውን ታላቅ ጥላቻ አሳየ... ውጤቱ የተነገረ ማታ ልጇ በደስታ ሲያለቅስ አደረ... ታዲያ በመሀከል ከምርጫው ውጤት በኋላ በተፈጠረው ግርግር ልቡ ተሰበረ! ከማንም ሰው ጋር ማውራቱን ተወ ... በታላቅ ዝምታ ተዋጠ... ቀድሞ ሲሰራው ወደ ነበረው የሊስትሮነት ሥራው ተመለሰ፡፡ ልቡ ግን አሁንም እንደተሰበረ ነው፡፡ በዚያ ላይ አብሮት ቅንጅትን ምረጡ እያለ ሲቀሰቅስ የነበረው ጓደኛው ቅንጅት በጠራው የተቃውሞ ሰልፍ ላይ ከአጠገቡ መሀከል ግንባሩ ላይ በጥይት ተመቶ ሲሞት ስላየም ልቡ ውስጥ ሀዘን ገባ! ቅስሙ ተሰበረ፡፡ ሚያዚያ 28 ምሽት ሁለት ሰዓት አንዲት መኪና መጥታ በራችን ላይ ቆመች፡፡ አራት ሰዎች ወረዱ፡፡ ቤቱ ተፈተሸ፡፡ ምንም ነገር ሲያጡ አይኔ እያየ 'እኛ ጫካ ለ17 ዓመታት ታግለን ያመጣነውን ስልጣን አንተ አዲስ አበባ ጎዳና ላይ ወረቀት በመለጠፍ ብቻ ስልጣን ለመያዝ ትሞክራለህ' እያሉ መሬት ላይ ጥለው እያንከባለሉት እንደ ውሻ ቀጠቀጡት! በነጋታው ፖሊስ ጣቢያ ሄጄ የሆነውን ጉዳይ አመለከትኩ፡፡ ዋና መርማሪው እየሣቀ 'አላርፍ ያለች ጣት ትቆረጣለች ብለን ነበር እዚህ የመጣሽው ለምን ጣቱን አልቆረጣችሁትም ከሆነ እንቆርጥልሻለን' ሲል አፌዘብኝ፡፡ እውነተኛ ፍትህ የእግዜር ነው! እምዬ ማርያም የስራችሁት ትስጣችሁ ብዬ ወደ ቤቴ ተመለስኩ ... ብቻ ልጄ የድሮው መኑ አይደለም፡፡ እርግጠኛ ነኝ አንተን ሲመለከት ደስ ይለዋል፡፡ እንደው የኔ ልጅ እባክህ አንተም በጨዋታ አድርገህ ራሱን እንዲያረጋጋ ንገርልኝ! እባክህ የቀድሞ የልጄን ፈገግታ መልስልኝ" አሉትና አይናቸው ላይ ያቀረረውን እንባ በነጠላቸው ጫፍ ጠረጉት፡፡ ሁሉንም ነገር ነገሩት፡፡ በጣም የደነቀው ቤታቸው ግርግዳ ላይ እሱ የያዛት ፎቶ ተመሳሳይ ተሰቅላ ማየቱ ነው፡፡ ሚልኪያስ ስለ ጓደኛው መኑ በሰማው ታሪክ በጣም ልቡ በሀዘን ተነካ፡፡

" አሁን የት ነው የሚሠራው እማማ ?"

" ዘሪሁን ህንፃ አካባቢ ነው"

" ዘሪሁን ሕንፃ" ብሎ ማስታወሻ ደብተሩ ላይ አሰፈረና ነገ እንደሚመጣ ተናግሮ ወጣ፡፡ ለህፃናቱ እንዳሰቡት መቶ መቶ ብር አስጨበጣቸው፡፡ በሩጫ ተሰወሩ!

" ወደ ዘሪሁን ሕንፃ ውሰደን" አለው መኪናው ውስጥ ገብቶ እንደተቀመጠ፡፡

ይዲዲያ መኪናውን አስነሳ:: ሚልክያስ ስለ ጓደኛው መኑ ከእናቱ የተነገረውን ታሪክ ለካትሪን ይነግራት ጀመር::

* * *

በውራኤል እና በሀያ ሁለት ማዞሪያ መሀከል በሚገኘው ዘሪሁን ሕንፃ ፊት ለፊት የውሃ ልማት ድርጅት አጥር ስራ ካሉት ሊስትሮዎች ሁሉ በእድሜ ትልቁ መኑ ነው:: በቦታው ያሉት ሊስትሮዎች ስለ መኑ የሚያውቁት ነገር ቢኖር በቃ... እንደነሱው ሊስትሮ እንደሆነ ብቻ ነው:: ስሙን ግን መኑ እያሉ ሳይሆን በቦታው ካሉት ሊስትሮዎች ኢንግሊዝኛ ተናጋሪው እሱ ብቻ ስለሆነ "ፈረንጁ ሊስትሮ" እያሉ ይጠሩታል:: መጥራት ብቻ አይደለም ኢንግሊዝኛ ስለሚችልም በጣም ያከብሩታል:: በአሁኑ ደቂቃ ሁሉም ስራ ስለሌለ ተቀምጠው ወሬ እየፈተፈቱ ነው:: መርቸዲሷ መጥታ ስትቆም ሁሉም ተነሱ::

ከመኪናዋ ካትሪን ቪዲዮ ካሜራዋን ይዛ ወረደች:: ሚልክያስም ወረደ::

" ፊልም ቀረፃ አለ ማለት ነው:: ይህን አክተር የሆነ ፊልም ላይ አውቀዋለሁ" አለ ሽልንጌ የሚሉት::

" እና ሊቀርፁን ነው እኛንም" አለ ሴንቾቶ የሚሉት::

" ምን ጨነቀን ብር ይለቁልናል"

ፓርኪንግ ተቆጣጣሪዋ በፍጥነት መጥታ ወረቀት ለጠፈች:: ሚልክያስም ፍፁም ፊቱ በደስታ በርቶ ወደ ጓደኛው ተጠጋ:: መኑ ጫማውን ተመለከተ:: ከደቂቃ በፊት ከፋብሪካ እንደወጣ ጫማው ያበራል! ስለዚህ ፊልም እየተቀረፀ ስለሆነ ፈገግ እያለ ተነሳ:: ሚልክያስ ለሠላምታ እጁን ዘረጋ...

መኑ ራሱን ነቀነቀ::

" My Hand is dirty sir" ሲል በኢንግሊዘኛ ተናገረ::

"አማርኛ እችላለሁ ይሁን ጨብጠኝ" አለው:: ሚልክያስ በፍጹም ትህትና በተሞላበት አነጋገር:: ምን አገባኝ አለና ጨበጠው:: ሚልክያስ ሳይናገር ወንበሩ ላይ ተቀመጠ::

"መኑ ታምራት ነው ስምህ?"

"አዎ ጌታዬ"

" የልጅነት ሕልምህ ምን ነበር?"

ዝም አለ:: ስለ አለፈ ሕይወቱ ማንም እንዲያዋራው በጭራሽ አይፈልግም:: የትላንቱ ሙኑ ከነታሪኩ ተቀብሯል:: አለቀ:: ዛሬ ሌላ ቀን ነው::

"ግዴለም !... ግን ነጋዴ ለመሆን ትመኝ ነበር?"

ሙኑ የተናገረው ነገር የለም፤ ዝም!

" አንድ ጥያቄ ልጠይቅህና ከመለስክ 100 ብር እሰጥሀለሁ"

" ኧረ ጌታዬ የፈለጉትን ጥያቄ እኔን ይጠይቁኝ! ጌታዬ የፈለጉትን ለመመለስ እችላለሁ" አለ መቶ ብሩን አይቶ የደነበረው ሽልንጌ ዘሎ በመምጣት ከሚልክያስ ፊት ላይ ቆሞ:: "ጌታዬ መቶ ብሩን ከሰጡኝ ልብስህን አውልቀህ ራቁትህን ራሱ ቁም ብባል እቆማለሁ! እውነቴን ነው! ጌታዬ መቶ ብር ማለት እኮ ቢያንስ የአምስት ቀናት አጠቃላይ ገቢ እኮ ነው"

ሚልክያስ ሳቀና ትኩር ብሎ ተመለከተው ::

" እንኳ ይዘህ ሂድ!" አለውና ብሩን ሰጠው:: ሌላ መቶ ብር አወጣ:: ያዘ::

" ቀላል ጥያቄ ነው ጓደኛ ማለት ምን ማለት ነው?"

" ጓ...ደ...ኛ" ብሎ ካሰበ በኋላ ተናገረ::

" ጓደኛ ማለት ደካማ ጎኔን የሚነግረኝ ስሳሳት የሚያርመኝ ስቸገር የሚረዳኝ ሰው ማለት ነው" ያለ ምንም ማዛነፍ ከአስራ ስድስት ዓመት በፊት የተናገረውን ነበር ሙኑ ታምራት የደገመው:: ሚልክያስ መቶ ብሩን ሰጠው:: ሌላ መቶ ብር አወጣ::

" የመጨረሻ ጥያቄ! መሙሚማታ ማለት ምን ማለት ነው?"

" ምን አሉ ጌታዬ" አለ ሙኑ በጣም ተገርሞ ጫማ የሚያስጠርገውን ግለሰብ እየተመለከተ::

" መሙሚማታ" ደገመለት::

" መሙሚማታ?" አለ ሙኑ በዝቅተኛ ድምፅ:: ምንም ሳይናገር እንባው ዝርግፍ

ብሎ ተንበርክኮ ሲጠርግበት ከነበረበት ኩርሲ ወንበር ላይ ዘሎ በፍጥነት በመሳሳት ተጠመጠመበት:: ሁሉም በግርምት መመልከት ገቡ:: ካትሪን እየተገረመች ትቀርፃለች:: መ በጭራሽ ያላሰበው ነገር ስለ ነበር ስቅስቅ ብሎ አለቀሰ:: ማመን አቃተው:: አስራ ስድስት ዓመት ማለት እኮ ትላንት ማለት አይደለም:: አስራ ስድስት ዓመት ማለት እኮ 5840 ቀናት ማለት ነው፣ አስራ ስድስት ዓመት ማለት እኮ 1401600 ሰዓታት ማለት ነው፣ አስራ ስድስት ዓመት ማለት እኮ 8409600 ደቂቃዎች ማለት ነው...504576000 ሴኮንዶች ማለት ነው... በአስራ ስድስት ዓመታት ውስጥ እኮ ሁለት ሺ ዘጠኝ መቶ ሀያ ቀናት እና ሁለት ሺ ዘጠኝ መቶ ሀያ ሌሊቶች አልፈዋል!... ስንቶች ተወልደው ስንቶች እኮ ሞተዋል!

... መኑ የሚያየውን ማመን ስላቃተው አይን አይኑን እየተመለከተ ስቅስቅ አለ ... ስቅስቅ ብሎ አለቀሰ...

ውብ ካትሪን ትቀርፃለች...

# 7

# ቀን አምስት

" እስከ አስራ ዘጠኝ ሰማኒያ ዘጠኝ ድረስ ጓደኝነታችን ቀጥሎ ነበር። ከሰማኒያ ዘጠኝ በኋላ ግን ተለያየን"

" ምክንያቱ ምን ነበር?"

" ማትሪክ ተፈትነን እኔና ማርያማዊት ፍፁም በማንጠብቀው ሁኔታ ወደቅን ሙሉጌታ አለፈ"

" ወደቅን .... እንዴት?"

" እስከ ዛሬ የሚገርመኝ ይሄው ነው! ማትሪክ እድል ነው የሚባለው ተራ አባባል እና የሰነፍ ተማሪ ንግግር ይመስለኝ ነበር ግን እውነት ነው"

" የሚደንቅ ነው ከዚያስ?"

" በቃ ሙሉጌታ ለዩኒቨርሲቲ ትምህርት ወደ አዋሳ አመራ እኔም ሌት ተቀን ሠርቼ ብር አጠራቅሜ በአንድ ነጋዴ ከፍተኛ ትብብር አማካኝነት ለንግድ ወደ ዱባይ አመራሁ። ከሁለት ዓመት በኋላ ሀገሬ ተመልሼ የተቃጠለውን መጠነኛ ፋብሪካ ከፈትኩ ግን ሁለቱንም ለማግኘት አልቻልኩም። በእርግጥ በየጊዜው ወደ ዱባይ ለስራ እመላለስ ስለ ነበር የጠበቀ ፍለጋ አላደረኩም። ከዓመት በፊት ግን ሙሉጌታ ሐረር እንዳለ መረጃ አግንቼያለሁ"

" ማርያማዊት የትገባች ታዲያ?"

" እስካሁን ያወኩት ነገር የለም"

" ፈልገን ማግኘት አለብን"

" ለኔ ተውልኝ የገባውበት ገብቼ አፈልጋታለሁ" ትላንት ነበር ይህን ንግግር ከሚልክያስ ጋር መኑ ታምራት ያደረገው እናም ገና ከጠዋቱ 12:00ሰዓት ሲል ነበር ማልዶ

የተነሳው::

"ምነው ልጄ? አሉ እናቱ እማማ አለምነሽ:: በጠዋቱ ስለተነሳ ግራ ተጋብተው::

" እማ... ማርያማዊትን መፈለግ አለብኝ እውነቱን ለመናገር ሌሊቱን ሙሉ ራሴን ስወቅስ ነበር:: ተማሪ እያለን ጓደኝነታችን ላይቋረጥ ቃል ኪዳን ገብተን ነበር:: ቃላችንን ግን አልጠበቅንም! ሕይወትን ለማሸነፍ ስንሯሯጥ ተበታትነን ቀረን! ያመልካም የነበረ ጓደኝነታችን ሳይቀጥል እንቅፋት ገጠመው ከዚህ በኋላ ግን ሁሉ ነገር ልክ ይሆናል አይዞሽ እማ የበፊቱ ደስተኛ ህይወቴ ይመለሳል" እናቱ ፊታቸው በደስታ አበራ::

"ታዲያ ቁርስ በልተህ ለምን አትወጣም?" እናቱን ላለማስከፋት ቁርሱን በልቶ አንድ ሰዓት ሲል ወጣ:: በር ላይ አቶ አሰግድ ቆመው የፍልስፍና መፅሐፍ በጠዋቱ ያነባሉ:: ጎረቤቱ ናቸው:: እርሳቸውም ቀንደኛ የቅንጅት ደጋፊ ነበሩ...

" እንዴ... አንተ ነህ ወይስ አይኔ ነው" አሉት እጅግ ውብ አልባሳትን ለብሶ እና ፀጉሩን ተቆርጦ ሲመለከቱት::

" እንደምን አደሩ እኔው ነኝ አቶ አሰግድ::"

" ምን ተገኘ ባክህ?" እቁብ ወጣልህ እንዴ?"

" እግዚሐብሄር መና አወረደልኝ"

" እየቀለድክ ነው?"

" ሌላ ጊዜ እንጫወታለን ጋሼ አሁን አንድ ስፍራ አስቸኳይ ቀጠሮ አለኝ"

" ሂድ ... ሂድ... ይቅናህ የኔ ልጅ" አሉት አቶ አሰግድ አግኝቶ ያጣ ሰው አጅግ በጣም ያሳዝናቸዋል:: መኑን ለመርዳት ከፍተኛ ጥረት አድርገው ነበር አልተሳካላቸውም እንጂ...

* * *

በታክሲ ውስጥ ሆኖ ዘሪሁን ሕንፃ ፊት ለፊት ያሉትን ሊስትሮ ጓደኞቹን ሲመለከት እንባው ሳያስበው ዝርግፍ አለ:: በታክሲው ውስጥ የነበሩት ሁሉ በምን ሆነ አትኩረው ተመለከቱት ግን ደፍሮ የጠየቀው አልነበረም:: ታክሲዋ እንዴ ስትቆም...እንዴ ስትሄድ ...

መገናኛ ደረሰችና ቆመች:: መገናኛ እንደ ደረሰ ያወቀው በወያላው ንግግር ነው::

" መገናኛ መጨረሻው እዚህ ነው" አለ ቆጣ ባለ አነጋገር:: ወያላው::

እንባውን ጠራረገና ወደ ሀያ አራት ቀበሌ የሚወስደውን መንገድ ያዘ:: በላዳ ተሳፈረ:: የነገው ሰው ትምህርት ቤት ሲደርስ ከላዳዋ ወረደና ወደ ግራ ታጠፈ:: ሀያ ሜትር ከመንገዱ ገብቶ የተሰራውን መኖሪያ ቤት አንኳኳ:: ለሁለተኛ ጊዜ ሲመጣ ነው:: ጥሩ ዜና እንዲያሰማው በልቡ እየፀለየ ነው:: አጭር ወፍራም ጡታቸው በጣም ግድንግድ ሴት በር ከፈቱ::

" እንደምን አደሩ እናቴ?"

" እንደምን አደርክ?"

" አባክዎት እናቴ... ላስቸግሮት ነበር"

" ምን ልተባበርህ?"

" አቶ ታሪኩ ሞላ የሚባሉ ሰው የእርሶን ቤት ከዓመታት በፊት ተከራይቶው ይኖሩ ነበር"

" የሞተውን ነው የምትለው?"

" ሞቱ .... እንዴ እናቴ?"

" የመቼህን ብዙ ዓመትም ሊሆናቸው አይደለም እንዴ? ነፍሳቸውን ይማርና ጥሩ ሰው ነበሩ ግን ለቤተሰባቸው የተውት ጥሪት አልነበረም! ቤቱን ብቸኛ ልጁ እና ሚስቱ ይኖሩበት ነበር"

" ከ...ዚያስ እናቴ"

" ጉለሌ ይበሉ ሳሪስ እንጃ ብቻ የት እንደ ገቡ"

" አባክዎ እናቴ ይርዱኝ"

" ቆይ አንተ ግን ምንድ ነህ? ለምንድነው የፈለካቸው"

" እናቴ እኔ ..." አለና ይዞት የነበረውን ፎቶ ግራፍ አሳያቸው:: በመጠኑ ጉዳዩን አስረዳቸው::

" እንጃ ብቻ ... ጉለሌ ይበሉ ሳሪስ ... ለማንኛውም ቆይ እስቲ " አሉና ፊታቸውን ወደ ቤታቸው መልሰው

" እጅግአየሁ ... እጅግአየሁ ... "ብለው ተጣሩ:: ግመል የመሰለች ወጣት መጣች::

አጠገባቸው ደርሳ በሚያስፈራ አይኖቿ እንግዳውን ተመለከተቻው:: እየፈራ እጁን ዘርግቶ ጨበጣት::

" እስቲ የነ ማርያማዊትን አድራሻ የምታውቂ ከሆነ ንገሪው!!"

" ካልለቀቁ ጉለሌ ሳሙና ፋብሪካው አጠገብ ያለው ሰማያዊ ብረት በር ነበር የተከራዩት"

" በጣም! በጣም ነው የማመሰግነው እናቴ! እንቺንም ከልብ አመሠግናለሁ መልካም ቀን ይሁንላችሁ" አላቸው::

" ካገኘሀቸው ሰላምታ አቅርብልን"

መኑ በፍጥነት ከአካባቢው ተሰወረ::

*  *  *

ግመል የመሰለችው ወጣት እንዳለችው መኑ የተጠቆመውን አካባቢ በፊትም ያውቀው ስለ ነበር ሳይቸገር ደርሶ ምልክት የተሰጠውን በር አንኳኳ:: ተከፈተ::

" ይቅርታ አባከህ ማርያማዊትን ፈልጌ ነበር?" መካከለኛ ቁመት ያለው ፊቱ ከርር ያለ፤ አይኖቹ የደፈረሱ፣ ጥርሶቹ ከመቆሸሻቸው የተነሳ መልካቸው ቢጫ ቀለም የተቀቡ የሚመስሉ ወጣት እግር ነው በሩን የከፈተው:: ወጣቱ በንቀት አይነት መኑን ከፀጉሩ እስከ እግሩ ተመለከተው::

" ከዚህ ለቀዋል እኮ!!"

በጥፊ እንደተመታ ሰው ክው ብሎ ቀረ::

" መ...ቼ?"

" ሁለት ዓመት አለፋቸው መሰለኝ"

" አሁን ያሉበትን አድራሻ ተባበረኝ እባክህ"

" አላውቅም"

" እባክህ አስታውስ ... ወይ ሌላ ሰው ጠይቅልኝ"

"አላውቅም ግን ..." አለና ትኩር ብሎ መኑን ተመለከተው:: መዘነው::

"ግን ምን?"

" ብር ትሰጠኛለህ?"

" የምን ብር?"

" አታርፍም እንዴ? ብር ነዋ! ጨላ! መረጃ ከፈለክ መበጠስ አለብህ... እርግጠኛ ሆኜ የምነግርህ ደግሞ ያለ እኔ ይህን መረጃ ማንም ሊነግርህ አይችልም" ፍፁም እርግጠኝነት በተሞላበት አነጋገር አለው::

" ስንት ልስጥህ?"

" 40 ብር ገፍትር"

መኑ ብሩን አወጣና ያዘው :: ልጁ መኑ ብር ሲያወጣ ዋሌቱ ውስጥ ብዙ እንደሆነ ሲመለከት ሀሳቡን ቀየረ::

" ተናገር ይኸው"

" እናቷ ሞተዋል!"

" ምን?"

" ደም ብዛት ነበረባቸው ጭረዋል! ምን ያስደነግጥሀል መሞት ብርቅ ነው እንዴ? እኔም አንተም እኮ ወረፋችን ሲደርስ እንሞታለን! ብዙነሽ በቀለ የዘፈነችውን ምርጥ ሙዚቃ አልሰማህም?"

"ሠምቻለሁ እሺ ማርያማዊትስ?"

" ጨምራ ብር?"

ሀያ ብር አውጥቶ ሰጠው::

" በሕይወት እዚሁ አዲስ አበባ አለች" ይህን ተናግሮ ዝም አለ:: እርግጥ ስለማርያማዊት እንዳለው እሱ ብቻ ነው የሚያውቀው ይህ ደሞ ያለ ምክኒያት አልነበረም:: በመሀከላቸው የአስር ዓመት ልዩነት ቢኖርም በጣም ነበር የሚያፈቅራት:: እናም ቤታቸውን ለቀው ከወጡ በኋላ እንኳ ስራዬ ብሎ የሚከታተላት እሱ ነበር:: አሁንም የሚከታተላት እሱ ነው:: መኑ ወጣቱ እየተጀነነ ዝም ማለቱ ተጨማሪ ገንዘብ እንደሆነ ስለገባው ሀያ ብር

ጨመረለት::

" ለምንድነው የፈለካት" አለው ከፍ ዝቅ አድርጎ እየተመለከተው::

" ጓደኛዋ ነኝ"

" ምን አይነት ጓደኛ?"

መኑ ምን ማለት እንዳለበት ትንሽ ጊዜ አሰበና በብስጭት መልክ ተናገረ::

" ቢቃ ጓደኛዬ ነች!"

እስካሁን የተቀበለውን ስማኒያ ብር አወጣ " እንካ ብርህን ያዝ ያለችበትን አላውቅም!"

መኑ ልጁን በጥፊ አልያም በቦክስ አልያም በቴስታ ቢመታው እጅግ ደስ ባለው ነበር:: ብስጭት እያለ ከኋላ ኪሱ ገብቶ ሀምሳ ብር አወጣ::

" እሺ ይህን ተጨማሪ ብር ያዝ"

" ብርህን እንካ ብያለሁ እኮ"

መኑ መቶ ብር አወጣና በንዴት ጨብጦ ያዘው::፤

" ስለ እግዚአብሔር ብያለሁ እባክህ ያለችበትን ንገረኝ"

ብሩን ተቀበለው:: ትንሽ ተነፈሰ:: ቢያንስ ሁለት ቀን የሚጨስበት ብር ሲያስበው ስላገኘ በጣም ተደስቶ ብሩን ኪሱ ውስጥ ከተተ::

" በሰላም ነው የፈለካት እርግጠኛ ነህ ግን"

" በሰላም ነው! ካላመንከኝ ይህን ፎቶ ተመልከት::" ወጣቱ ፎቶውን ተመልክቶ ራሱን ነቀነቀ:: ፎቶው ላይ ያለችውን ማርያማዊትን ሳማት:: ገና ህፃን ሳለችም ውብ እንደ ነበረች ተገነዘበ:: ይህን ፎቶግራፍ መወሰድ እንዳለበት ወሰነ::

" በአንድ ነገር ከተስማማን ያለችበትን እነግርሀለሁ"

ምን እንዳሰበ ለማወቅ አይኖቹን ተመለከተው፤ ምንም ነገር ግን ሊያነብ አልቻለም:: በዝምታ ተመለከተው...

" ይህን ፎቶ እወስደዋለሁ!"

መኑ አንድ አይንህን ስጥ እንደተባለ ሰውነቱን የሆነ ነገር እንደወጋው ስቅጥጥ ... ውርር

ነገር አደረገው፡፡ ወጣቱ ሳያስበው ፎቶውን ከእጁ ላይ ምንጭቅ አደረገው፡፡ በሁኔታው ወጣቱ ደንገጥ ነገር አለ፡፡ መኑ ቦርሳው ውስጥ የቀረውን አምሳ ብር አወጣና ሰጠው፡፡ ትዕግስቱ ስላለቀ በስጨት ብሏል፡፡

" የት ነው ያለችው"

" ከሷ ፍቅር ቦንቃ ታውቃለህ ስለቀጨመኝ ነው የምከታተላት እንዴት አይነት ልዩ ውብ ልጅ ነች መሰለችህ? በጣም ነው የማፈቅራት! ውብ አይናማ እያልኩ ነው የማዜምላት! የዘንባባ ማር ነሽ ነው እያልኩ የማዜምላት!..."

" አባክህ ያለችበትን ብቻ ንገረኝ"

" እንድነግርህ ከፈለክ ኪስህ ውስጥ ያለውን ብር አስር ብር ለታክሲ ብቻ አስቀርተህ ስጠኝ! ይቺን የለበስካትንም ምርጥ ጃኬት አውልቀህ ስጠኝ! ያደረካትንም ጫማ አውልቀህ ስጠኝ! እንቢ ካልክ የሰጠሽኝን ብር ይዘህ መጥፋት ትችላለህ! በእርግጠኝነት የምነግርህ ግን ማርያማዊት ያለችበትን ያለ እኔ ማንም ሊነግርህ በተዓምር አይችልም፡፡

መኑ ታምራት ወጣቱን በትኩረት ተመለከተው፡፡

" እባክህ አትቀልድብኝ"

" እየቀለድኩ አይደለም"

መኑ ጃኬቱን አወለቀ፡፡ ሚልኪያስ ያመጣለትን ውድ ጫማም አወለቀ፡፡ ኪሱ ውስጥ ያለውን ገንዘብ ሁሉ አውጥቶ አሳየውና አስር ብር ብቻ አስቀርቶ የተቀረውን ሰጠው፡፡ ወጣቱ በፍጥነት ተቀበለው፤ ፈገግ ለማለት እየሞከረ ጠጋ ብሎ በጆሮው ሹክ አለው፡፡ መኑ ኤሌክትሪክ እንደያዘው ሰው ክው ብሎ ቀረ፡፡ እንደ ምንም ብሎ አይኖቹን አጥብቦ ግንባሩን ሰብስቦ ተመለከተው፡፡

" እውነትህን ነው?"

" እውነቴን ነው!"

# 8

# ቀን ስድስት...

ከምሽቱ 3፡25 ደቂቃ ነው፡፡

Rose Concorde Hotel የተሰጠውን ትዕዛዝ ለመፈፀም ይዲድያ ከሸራተን ሆቴል መርቸዲሱን ይዞ የተነሳው ከምሽቱ 2፡45 ላይ ነበር፡፡ ከሆቴሉ ገብቶ ምቹ ቦታ መኪናዋን አቆማትና ሞባይሉን አውጥቶ ተጫነው፡፡

" ግቢ ገብቻለሁ"

" መጣሁ እሺ"

መካከለኛ ቁመት ያለው ፀጉሩ ወደ ኋላ የሸሸ በሰላሳዎቹ መጨረሻ የሚገኝ ሰው በፈገግታ ተሞልቶ መጣ፡፡ ረዘም ላለ ጊዜ ስላልተገናኙ በምነው ጠፋህ ብዙ አወሩ፡፡

" ምን እግር ጣለህ ዛሬ"

" እዚህ ቤት አንዲት ልጅ አለች እሷን እንድታገናኘኝ ፈልጌ ነበር"

" ምን ችግር አለው"

" ማርያማዊት ታሪኩ ትባላለች"

" ማርያማዊት ... ታሪኩ??"

" ልክ ነህ ?"

" ምን ስማቸውን በየቀኑ ነው የሚለዋወጡት እንደዚህ የምትባል የለችም ግን እርግጠኛ ነህ እዚህ ነው ያለችው?"

" መረጃውን የሰጠኝ በጣም እርግጠኛ ነው"

" እንግዳውስ መጣሁ በቃ ትንሽ ጠብቀኝ" ከመኪናዋ ወርዶ ሊሄድ ሲል ይዲድያ ድንገት ትዝ አለውና ጠራው፡፡

"ምናልባት ይቺ ነገር ከጠቀመችህ"

" ምንድናት ...እ!" ትኩር ብሎ ተመለከተና ፎቶውን መልሶ ሰጠው::

" አውቂያታለሁ! ማከዳ ትባላለች መጣሁ በቃ"

ፈጠን ፈጠን እያለ ባር ውስጥ ገባ:: ብዛት ያላቸው ቻይናዊያን ባሩ ውስጥ ይታያሉ:: ካለው የሙብራት ቀለም ድብልቅልቅነት እና ድብዝዝነት የተነሳ አንዱን ከሌላው በመልክ ለመለየት በጣም አስቸጋሪ ነው:: እሱ ግን ብርሃኑን ስለለመደው በአትኩሮት ተመለከተ:: ይሳሳቃሉ... ይተሻሻሉ... ይሳሳማሉ... ዝሙት ለጉድ እየተፈፀመ ነው... ፈለገ ፈለገና በመጨረሻ ማከዳን ተመለከታት::

ከቀናት በፊት ኢትዮጵያ ለንግድ ስራ ከመጣው ቻይናዊ ኢንጂነር ጋር ተቀምጣለች:: ቀስ ብሎ ተጠጋትና በጆሮዋ ሹክ አላት:: ይቅርታ ጠይቃ ተነስታ ተከተለችው::

" ምን ተገኘ?"

" ሰው ይፈልግሻል"

" ዜጋ ነው አበሻ"

"አበሻ..."

እያወሩ መርቸዲሷ ጋር ደረሱ:: ይዲድያ በማከዳ ውበት ክው ብሎ ቀረ::

" ይኸው ወዳጄ ተፈላጊዋ እሷነች" አስተዋወቃቸውና ወደ ስራው አመራ:: መኪናዋ ውስጥ ገብታ ተቀመጠች:: የተቀባችው ደስ የሚል ሽቶ መኪናዋን አወዳት:: በሚያምሩት አይኖቿ ተመለከተችው:: ሚሪንዳ የሚመስሉት ትናንሽ ከንፈሮቿ ወደ ጎን አፈገፈጉ:: የይዲድያ የልብ ትርታ ጨመረ... እንደዚች ያለች ውብ አይቶ አያውቅም...

...'ከጋለሞታ ሴት ከንፈር ማር ይንጠባጠባልና አፍዋም ከቅቤ የለሰለሰ ነውና ፍጻሜዋ ግን እንደሬት የመረረ ነው! ሁለት አፍ እንዳለው ሰይፍም የተሳለ ነው፤ እግሮችዋ ወደ ሞት ይወርዳሉ አረማመድዋም ወደ ሲኦል ነው፤ የቀና የሕይወት መንገድ አታገኝም በአካሄድዋ የተቅበጠበጠች ናት:: የሚታወቅም አይደለም...'

የት ይሆን ያነበበው? ምናልባት መፅሐፍ ቅዱስ ላይ ነው?... የአባቱ ምክር ልክ

እንደሆነ ማመን የጀመረው ገና ወጣት ሳለ ነበር፡፡

"የወንድ ልጅ መጥፊያ የገንዘብ ፍቅር እና ቆንጆ ሴት ናቸው፡፡ ወንድ ልጅ ገንዘብ ሲያገኝ አስተሳሰቡ ይታወራል! ገንዘብ ሁሉን ነገር ማድረግ ይችላል ሲል ይታበያል በተለይ ወንድ ልጅ ከውብ ሴት ፍቅር ከያዘው ዓለም ሁሉ ይገለባበጥበታል!" ይሉት ነበር፡፡ በደንብ ሲመለከታት 'ውብ ግን የተሰማራችበት የሽርሙጥና ንግድ እጅግ አስጠሊታ ነገር ነው...' አለ ለህሊናው፡፡ ከሀሳቡ የመለሰው የማከዳ ድምፅ ነበር፡፡

"እንነጋገራ!"

" ይቅርታ ለኔ አይደለም" አለና ካርዱን አውጥቶ አሳያት፡፡ ወደ ስምንት ጊዜ ሸራተን ከተለያዩ የውጭ ሀገር ሰዎች ጋር አድራለች፡፡ የምታገኘው ብር በዛያለ ስለሚሆን ደስ አላት፡፡

" ለአንድ ቀን ነው ወይስ..."

" ስለገንዘቡ አትጨነቂ... ነገ ጠዋት 4፡00ሰዓት ላይ ሸራተን ትመጪያለሽ ወይስ መጥቼ ልውሰድሽ?"

" እመጣለሁ! ስደርስ ካርዱ ላይ ባለው ስልክ እደውላለሁ"

" አደራ እንዳትቀሪ፡፡"

" አትጨነቅ አልቀርም! ሽርሙጣን ማመን ሱሪ በአንገት ቢሆንም እኔ ግን ቃሌን አጠብቃለሁ"

... ግርማ ሞገስ ባለው አረማመድ ከመኪናዋ ራቀች፡፡ ይዲድያ መኪናዋን አስነስቶ ከሆቴሉ ወጣ፡፡ መንገድ ላይ ለሚልክያስ መደወል እንዳለበት ትዝ አለውና ሞባይሉን ተጫነው፡፡

" እግንቼያታለሁ ጌታዬ"

" ምን አለችህ?"

" ነገ 4፡00 ሰዓት ላይ ትመጣለች!"

" ሜርሲ! አመሠግናለሁ! ግን እባክህ የሚቻል ከሆነ ይቺ ጌታዬ የምትለዋን ቃል ባትጠቀም ደስ ይለኛል"

" አምክራለሁ ጌታዬ" ይዲድያ ሊል ካሰበ በኋላ በልቡ እየሳቀ "እሞክራለሁ" ብቻ አለው::

# 9

# ቀን ሰባት ...

ከግማሽ ሰዓት በፊት ሚስተር ኤድዋርድ ደውሎ ለረጅም ደቂቃ ሁለቱንም ሲያናግራቸው ነበር፡፡ ሁለቱም ትላንት የጀመሩት አዲስ መፅሐፍ በጣም ልብ አንጠልጣይ ስለ ነበር እያነበቡ ናቸው፡፡ ድንገት ግን ካትሪን ማንበቧን አቁማ ዝም ብላ ትመለከተው ገባች፡፡ራሷን ትጠይቅም ገባች፡፡ 'እንዳፈቀርኩት ያውቅ ይሆን?... ወይስ እንደ ተማሪው ወይስ እንደ እህቱ... ወይስ እንደ ጓደኛው ይሆን የሚመለከተኝ ወይስ ..?'

ስድስተኛ ስሜቱ ሹክ ብሎት ይሆናል እሱም ድንገት ቀና ሲል በትኩረት ስትመለከተው ያዛት፡፡ ፈገግታ ለገሳት፡፡

" ከማንም በላይ እንደምወድህ ግን ታውቃለህ?"

" እኔ ራሴ ከማንም በላይ እወድሻለሁ"

" እውነት? ለምን?

" ቆንጆ ነሽ! ግልፅነሽ! ተጫዋች ነሽ! ጎበዝ ነሽ! አንባቢ ነሽ! ሰው ታከብሪያለሽ! በጣም ብዙ የሚወደዱ ነገሮች አሉሽ፡፡ ከሁሉም በላይ በጣም የምወድልሽ ግን የቢሊየነር ልጅ አይነት ሙዝዝ ያለ ፀባይ የለሽም! በዚያ ላይ ባለትልቅ ተስፋ ነሽ!!"

" እኔ ግን ለምን እንደምወድህ ታውቃለህ?"

ዝም ብሎ ተመለከታት፡፡

" ባሌ ስለምትሆን እኮ ነው!!"

ረጅም ሳቅ ሳቀ፡፡ ሳቁን ሳይጨርስ ሞባይሉ ጥሪ አሰማ ፡፡ አነሳው፡፡

"አሺ ይዲድያ"

"ግቢ ደርሳለች ላስገባት"

" በጣም አመሠግናለሁ አስገባት"

እያነበበ ያለው መፅሐፍ መሳጭ ስለ ነበር የሰዓቱ መከነፍ አልታወቀውም::

" መጣች" አለችው ካትሪን ማርያማዊትን ለማየት በጣም ስለቋመጠች::

"አዎ ካትሪ" አላት ሚልከያስ ፊቱ በደስታ ተሞልቶ:: ደማቅ ፈገግታ ከለገሰችው በኋላ መጽሐፉዋን ይዛ መኝታ ቤቷ ገባች:: ማርያማዊት አፍታም ሳትቆይ እጅግ አጭር ቀሚስ አድርጋ ከሌላው ጊዜ ይበልጥ ተውባ መጣች:: ሚልከያስ የሚያምረው ሶፋ ወንበር ላይ እንዳለ በሩን ይዲድያ ከፈተና አስገብቶዋት ሄደ:: ሚልከያስ ገና እንዳያት ሄዶ ሊጠመጠምባት አሰበና እንደምንም ብሎ ግን ራሱን አረጋጋ::

ክፍሉን አማተረች::

በፈገግታ ተውባ ቀረበችው:: በደንብ ተመለከተችው:: ለምን እንደሆነ ባይገባትም ሰውነቷን የሆነ ነገር ውርር አደረጋት:: እስካሁን ካየቻቸው ሆነ አብራቸው የወሲብ ንግድ ከፈፀመቻቸው ወንዶች ሁሉ በውበት እሱ ግንባር ቀደም ነው:: ሞዴሊስት እንደሚሆን ገመተች:: ምንም ሆነ ምንም የሚመጣ ለውጥ ግን የለም... ምናልባት የጠየቀችውን ብር ይከፍላታል... አልጋ ላይ ይፋተጋሉ.. ገንዘቧን ትቀበላለች... ትሄዳለች:: አለቀ! የሸርሙጣ ሕይወት ይሄ ነው... እንደ ተቀመጠ ተናገረ::

"Please , Have a sit"

አመስግና ተቀመጠች:: ከላይ ለብሳ የነበረውን ጃኬት አውልቃ ወንበሩ ላይ አስቀመጠች:: እንዴት ታምራለች?

ከጠረጴዛው ላይ የወረቀት ከምር እና ብዕር ተቀምጧል:: ጨዋታ ለመጀመር ያህል ጠየቀችው::

"Are you a writer?"

" እመስላለሁ ቆንጂት?"

" አማርኛ ትናገራለህ እንዴ?"

" እምከራለሁ! እንዳልሽው ጀማሪ ፀሐፊ ነኝ አንቺንም የፈለኩት ለዚሁ ጉዳይ ነው"

" አልገባኝም"

" ለምትሰጪኝ መረጃ የጠየቅሽኝን ብር ሁሉ እከፍላለሁ"

" የምን መረጃ?"

ሽርሙጥና /Prostitution/ የሚለውን ቃል መጥራት በጣም ስላስጠላው ነው ቃላት ፈለገና ተናገረ::

" እንዳንቺ አይነት ሥራ የሚሰሩ ወጣቶች ዙሪያ ነው ጥናት የማደርገው እና መረጃ እንደምትሰጪኝ ተስፋ አለኝ"

" ምን ዓይነት መረጃ ነው የምሰጥህ?" አፍንጫው ላይ የነበረውን መነፀር ወደ አይኑ በሌባ ጣቱ አደረገና ተመለከታት::

" የተወሰኑ ጥያቄዎች ናቸው ለእነሱ መልስ መስጠት ብቻ ነው፤ ለእያንዳንዱ ጥያቄ መቶ ዶላር እከፍልሻለሁ"

" ጀምር!!" አለች በፍጥነት::

" ወደዚህ ስራ እንዴት ገባሽ?"

ምንም ሳትጨነቅ መናገር ጀመረች::

" በቃ! በሕይወቴ ትልቅ ቦታ የነበራቸው እናቴም አባቴም ተስፋዬም ሞቱ:: ሥራ የለኝም አማራጭ ሳጣ በጓደኛዬ አማካኝነት እንደቀልድ ጀመርኩት፤ በነገራችን ላይ በምንም ተዓምር ሴተኛ አዳሪዎችን በጭራሽ እንዳታምናቸው ሁሉም እንድታዝንላቸው የሆነ የሚያሳዝን የፈጠራ ታሪክ አቀነባብረው ይነግሩሀልና! ለማንኛውም ወደ እኔ ታሪክ ስመለስ ባጭሩ ስራውን የጀመርኩት በራሴ ስንፍና የተነሳ ነው"

" ማለት?"

" ሆቴል ቤት የምትሰራ ጓደኛ ነበረችኝ ስለ ስራው ነገረችኝ በተለይ ሳቢ የሆነ መልክ እና ቁመና ስላለሽ በፍጥነት ቶሎ ይሳካልሻል ስትለኝ ገባሁበት"

" የልጅነት ህልምሽ ምን ነበር? ማለቴ የሞተው ተስፋሽ ምን ነበር?"

"ጋዜጠኛ ወይም ደራሲ መሆን ነበር"

" በምትሰሪው ስራ ሀጢያተኝነት ተሰምቶሽ ያውቃል... ማለቴ ከሀሊናሽ ጋር ግብ ግብ አይነት ነገር"

" አሁን አንድ የተገነዘብኩት ትልቅ ሀቅ ሁሉ ነገር የሚያስፈራህ እስከምትጀምረው ድረስ ብቻ ነው፤ ከዚያ ልምድ ይሆናል! ልምድ ደግሞ ሲደጋገም ለራስህ የምታቀርበው ምክኒያት አሳማኝ ይሆናል:: በዚያ ላይ ሀጢያት ሲደጋገም ፅድቅ ይሆናል!"

ፈገግ አለ:: ፈገግታው ተመቻት:: ' ጥርሶቹ ደግሞ ሲያምሩ ... ምነው ለሴት ቢሰጣቸው ኖሮ' አለች ማርያማዊት ለህሊናዋ::

" ጥርስህ በጣም ያምራል"

" አመሠግናለሁ! ስምሽ ማን ነው?"

" ማክዳ"

" እውነተኛው"

" እህ እውነተኛ ስሜን ለማንም ነግሬ አላውቅም ላንተ ግን እነግርሀለሁ ማርያማዊት"

" መቅደላዊት ማርያምን ታውቂያታለሽ?"

"በጣም ብዙ ጊዜ ስላለኝ በርከት ያሉ መፅሐፍትን ለማንበብ አጋጣሚ ተፈጥሮልኛል! በዳቪንቺ ኮድ መፅሐፍ መሠረት የኢየሱስ ፍቅረኛ ነበረች:: እሱን መፅሐፍ አንበብከው በጣም የተመቸኝ መፅሐፍ ነው"

" ሠምቻለሁ ግን አላነበብኩትም" አላት:: ስለ ኢየሱስ ካትሪን የነገረችውን እያስታወሰ::

" በመፅሐፍ ቅዱስ መሠረትስ" አላት

" መፅሐፍ ቅዱስ አላነብም"

"ለምን?"

" መፅሐፍ ቅዱስ የሚያነብ ሚስኪን እና ደፋር ሰው ነው! እኔ ደሞ ፈሪ ነኝ፤ ከብርሃን ይልቅ

ጨለማን እወዳለሁ:: በዚያ ላይ አንድ የቲዎሎጂ ምሁር መፅሐፍ ቅዱስ ደህዎችን ለማፅናናት የተፃፈ የክፍለ ዘመኑ ምርጥ ልቦለድ ነው ሲል ሠምቻለሁ"

በግርምት እና በአድናቆት ተመለከታት::

" እሺ ሕይወትሽን ለመቀየር ትፈልጊያለሽ?"

" አልፈልግም"

"ለምን?"

"ስለወደፊት የሚጨነቅ ተስፋ ያለው ሰው ነው:: ወንድሜ!" አለችው ግዴለሽነት በተሞላበት አነጋገር:: ሚልኪያስ ጭንቅላቱን ከግራ ወደ ቀኝ አወዛወዘ:: አይኑ ላይ ጋርዶት የነበረውን መነፅር አነሳና ጠረጴዛው ላይ አስቀመጠው:: እሷ ደሞ አበባ አበባውን በግዴለሽነት ትመለከታለች::

" ማርያማዊት ታሪኩ 100ሺ ዶላር ብታገኚ ምን ታደርጊያለሽ?" ከብሩ ብዛት ይልቅ ያስደነገጣት ሙሉ ስሟን ማወቁ ነው::

" ታሪኩ? አባቴን እንዴት አወከው?"

" ሰዎች ነግረውኝ ነው ይልቅ በብሩ ምን ታደርጊያለሽ?"

" ወይ አንተ በጣም ቀልደኛ ነህ! 100 ሺ ዶላርን እንደ ቀላል ነገር ስትጠራው ትገርማለህ! አንድ ጊዜ አንድ ሀብታም ብዙ ወጣቶችን ሰበሰበና ወረቀት አውጥቶ ሰጥቶዋቸው ሁሉ በፍጥነት በአስር ደቂቃ ውስጥ የምትፈልጉትን ያህል የብር መጠን ፃፉና በዚያ ብር ምን እንደ ምትሰሩበት አስፍሩ አላቸው! ወጣቶቹ ሁሉ ህልም አልነበራቸውም ምን መስራት እንዳለባቸው ከራሳቸው ጋር ሲያወጡ ሲያወርዱ ሀብታሙ ሰው የሰጣቸው አስር ደቂቃ አለቀና ሀብታሙ ሰው በወጣቶቹ ህልም አልባነት በጣም እያዘነ ሄደ:: ስለገንዘብ የሚያወራ አንድ መፅሐፍ ሳነብ አስቀድመህ ማወቅ ያለብህ ዋናው ትልቅ ቁም ነገር ገንዘብ ቢኖረኝ ብለህ ሳይሆን ገንዘብ ሲኖረኝ በዚያ ገንዘብ ምን ላደርግበት እችላለሁ?? የሚለውን ወሳኝ ጥያቄ መመለስ ነው ይላል:: ባጠቃላይ ወሬዬን ሳላጥረው የኔ ችግር ገንዘብ ነው፤ ገንዘቡን ካገኘሁ የምተውን ህልሜን ዳግም ሕይወት እዘራበታለሁ!!"

"ዋው! በጣም ልክ ነሽ!" አላትና ጠረጴዛው ስር የነበረውን ሳምሶናይት አወጣና ታሽጎ የተቀመጠውን ትልቅ ፖስታ አውጥቶ ሰጣት::

" ምንድ ነው?"

"100 ሺ ዶላር! ሕይወትሽን ለውጪበት! የሞተውን ህልምሽን እንዳልሽው ዳግም ሕይወት ዝሪበት! እውነቱን ነው የነገርሽኝ ታሪክ በጣም አስተማሪ ነው ትልቁ ነገር ገንዘብ ሳይሆን ህልም ነው! ህልም ከሌለሽ ግንዘብ ቢኖርሽም ሆነ በአጋጣሚ ብታገኚ ምንም ነገር ሳትሰሪበት በዋዛ ፈዛዛ ያልቃል:: አንቺ ግን ህልም ስላለሽ ያን ህልምሽን እውን አድርጊበት!!"

"እየቀለድክብኝ ነው? የውሸት ገንዘብ ነው እንዴ?"

በዚህን ደቂቃ ሚልክያስ በእግሩ መሬቱን በመጠብጠብ ምልክት ስለሰጣት ካትሪን ከመኝታ ቤት ቪዲዮ ካሜራዋን ይዛ ወጣች::

" ጓደኛ ማለት ግማሽ አካል ነው" ቀና ብላ ተመለከተችው:: ኪሱ ውስጥ የነበረውን የአንገት ሀብል አወጣ::

" ይህ የእናትሽ ነበር አይደለም?"

" ከ... ከ... የት አመጣኸው?" አለች በጣም ደንግጣ::

ከዚህ በላይ ሊገድበው ስላልቻለ እንባው ዝርግፍ አለ:: ኪሱ ውስጥ የነበረውን ፎቶ አወጣና አሳያት:: እንደምንም ተናገረ::

"ማርያማዊት... ሚልክያስ እኮ ነኝ"

ባለማመን እጇን አንስታ አፉዋን ያዘች:: እንዴት እንደተነሳች ባታውቅም ሄዳ ጥምጥም አለችበት::

* * *

ማርያማዊት ሆሊውድ ወይም ቦሊውድ ውስጥ የተሰራ ፊልም የምታይ እንጂ እውነት አልመሰላትም:: በፍፁም ከ16 ዓመታት በኋላ አስታውሶዋት ይመጣል የሚል ግምት አልነበራትም:: ሕይወቷ ግን ወደ አዲስ ምዕራፍ እንደተሸጋገረ ወዲያው ተሰማት:: ለመጀመሪያ ጊዜ የደስታ ሳቅ ሳቀች::

በጣም ያላሰበችው ነገር ስለ ነበር ከብዙ ደቂቃ በኋላ ነው ከፍሉ ውስጥ ያለችውን ውብ ወጣት የተመለከተቺያት:: ይቅርታ ጠይቃ ራሷን አስተዋወቀች::

" ካትሪን ኤድዋርድ እባላለሁ ስላገኘሁሽ በጣም ተደስቻለሁ"

" ኦ! በጣም የምታምር ናት ሚልክያስ" አለችው:: ሚልክያስ ሳቀና ዝም አለ:: ልክ 4:38 ሲል በሩ ተከፍቶ መኑ ገባ:: ከኋላዋ መጥቶ እስከሚቆም ድረስ አላየችውም::

" መሙሚማታ"

ዞር ብላ ተመለከተችው:: የምትናገረው ስለጠፋት ዝም ብላ ተነስታ ጥምጥም አለችበት:: ቤቱ ሳቅ ብቻ ሆነ:: ከአስራ ስድስት ዓመት በኋላ ተመልሰ መገናኘት የሚፈጥረውን የስሜት ድባብ በትክክል ማስረዳት የሚችሉት ያለጥያቄ እነሱ ብቻ ናቸው:: መኑ...ሚልክያስ ... ማርያማዊት... ካትሪን ትቀርፃለች...

# 10

# CITY OF LOVE

## የፍቅር ከተማ

## ቀን ዘጠኝ...

ነጮቹ የፈረንሳዩዋን ፓሪስን የፍቅር ከተማ እንደሚሏት ሁሉ አበሾችም ጥንታዊት የሐረርን ከተማ የፍቅር ከተማ እያሉ ይጠሩዋታል:: በሀረር ሰው ከሰው ለመላመድ ሳይሆን ሰው ከጠላቱ ጅብ ጋር ማዕድ አብሮ ተቀምጦ ይበላል:: ጅብና ውሻ እንደ ወዳጆች አብረው ይጫወታሉ... አይጥና ድመት አብረው ዳንኪራ ይመታሉ... ለእስልምና እምነት ተከታዮች ደሞ አራተኛዋ የአለም ቅዱስ ከተማ ናት... ጥንታዊት ሐረር::

ከአራት ዓመታት በፊት በ1994 ሙሉጌታ ታመነ ከአዋሳ ተመርቆ አዲስ አበባ ሁለት ዓመት ከሰራ በኋላ የተሻለ ክፍያ ስላገኘ ሐረር ይመጣል:: ታዲያ ሁለት ዓመት ሰርቶ አዲስ አበባ ተመልሶ ቋሚ ሕይወት ለመመስረት ነበር እቅዱ::

ከታሪካዊቷ ሐረር ከተማ በገባ በሁለተኛው ወር ግን ከአንዲት ሐረሪ ጋር ፍቅር ወደቀበት፤ በዓመቱ መጨረሻ አብረው ነበሩ:: በሁለተኛው ዓመት ዓይኑን በዓይኑ ተመለከተ... አለቀ:: ቤተሰብ የለም! አዲስ አበባ የለም ...ኑሮውን ሁሉ ጠቅልሎ ሐረር ከተማ ላይ መሠረተ::

ባለቤቱ ወ/ሮ አፊያ ቃሲም ዘወትር ፈገግታ የማይለያት ሴት ነች:: በሕይወቱ እንደሷ ያለ ታታሪ እና ደስተኛ ሴት አላየም:: የመጀመሪያ ጊዜ ወደ መፅሐፍት ማከፋፈያ ቤቷ ያመራው መፅሐፍት ለመግዛት ነበር:: ብቻዋን ነበረች:: ቀድሟ የወደደችው አፊያ ቃሲም ነበረች:: ለዚህ ደሞ በፊት እንዲህ አይነት ወንድ ባገኝ እያለች ታስብ ስለ ነበር ነው:: በምኞት! ... አስተማሪ ባል እንዲኖራት በጣም ትመኝ ነበር::

“Calculation in chemistry የሚል የአትርሳው ጣሰው መፅሐፍ አለሽ?”

“Calculation …ቆይ እስቲ …” ፍለጋ ስትሄድ ከኋላዋ በደንብ ተመለከታት:: ዳሌዋ በጣም ያምራል! ትልቅ ነው! ወንዶች የሴቶችን ትልቅ ዳሌ ለምን እንደሚወዱ ለራሱ ግራ ይገባዋል::

“ ይኸው!” አለችው በፍፁም ፈገግታ እያንፀባረቀች:: የመፅሐፉን ጀርባ አነበበና ገንዘብ አውጥቶ ከፈለ::

“ አመሠግናለሁ የኔ እህት” ብሎዋት ሊወጣ ሲል ፈገግታ የተቀላቀለበት ድምፅ መለሰው::

“ እህትህ ሳልሆን አፈያ ቃሲም እባላለሁ! ኢትዮጵያ ውስጥ ብትዞር አፈያ በሚል የሚጠሩ በጣም ጥቂት ሴቶችን ነው የምታገኘው… ስለዚህ አፈያ ቃሲም ብለህ መጥራት ትችላለህ”

“ሙሉጌታ ታመነ” አላት ሳቅ ለማለት እየሞከረ::

“የት ትምህርት ቤት ነው የምታስተምረው?”

“በምን አወቅሽ አስተማሪ መሆኔን?”

“አቦ የሐረር ተማሪ መፅሐፍ ሊገዛ አይመጣም ሳንቲም ካለው ጫት ቤት ነው የሚያመራው 90% ደንበኞቼ አስተማሪዎችና ወላጆች ናቸው”

ፈገግ አለ:: ደማቅ ፈገግታ::

“ፈገግታህ ያምራል!”

ድንብርብሩ ወጣ:: ከዚያች ቀን በኋላ ትምህርት ቤት የሚያመራው በበሩዋ ላይ ስለ ነበር ሰላምታ መለዋወጣቸውን ቀጠሉ:: በሁለተኛው ወር መጨረሻ

“አቦ ምሳ ለምን አልጋብዝህም ከንግድ ውጪ ምግብ በመስራትም የተዋጣልኝ ነኝ” አለችው:: ወይ ጉድ ተገኝቶ ነው?” ያለ ጥያቄ እሽታውን ገለፀ:: ቤቷ ወሰደችው:: ከቤተሰቧ የወረሰችው የራሷ ቤት አላት:: ሰራቢሶቹን አከራይታ ዋናው ቤት ውስጥ ነው የምትኖረው:: በአራተኛው ወር መኑ አፈያ ቃሲም ቤት ውስጥ ተቀምጦ ሀይለኛ ዝናብ መዝነብ ጀመረ:: ሳያስበው አብሮዋት አደረ… አለቀ በቃ:: እሱ አንድ ቁጥሩን ስጣት እሷ ዜሮዋን ሰጠችው…

ምድር ዘጠኝ ሳትሆን አስር ሞላች:: እንደሞት ሲፈራው የነበረውን ጋብቻ ሳያስበው ተዘፈቀበት:: ሁለቱም ስራ አላቸው ... ሁለቱም ይተሳሰባሉ... ከምንም በላይ ይዋደዳሉ ... እስከ ዛሬም በሚኖሩበት አራተኛ መንደር እንደ ጥሩ የፍቅር እና የጋብቻ ምሳሌ ተቆጥረው ስማቸው በመልካም ሁኔታ ይነሳል:: እርጋታ የሰፈነበት ጋብቻ!

* * *

ሙሉጌታ ከትላንት ጀምሮ እስከ ዛሬው ጠዋት ድረስ የግራ አይኑ እየቆየ በመሀከል በመሀከል ያለ ወትሮው ይንቀጠቀጣል:: ቁርሳቸውን በልተው ከቤት እየወጡ ሳለ ግራ ቢገባው ወደ አፊያ ተመለከተ

"አይኔ ምን ሆኗል ፍቅሬ?"

" ምን ሆነ?"

"ከትላንት ጀምሮ ይርገበገባል"

" አቦ የማትጠብቀውን ሰው ልታይ ነው" አለችውና እየሣቀች መጀመሪያ አይኑን ቀጥሎ ግንባሩን በመጨረሻ ከንፈሩን ሳመችው:: መልካም ውሎ በመመኘት ተለያዩ:: ሙኑ ወደ ት/ቤት አመራ:: አፊያም ወደ መፅሐፍ ቤቷ አመራች:: ሙኑ ትምህርት ቤት ገብቶም የሚያስበው ስለሚንቀጠቀጠው አይኑ ነበር:: ማንን ሊያይ ይሆን? ትዝታ ወሰደውና 1983 ላይ ጣለው:: ሁሉ ነገር ትዝ አለው 'እግዚሐብሄር ከፈቀደ አንድ ቀን ተመልሰን አንድ ላይ እንሆናለን' ራሱን በትዝብት ነቀነቀ:: ቢያንስ ኢትዮጵያ ውስጥ ያሉትን ጓደኞቹን እንኳ የት እንዳሉ አያውቅም ግን ሕብረታቸው እንደሚፀና ቃል ተገባብተው ነበር:: የገባውን ቃልኪዳን አስታወሰ...

ሕይወት ግን ውጥንቅጣቸውን አወጣቻቸው! ፀፀት ወገረው:: ወዲያው ግን በዚህ ክረምት አዲስ አበባ መሄድ እንዳለበት ወሰነ:: ቢያንስ አይናቸውን ማየት እንዳለበት ተሰማው:: በዚህ ሀሳብ ተወጥሮ ሳለ ጓደኛው ከሀሳብ ጎዳና መለሰው::

" እሺ ሙሌ ምነው ተከዝክ?" አለው

" ምን ባክህ ከትላንት ጀምሮ የግራ አይኔ ይርገበገባል?"

" እንግዲህ እኔ ባላምንበትም በባህላችን መሠረት የግራ አይን ለብዙ ጊዜ ሲንቀጠቀጥ የማትጠብቀውን ሰው ልታይ ነው ይላሉ... አንዳንዴ ስለ ባህላችን ሳስብ በጣም ያስቀኛል። ውስጥ እጅህን ሲበላህ ወርቅ ወይም ሀብት ታገኛለህ ይሉሀል... ጥቁር አሞራ ቤትህ ላይ ካረፈ ከዚህ ቤት ውስጥ አንድ ሰው ይሞታል ይሉሀል... የሠርግህ ዕለት መንገድ ላይ እየሄዳችሁ ሌላ ሠርገኛ መስቀለኛ መንገድ ላይ ከመጣ ጋብቻው ይፈርሳል ይሉሀል... ሀቅ ሲልህ ሰዎች እያሙህ ነው ይሉሀል ... እያንዳንዱ ሰው የእርባ ቀን እጣፋንታ አለው ይሉሀል... እነዚህ ሁሉ ከሳይንስ ውጪ ናቸው። አንተስ ምን ይመስልሀል?"አለው።

በመሀከል`መምህራን ወደ ክፍል ግቡ' የሚለው ደውል ስለተደወለ እያወሩ ወደ ክፍል ማምራት ያዙ። ለሚጠብቋቸው ተማሪዎች የያዙትን እውቀት ለማስራጨት ... እውቀትን ከመስጠት የበለጠ ምን ትልቅ ስጦታ አለና!!

11

# ቀን አስር

"አባባ ሚልክያስ አንድ ሀሳብ መጥቶልኝ ነበር?"

"ምን እማማ ካትሪን?"

ተሳሳቁ::

" ጓደኛህ ለሚያስተምርበት ትምህርት ቤት 2000 ሺ ዶላር መድቤያለሁ:: የሴሚስተሩን ሰቃይ ተማሪዎች ለማበረታታት ለምን የብር ሽልማት ወይም ለተማሪ ብር መስጠት ክልክል ከሆነ ብሩ በሚችለው መጠን መፅሐፍትን ገዝተን አንሰጣቸውም?"

በጣም ስለ ተደሰተ ምንም ሳይናገር ግንባሩዋን ሳማት:: ደስ አላት:: ይበልጥ ደስ የሚላት ደግሞ ከንፈሯን ቢስማት ነበር:: ምናልባት ፌንት ታደርግም ይሆናል...

" በጣም ደስ የሚል ሀሳብ ነው ካትሪ" በፕሮግራማቸው መሠረት ሂልተን እና ግዮን ሆቴልን አሳያት:: ታላቁን የአፍሪካን የገበያ አዳራሽ መርካቶን ለሁለተኛ ጊዜ አሳያት:: ምሳቸውን ኢንፔሪያል ሆቴል ተመገቡ:: በሁሉ ነገር ደስተኛ ነች! ከምንም በላይ የተደሰተችው ግን ከእርሱ ጋር ሀያ አራት ሰዓት ከጎኑ በመሆኑዋ ነው::

ከሰዓት በነበራቸው ቀጠሮ መሠረት ከመኑ እና ማርያማዊት ጋር ሲዝናኑ እና ቢጨዋወቱ ዋሉ:: አመሻሽ ላይ ይዲድያ የሐረሩ ጉዞ ሁሉ ነገር እንዳለቀና ዝግጅት ንዲያደርጉ ነገራቸው:: በቀጠሮዋቸው መሠረት ቀልጣፋው ይዲድያ ለራሱ፣ ለመኑ፣ ማርያማዊት፣ ለሚልክያስ፣ ለካትሪን እስከ ድሬደዋ የሚያደርሳቸውን የአውሮፕላን ትኬት ቆረጠላቸው:: ነገ ከጠዋቱ 4:30 ደቂቃ ከቦሌ አየርመንገድ ይነሳሉ:: ድሬደዋ 5:15 ደቂቃ ላይ ይደርሳሉ ከዚያ ሐረር በመኪና ይወስዳቸዋል...

* * *

ሚልከያስ እና ካትሪን ማታ ሽራተን ተመልሰው 'My Bollywood Bride' የሚለውን የ95 ደቂቃ ምርጥ Romance comedy ፊልም አይተው ሲጨርሱ ድንገት ቀን ማርያማዊት ለሁለቱም ያመጣችላቸው ስጦታ ትዝ አላትና መኝታ ቤቷ ገባች፡፡ ይዛ ተመለሰች፡፡ ከፈተችው፡፡ የሀገር ባህል ልብስ ነበር፡፡ በግርምት ተመለከተችው፡፡

" ምን አይነት የሚያምር ልብስ ነው ሚኪ?"

" ባህላዊ ልብሳችን ነው!"

ባለችበት ልብሷን አወላለቀችና ለበሰችው፡፡ በልኳ የተሰራ ይመስል ልክክ ነው ያለባት፡፡

" ዋው! በጣም ነው የሚያምርብሽ ካትሪ!!"

በመስታወት ራሷን ተመለከተች፡፡ ማመን አቃታት!

"በጣም የሚያምር ልብስ ነው! ወድጄዋለሁ! በተለይ ቅለቱ በጣም ደስ ይላል!"

ቀጥሎ የሚመጣው ልመና ወይም ትዕዛዝ ስለገባው ተነስቶ ከማርያማዊት የመጣለትን የባህላዊ ልብስ ስጦታ ለበሰ፡፡ በጣም ነው የለወጠው፡፡ ሁለቱንም ትኩር ብሎ የተመለከታቸው መልስ ላይ ለመቅረብ የተዘጋጁ ሙሽራ እና ሙሽሪት ይመስሉ ነበር፡፡

* * *

እስከ አራት ሰዓት ሲያወሩ ቆይተው ለመተኛት ሁለቱም ወሰኑ፡፡ ወደ ክፍላቸው ሄደው ለሀያ ደቂቃ ያህል እንደተኙ ካትሪን ከመኝታ ቤቷ መጣች፡፡ እንዳሰበችው አልተኛም ነበር፡፡ በፈገግታ እንደሞላች ቀረበችው፡፡

"ምነው ካትሪ?" አላት

"እንቅልፍ እንቢ አለኝ፤ በዚያ ላይ ደግሞ ካንተ ጋር መተኛት እፈልጋለሁ ብቻዬን መተኛቴ ብዙ ምቶች አልሰጠኝም"

ሚልከያስ ደነገጠ፡፡ ሁለቱንም አይደለም ሌላ እንደነሱ የመሰሉ አስር ቀጫጭኖችን በአንድ ላይ ለማስተኛት አልጋው ያስችላል፤ ታዲያ ምን አስደነገጠው? ምንም ሳይናገር ፈገግ ብሎ ተመለከታት፡፡ ዘላ አልጋው ላይ ወጣችና ብርድልብሶቹን አንስታ ከውስጥ ገባች፡፡ እየሳቀች ተመለከተችው፡፡

"ምን እያሰብክ ነው?"

"ስለምንም! ፀጥታ ብቻ!"

" በቃ ተኛ! ነገ መንገደኛ ነን እኮ"

" እሺ ካትሪ"

አጠገቡ የነበረውን መብራት ተጫነው:: ቤቱን ጨለማ ዋጠው:: የሰው ልጅ መብራትን አጥፍቶ የሚተኛው መብራት እንዳይቆጥር.. ቤቱ እንዳይሞቅ ሳይሆን ... ብርሃንን ስለሚፈራ መሰለው:: አሁንም ስለምን እያሰበ እንደሆነ በውል ባያውቅም በጨለማው ክፍል ውስጥ የሕሊናው መብራት እንደበራ ነው:: እንደ ምንም ለመተኛት ግን መጣር ጀመረ::

# 12
# ቀን አስራ ሁለት ...

የጥንታዊት እና ታሪካዊት ሐረርን ዝና! ንግስና! ያቆመው የባቡር ሀዲድ እስከ ድሬደዋ ተዘርግቶ ሲጠናቀቅ እና ለባቡር ዝርጋታው የሐረር ወጣ ገባው መልከዐ ምድር አመቺ አይደለም ተብሎ ሲተው በሐረር ቦታ ድሬደዋ የንግስናውን ቦታ ተረከበች! ሐረር እያዘነች ... እርር... ቅጥል ... እያለች ለድሬደዋ እጇን ሰጠች! ድሬ በተራዋ ማበብ ጀመረች...

መጨነቅ ሆነ ማስጨነቅ የማይወዱት የድሬደዋ ነዋሪዎች ከኢትዮጵያ ከተማዎች ሁሉ እንግዳን በፍቅር በማስተናገድ እና ማህበራዊ ሕይወትን በማወቅ የሚያከላቸው የለም!! እነ ሚልክያስ ... ምሳቸውን ድሬደዋ ራስ ሆቴል ተመግበው ድሬን በመጠኑ ተመልክተው ከአዲስ አበባ 526 ኪ.ሜትር ርቀት ላይ ወደየምትገኘው ታሪካዊት ከተማ ሐረር ትላንት ስምንት ሰዓት ላይ ደረሱ:: የሙሉጌታን አድራሻ ለማግኘት ብዙም አልተቸገሩም ነበር:: በዛሬው ጠዋት ቀጠሮዋቸው መሠረት በቀጥታ ለሐረር ከተማ ታሪካዊ ወደሆነው ትምህርት ቤት ለማምራት ነው ያቀዱት::

ቁርሳቸውን በልተው ወደ ትምህርት ቤቱ አመሩ:: ተማሪዎች ከገቡ በኋላ ስለደረሱ ግቢው ጭር ብሎ ነበር:: መኑ እና ማርያማዊት መኪናው ውስጥ ለመቆየት ወስነው ተቀመጡ:: ካትሪን፣ ሚልክያስ እና ይዲድያ የትምህርት ቤቱ ግቢ ውስጥ ዘለቁ::

" ዳሬክተሩን ፈልገን ነበር" አለ ይዲድያ በፍፁም ትህትና ተሞልቶ:: ዘበኛው እየመራ ወደ አቶ ሁሴን አሊ ቢሮ ወሰዳቸው:: አቶ ሁሴን አሊ አጭር ቦርጫም አስቂኝ የሰውነት ቅርፅ ያላቸው ሰው ናቸው:: ሲያወሩ ከአፋቸው ምራቅ ፍንጥቅ ፍንጥቅ እያለ ይወጣል:: በፈገግታ ተሞልቶው ከወንበራቸው ብድግ አሉ:: ተጨባበጡ:: እነ ይዲድያ የመጡበትን ጉዳይ አጠር አድርገው ነገሩዋቸው::

"በጣም! የምትደንቁ ናችሁ! በእውነት ትልቅ ነገር ነው ያሰባችሁት! ምንም ችግር የለም:: ዛሬን ስጡኝ ነገ 4:00 ሰዓት ላይ ብትመጡ ሁሉን ነገር አዘጋጅተን እንጠብቃችኋለን" አሉ እርግጠኝነት በተሞላበት አነጋገር::

" ሜርሲ መስየ... አመሠግናለሁ ጌታዬ! ሌላም የሚተባበሩን ነገር አለ ጌታዬ" አለ ሚልኪያስ "ጌታዬ" መባልን እሱ ባይወዱም ሰዎችን ግን "ጌታዬ" ማለት ይወዳል...

"ምን ልተባበራችሁ" አሉ አቶ ሁሴን ሁሉንም ለማየት ከፍተኛ ጥረት በአይናቸው እያደረጉ::

"ለተማሪዎች ሽልማት የሚሰጡልን እርሶ እና መምህር ሙሉጌታ ታመነ ናችሁ"

"ምን ችግር አለ! መምህር ሙሉጌታ ማለት እኮ ለሁሉም በትጉህነቱ አርአያ የሚሆን ጠንካራ ተወዳጅ መምህር ነው:: ምንም ችግር የለም:: ይሄ በጣም ቀላል ነገር ነው ሌላ ምን የምረዳችሁ ነገር አለ?"

" እናመሠግናለን ጌታዬ በዚች ሰልክ እንደጨረሱ የተማሪዎቹን ብዛት ይንገሩን ብሩን ለመደልደል እንዲመቸን..."

ተጨባብጠው ከቢሮው ወጡ:: ልክ እነሚልኪያስ ከቢሮው እግራቸው እንደወጣ አቶ ሁሴን አሊ ወዲያው የእስቸኳይ ጊዜ ደውል ደወሉ:: ሁሉም መምህር ግራ እየገባው ከክፍል ወጣ:: ገና አስር ደቂቃ ያህል ግን ይቀር ነበር:: በድንገተኛው ደውል የተደሰቱት ተማሪዎች በአንድ አፍታ የትምህርት ቤቱን ቅጥረ ግቢ አጥለቀለቁት ... በዝምታ ተሞልቶ የነበረው ግቢ በትርምስና ጩኸት ተሞላ...

*　　*　　*

ይዲድያ ከድሬደዋ ጓደኛው የተከራየውን ላንድክሩዘር መኪና አስነስቶ ከትምህርት ቤቱ ቅጥረ ግቢ ወጡ:: በእቅዳቸው መሠረት ከዚህ ቀጥሎ ያለው ፕሮግራም ታሪካዊት ሐረርን በከፊል መጎብኘት ነው::

" ሐረርን በደንብ የምታውቃት ይመስላል" አለው ሚልኪያስ በይዲድያ ቅልጥፍና እየተደሰተ:: በሆቴል ስራ ላይ በጣም ከሚያስፈልጉት ሰዎች መሀከል ስለ ከተማዎች ታሪክ

የሚያውቁ፣ እያንዳንዱን መግቢያ መውጫያውን የሚያስረዱ ፤ በማንኛውም ርዕሰ ሀሪያ ማውራት የሚችሉ ፤ ደማቅ ፈገግታ የማይለያቸው እንደ ይዲድያ ያሉ ፈጣን ሰዎች ናቸው።

" በደንብ ነዋ! ግብፅ የሐረር ከተማን ለአስር ዓመታት በቁጥጥሯ ስር አድርጋ አስተዳድራ እንደ ነበር ሁሉ እኔም ልክ እንደ ግብፅ ሐረር ከተማ ላይ ለአስር ዓመታት ያህል ኖሬያለሁ! በተቻለኝ መጠን የሐረርን መግቢያና መውጫ ሆነ ታሪክ ለማወቅ ጥረት አድርጌያለሁ! ስለዚህ ማንኛውም ጥያቄ ካላችሁ መጠየቅ ትችላላችሁ በነገራችን ላይ ከዚሁ ለመጀመር በሐረር ታሪካዊ እና ዝነኛ ት/ቤቶች መሀከል ጌይ መድረሳ፣ የሼ. አመቤት ልዑል ራስ መኮንን፣ ቀኃሥ(አርበኞች) ት/ቤት ይጠቀሳሉ እንግዲህ ጓደኛችሁ እያስተማረበት ያለው በጣም ታሪካዊ ከሆኑት ት/ቤቶች መሀከል አንደኛው በሆነው ነው" አለ:: ሁሉንም ለማሳየት እየሞከረ::

ካትሪን ቀስ ብላ ከአጠገቧ የተቀመጠውን ሚልከያስን ቆነጠጠችው:: እየሣቀ ተመለከታት::

"ምነው ካትሪ" አላት በግንባር ምልከት::

" እኔም ስለ ከተማዋ መስማት እፈልጋለሁ"

" አ! በጣም ይቅርታ ዋና ዋና ነጥቦችን እተረጉምልሻለሁ" አላት::

ይዲድያ ይበልጥ ዘና እንዲሉ በማለት መኪናው ውስጥ የነበረውን ካሴት ከፈተው፣ የመሀሙድ አህመድ ሙዚቃ...

.... የሐረር ልጅ ነች የአዋሽ ማዶ
ልቤ ተወሰዷል እሷን ወዶ
ልጅቷ አቤት ውበቷ
ሰው ማስደሰቷ
የሐረር ልጅ ነች ወጣቷ
ጆሮል ነው ቤቷ...

" በአሁኑ ሰዓት የሐረር ህዝብ ከ170ሺ በላይ ነዋሪ ይሆናል! የዛሬ ዓመት ማለትም በ1997

ስፔን ባርሴሎና ከተማ ላይ በተደረገው ምርጫ በዩኒስኮ (UNESCO) የሐረር ከተማ 'የሠላም የመቻቻልና የፍቅር ከተማ' ተብላ ተሸልማለች! ለእስልምና እምነት ተከታዮች ደግሞ በዓለም ላይ አራተኛዋ ቅዱስ ከተማ የሚል እውቅና ተቀብላለች:: ፈረንጆች ሐረርን' The City of Saints' እያሉ ይጠሩዋታል:: ይቺ ታላቅ የንግድ ከተማ የሆነች ታሪካዊት ከተማ የእስልምና የክርስትና የፕሮቴስታንት የካቶሊክ... የሁሉ መኖሪያ ስትሆን ብዙዎች የሐረርን ነዋሪዎች እንግዳ አክባሪዎች ፣ ጭንቅ የማይችሉ ፣ ሠላም ወዳዶች ተቻችለውና ተከባብረው የሚኖሩ ህዝቦች ያሉበት ነው ይላሉ:: ሐረር የሚለውን ስያሜ በተመለከተ ሶስት መላምቶች አሉ የመጀመሪያው "ሐርላ" ከሚል የዘር ግንድ መጣ ሲሉ ሁለተኛው "ኤረር" ከሚል ሸለቆ መነሻ ተሰየመ ይላሉ፤ የመጨረሻው "ሐረር" የሚለው ስያሜ በሂጅራ አቆጣጠር በ405 ማለትም የዛሬ 1023 ዓመት ነበር ስያሜውን የተገኘው ለዚህ ስያሜ ዋነኛው ምክኒያት በጨረቃ አቆጣጠር 405 የሚለውን በስሌት መሠረት

ሐ= 5

ረ =200

C= 200

"ሐረር" የሚለው ፍቺ ወይም ፊደል ይሰጣል በማለት ሐረር ብለው የሐረር ታላቅ መንፈሳዊ አባት የሚባሉት ሼክ አባድር ሰይመውታል የሚል ግምት በሰፊት አለ:: በነገራችን ላይ እኚው የሐረር መንፈሳዊ አባት ናቸው ጀጎልን የመሠረቱት..."

ይዲድያ መኪናዋን በቀስታ እያሽከረከረ ስለ ሐረር ከተማ ታሪክ በወፍ በረራ እየነገራቸው ራስ ሆቴልን አልፈው ወደ ራስ ልዑል መኮንን ሐውልት ጋር ደረሱ፤ ሚልክያስም ለካትሪን በቀስታ በኢንግሊዝኛ እየተረጎመ ይነግራታል:: መኪናቸውን ከመንገዱ ጥግ አቁመው ሐውልቱ ስር ፎቶ ተነሱ:: የልዑል ራስ መኮንን ሐውልት ላይ የተቀረፀው ፅሑፍ ተነቃቅሎ ተወስዷል... እናም ለማንበብ በጣም አስቸጋሪ ነው... ሁሉም ይህን ሲመለከቱ በጣም ተበሳጩ በተለይ ካትሪን የታሪክ አስተማሪዋ ዳቪንቺ ያላት ንግግር እንቃጨለባት 'ጥቂሮች የነጮችን ታሪክ እንጂ የራሳቸውን ታሪክ አይወዱም! በሀገራቸው ውስጥ አንድ

ታሪክ ያለው ግለሰብ መታሰቢያ ሐውልት ከተሰራለት ከተቻላቸው ምሽት ላይ ሐውልቱን ያፈርሱታል! ሐውልቱ የማይፈርስ ከሆነ ከሐውልቱ ስር ስለሰውየው ማብራሪያ የሚሰጥ የተቀረፀ ፅሁፍ ካለ ይነቃቅሉታል! ያሐውልት ቢያንስ የከተማ ውበት እንደሆነ ቱሪስቶች እየጎበኙት የገቢ ምንጭ እንደሆነ አይረዱም! አስተሳሰባቸው ሁሉ እኔ ከሞትኩ ሥርዶ አይብቀል እንዳለችው አህያ ነው! ብቻ ጥቂሮች እንደ ቺጋንዚ እንኳን ማሰብ የማይችሉ ደደብ ህዝቦች ናቸው! ለዚያ ነው ታላቁ ፈላስፋ ፕሉቶ ማሰብ ባትችል እንኳን ማሰብ እንደምትችል አስብ ያለው'

ካትሪን በልቧ ፈገግ አለች::

መኪናዋ ቁልቁል ወደ ጀጎል አመራች:: ይዲድያ ስለ ሐረር ማስረዳቱን ቀጥሏል:: በተለምዶ ጫት ተራ የሚባለው ቦታ መኪናዋ ደርሳ እግረኞች በእግራቸው፣ ባለመኪናዎች መኪናቸውን አቁመው እየወረዱ ጫት ለመግዛት ሲራወጡ ግርግሩን ትርምሱን ጫት ሻጮች 'የኔ ጫት ምርጥ ነው! ቶሎ ስለሚያመረቅን ግዙኝ እያሉ' በጩኸት ሲጣሩ... ከፊሎች የገዙትን ጫት አዛው ጥጋጥግ ቆመው ሲቅሙ ሲመለከቱ ሚልክያስ ... ማርያማዊት.. መኑ ... ካትሪን በጣም ተገረሙ:: ካትሪን ስለ ጫት ሰምታለች በአይኑዋ ግን አይታ ስለማታውቅ በጣም ተደነቀች "የሐረርን ስም በግንባር ቀደም ከሚያስጠሩዋት ነገሮች ሁለቱ ጫት እና ቡና ናቸው:: የቡናም የጫትም መነሻ ሐረር እንደሆኑ ታሪክ ያወሳል! እንግዲህ በሐረር ጫት መቃም ብርቅ አይደለም! መዝናኛቸው ነው... እስላሞች ደግሞ ለሀይማኖታዊ ስርዓት ይጠቀሙበታል.. አንዲት ብዙ ሰው የሚያውቃት የኦሮምኛ የቃል ግጥም ትዝ አለችኝ ልበልላችሁ?"

" ደስ ይለናል" አሉት::

'እስቲ ቅሜ ልየው ይህን የጫት ቅጠል
በአሊባሌ አገር ይቅመዋል ግመል
ጫት ላንተ ቢመስልህ የሆነ ቅጠል
ለኔ ሻኛ ነው ያውም የግመል...' ትላለች... ታዲያ ሐረር ውስጥ የሚኖር

ሆነ የተወለደ ሰው ሁሉ ጫት ይቅማል ማለት ግን አይደለም! ቀና ብለው የማያዩት እንዳሉ ሁሉ ያለ ጫት መኖርም የማይችሉ ግለሰቦች በብዛት አሉ! ጥርሳቸው እንኳን ቢያልቅ በሙቀጫ እየወቀጡ ይጠቀሙታል፤ እኔ ራሱ ለሰባት ዓመታት ያህል ቃሚ ነበር የተውኩት…"

ካትሪን የምታየው ነገር በጣም ስለደነቃት ሚልኪያስን ቆነጠጠችው:: ተመለከታት:: የካትሪን የሚያምሩት ዓይኖቿ ጫቶቹ ላይ አነጣጥረዋል::

" አባክህ የተወሰነ ግዛልኝ እኔም መብላት እፈልጋለሁ ምን አይነት ስሜት እንደሚፈጥርብኝ ለማወቅ እፈልጋለሁ"

ሚልኪያስ ሣቀና ውቧን ካትሪንን በትኩረት እየተመለከተ

" አይሆንም ካትሪን! ብዙዎች በጫት ሱሰኛ ሆነው የሚቀሩት ምን ስሜት እንደሚፈጥርብኝ ሞክሬ ልየው ብለው እንደቀልድ ጀምረው ሳያስቡት በዚያው ቀልጠው ይቀራሉ::"

የጫት ተራውን ትዕይንት ለግማሽ ሰዓት ያህል ሲመለከቱ እና ሲታዘቡ ቆይተው ሄዱ… በላይነህ ሆቴል ዘና እያሉ ምሳቸውን ተመገቡ:: ቀለል ያሉ መጠጦችን ወሰዱ:: የተወሰነ እረፍት አድርገው ወደ ጉብኝታቸው ቀጠሉ:: ጀጎል ደረሡ… ገቡ… ይዲድያ ማስረዳቱን ቀጠለ::

"… በርካታ ቱሪስቶች በዓለም ላይ ሊመለከቱዋቸው ከሚፈልጉ በዩኔስኮ እውቅና ከተሰጣቸው ቦታዎች መሀከል አንደኛው ይህ የጀጎል ግንብ ነው:: የጀጎል ግንብን ራሳቸውን ከጠላት ለመከላከልና ለመጠበቅ በአሚር ኑር ኢብን ሙጃሂድ ዘመነ መንግስት በኛ በሀበሻዊያን አቆጣጠር በ1545 አካባቢ የተገነባ ግንብ ነው:: 5 በሮች ሲኖሩት በአማርኛ አጠራራቸው ኤረር በር፣ ሠንጋበር፣ ፈላናበር፣ ሸዋበር፣ ቡዳበር… የሚል ስያሜ አላቸው… 24 መቆጣጠሪያ ማማዎች… ከ46 ሄክታር ስፋት በላይ በሚያካልል መሬት ላይ የሰፈረ ግንብ ሲሆን በአሁኑ ወቅት እስኪ 2000 ሺ ቤቶች እና 360 አቋራጭ መንገዶች በውስጡ ይኖራሉ … የግንቡ ዙሪያ ርዝመት 3344 ሜትር ገደማ ሲሆን በአማካይ 3 ሜትር ከፍታና 3 ጫማ ውፍረት አለው እንግዲህ እንደምታዩት ቤቶቹ በአሠራራቸው ሆነ በቀለማቸው ሁሉም

በጣም ተመሳሳይነት ስላላቸው አንዱን ቤት ከሌላው ቤት ለመለየት እጅግ በጣም አስቸጋሪ ነው… በዚያ ላይ እንዳልኳችሁ 360 አቋራጭ መንገዶች ነው ያሉት…"

ሚልኪያስ ፣ ካትሪን (የምታየውን እየቀረፀች) ፣ መኑ እና ማርያማዊት በይዲይያ አስጎብኚነት ከአንድ ሰዓት በላይ እየተዘዋወሩ የጀጎል ግንብን ለማየት ጥረት አደረጉ…

" እንግዲህ ቤተክርስቲያንም በትልቁ መንደር ውስጥ እንዳለ አይታቹኋል ይህ ቤተክርስቲያን እዚህ እንዴት ተሰራ? ለሚለው ራሱን የቻለ ታሪክ አለው ለማንኛውም በጀጎል ውስጥ ከ82 በላይ መስኪዶች አሉ:: አሁን ደግሞ ሁለቱን ሙዚየሞች እንመልከት በነገራችን ላይ ለመጀመሪያ ጊዜ ሐረርን የተመለከተው ኢንግሊዛዊ ሪቻርድ በርተን የተባለ ግለሰብ ነው:: አንደኛው ሙዚየም የተሰየመው የፈረንሳይ ነጋዴ እና ገጣሚ ነው በሚባለው አርተር ራምቦ ነው … ይህ ሰው አወዛጋቢ ታሪክ አለው ግማሹ ሐረር ውስጥ በሐረር ፍቅር ተማርኮ እዚህ በስሙ በተሰየመው ሙዚየም ውስጥ ለዘመናት ኖረ ይላል! ግማሹ አርተር ራምቦ ነጋዴም ገጣሚም ሳይሆን ሐረር ከተማ ውስጥ ወርቅ እና እንቁ ያለ መስሎዋቸው ወርቅ እና እንቁውን አውጥቶ ለመውሰድ የፈረንሳይ መንግስት የላከው ወስላታ አሳሽ እንጂ የምን አባቱ ገጣሚ ነው ይላሉ… ብቻ ምንም ተባለ ምንም በዚህ ሰው የተነሳ የፈረንሳይ መንግስት እና የሐረር ከተማ ቅርበታቸው ጨምሯል፤ በዚህ ሰው ታሪክ ዙሪያ በኢንግሊዘኛ ፣ በፈረንሳይኛ እና በአማርኛ ቋንቋ መፅሐፍ ተፅፎለታል እሱን ማንበብ የምትፈልጉ ከሆነ መግዛት እንችላለን… ለማንኛውም ሐረር በጣም በጥቂቱ ይህን ትመስላለች በነገራችን ላይ ቅድም አምስት ትላልቅ ዋና ዋና በሮች በሰሜን በምስራቅ በምዕራብ በደቡብ… ማስገቢያ እንዳሉ አይታቹሀል በየቦታው ያሉት አነስ አነስ ያሉት በሮች ደግሞ የጅብ መግቢያ በሮች ናቸው! ሐረር እና ጅብ በጣም የቆየ ዝምድና አላቸው! የአንድ ሳንቲም ገፅታ ናቸው ለማለት ይቻላል… በየዓመቱ አንድ ጊዜ የሚከናወን ሞቅ ደመቅ ያለ ጅብን ገንፎ በቅቤ የማብላት ስርዓትም ቀኑን ጠብቀው ነዋሪዎች ያከብራሉ ከዚው ከአሹራ በዓል ጋር በተያያዘ የተወሰኑ ሰዎች ለጅብ የሚደረገውን ዓመታዊ ሥነ ሥርዓት ቢቀር ወይም ሳይከበር ቢታለፍ ከተማዋን ጅብ ይወራታል ! መውረር ብቻ አይደለም ምሽትን ጠብቆ በየሰው ቤት እየገባ ሰውን ይበላል

ብለው ያስባሉ... ይሠጋሉ... ይፈራሉ... በሌላ በኩል ደግሞ ይህን ጉዳይ በተመለከተ የተወሰኑ ነዋሪዎች ይህን ድርጊት ከባዕድ አምልኮ ጋር ወይም ከጥንቁልና ጋር በማያያዝ ለጅብ የሚደረገው የገንፎ በቅቤ የማብላት ደማቅ የአሹራ በዓል መቅረት አለበት! ጅቦቹም የሚተናኮሉ ከሆኑ በመሣሪያ መገደል አለባቸው የሚል ሀሳብ ያቀርባሉ ... ለማንኛውም ሁላችሁም ፍቃደኛ ከሆናችሁ የመጨረሻ ጉብኝታችን ጅቦችን ማየት፣ ሥጋ ማብላት እና ፎቶ መነሳት የምትችሉበት አጋጣሚ ነው... እሺ ሁላችሁም ለመሄድ ዝግጁ ናችሁ?" አላቸው ይዲድያ ሁሉንም እየተመለከተ:: ሚልክያስ ለካትሪን ስለ ሁኔታው አስረዳት:: የተነገራትን ለማመን ብዙም አልተቸገረችም :: አልሞቃትም:: አልበረዳትም:: ምክኒያቱም ከቢሊየነር አባቷ ኤድዋርድ ጋር ህንድ ሄዳ ህንዳዊያን ለሰው ልጅ በጣም አደገኛ ናቸው ከሚባሉት ከእባብ ጋር ከኮብራ ጋር ሲጫወቱ በሰውነታቸው ላይ ሲጠመጠሙ አይታለች... ፔሩ ውስጥ አንበሳ ከሰዎች ጋር ስጋ ሲመገብ .. አብረውት እያቀፉት ፎቶ ሲነሱ አይታለች... ኮሪያ ውስጥ ውሻ ሲመገቡ ... ታይላንድ ውስጥ ሰዎች ከአዞ ጋር ሲጫወቱ ተመልክታለች ... ስለዚህ 'ሐረር ውስጥ ሰው እና ጅብ አብረው ሥጋ ይበላሉ፣ ከጅብ ጋር ፎቶ መነሳት ይቻላል' ስትባል ብዙም ሳይገርማት ለማየት ተስማማች ... ሙኑ፣ ሚልክያስ፣ እና ማርያማዊትም በሀሳቡ ተስማሙ:: ለአንድ ሰዓት ያህል ቆይተው ሄዱ:: ሁሉም ወደ ተያዘላቸው ሆቴል ተመለሱ:: ሆቴላቸው ገብተው እንደተቀመጡ ሚልክያስ ካትሪንን ጥያቄ ጠየቃት

" ሐረርን እንዴት አየሻት?"

" ደስ ብሎኛል እስካሁን የአገርህን ሶስት ከተሞችን አየሁኝ:: ሶስቱም ከተሞች ላይ ያየሁት ትልቅ ችግር የንፅህና ጉድለት ነው:: በየቦታው ቆሻሻ አያለሁ ይህ ደግሞ በጣም ያስጠላል! ምናልባት ከዓለማችን ውብ ከተማ አንደኛዋ ከሆነችው ፓሪስ ተወልጄ ስላደኩ ሲሆን ይችላል ለንፅህና ከፍተኛ ቦታ እሰጣለሁ በተለይ እዚህ ያየሁት ጀጎል ያላችሁት አስገራሚ መንደር በዩኒስኮ ጭምር እውቅና ተሰጥቶት የከተማዋ አስተዳደር በንፅህና አለመያዙ አነጋጋሪ ነው! በየቦታው ስዘዋወር ቆሻሻ በብዛት አይቻለሁ! ቆሻሻ እና የንፅህና ጉድለት ደግሞ የአንድን ከተማ ውበት እጅግ በጣም ይቀንሰዋል፤ በተረፈ ባየሁት ነገር በጣም

ተደስቻለሁ! አገርህን ኢትዮጵያን እንድመለከት አባቴን አሳምነህ ስላመጣኸኝ በድጋሚ በጣም አመሰግናለሁ:: ከምንም በላይ ደግሞ ለእ ካንተ ጋር የማሳልፋት እያንዳንዷ ሰከንድ ትልቅ ደስታ ትፈጥርልኛለች!" አለችና እቅፍ አድርጋ ሳመችው::

* * *

የትምህርት ቤቱ መምህራን እና የቤተ-መፅሐፍት ሰራተኞች ሁሉ ፈጠን ፈጠን እያሉ ወደ አዳራሽ ገብተው ሞሉ:: እስቸኳይ ስብሰባው ለምን እንደሆነ ለማወቅ ጓጉተዋል::

" ከደቂቃዎች በፊት ሁለት የፈረንሳይ ዜግነት ያላቸው ሰዎች የተቀደሰ ሀሳብ ለተማሪዎች ይዘው መጥተዋል :: ሀሳባቸው ..."

ሁሉንም ነገሩዋቸው::

" በዚሁ መሰረት  እስከ ስምንት ሰዓት ካስተማራችሁ በኋላ ተማሪዎችን ለነገው ፕሮግራም ዝግጅት ግቢውን እንዲያፀዱ እና ከባንዲራው መስቀያ ፊት ለፊት ወንበሮችን አውጥተው እንዲያስተካከሉ አድርጉ:: ለዚሁ ነው አመሠግናለሁ::"

የታሰበው ሁሉ ዘጠኝ ሰዓት ከሰላሳ ደቂቃ ላይ ተጠናቀቀ:: በተሰጣቸው ስልክ መሠረት ደወሉ ፤ አቶ ሁሴን አሉ::

" እሺ ጌታዬ" አለ ሚልክያስ

" 45 ተማሪዎች ናቸው"

" በጣም አመሠግናለሁ! ነገ እንገናኛለን ጌታዬ!"

ራት በልተው ሲጨርሱ አንደኛ፣ አንደኛ ለወጡት አስራ አምስት ተማሪዎች 500 ብር ... ሁለተኛ ሁለተኛ ለወጡት አስራ አምስት  ተማሪዎች 400 ብር እና ለተቀሩት 15 ሶስተኛ ሶስተኛ ለወጡት ተማሪዎችም 300 ብር ለእያንዳንዳቸው ለመስጠት ወስነው የተቀረውን አራት ሺ አምስት መቶ ብር እየቆጠሩ ፖስታ ውስጥ አስገቡ:: ባጠቃላይ 500x15=7500 ብር 400x15=600 ብር 300x15=4500 ብር 18,000 ብር ወጪ አደረጉ::

አራተኛ ጓደኛቸውን ነገ ነግቶ እስከሚያገኙት

መኑ ...

ሚልክያስ...

ማርያማዊት

በ

ጣ

ም

ጓ

ጉ

::

# 13

# ቀን አስራ ሶስት

ከጠዋቱ 3፡25 ደቂቃ ሆነ፡፡ ከፊት ለፊት ወንበሮች መምህራን ተቀምጠዋል፡፡ ከእነርሱ ኋላ ተማሪዎች ሁሉ ግጥም ብለው ተቀምጠዋል፡፡ ከመምህራኑ አጠገብ ሁለት አግድም ወንበሮች ክፍት ሆነው ተቀምጠዋል፡፡ በተባለው ሰዓት የእነ ካትሪን መኪና መጥታ ግቢው ውስጥ ገባች፡፡

አቶ ሁሴን በፈገግታ ተቀብለዋቸው በተዘጋጀላቸው ቦታ ላይ አስቀመጧቸው፡፡ መምህር ሙሉጌታ መነጋገሪያ እያስተካከለ ስለነበር የመጡትና እንግዶች አላየም፡፡

እንደታቀደው 4፡00 ሰዓት ሲሆን አቶ ሁሴን አሊ መድረኩ ላይ ወጡ፡፡ ተማሪው ሁሉ ስለሚያከብራቸው እና ስለሚፈራቸው ብድግ ብሎ አጨብጭቦ ተቀበላቸው፡፡

" አመሠግናለሁ ተቀመጡ!!"

ተማሪው ሁሉ ተቀመጠ፡፡ ሁለት ደቂቃ ያህል የፈጀውንና ማታ የፃፉትን ፅሁፍ አንብበው ጨረሱ፡፡ መማር ራስንም፣ ሀገርንም መጥቀም እንደሆነ፣ ሀገሪቱ እንደምትፈልጋቸው፣ ሕልማቸውን ሁሉ እውን ሊሆን እንደሚችል... ጎበዝ ተማሪን ሁሉም እንደሚወድና እንደሚያከብር ነበር ያነበቡት፡፡ በንባባቸው መጨረሻ በቃላቸው "አሁን በቀጥታ ወደ ሽልማቱ ስነ ስርዓት ነው የምናመራው ከየክፍላቸው ሶስተኛ ለወጡ ተማሪዎች ሽልማቱን መምህር ሙሉጌታ ይሰጥልናል" አሉ፡፡

መምህር ሙሉጌታ ግር አለው፡፡ እሱም ሆነ ሌሎች መምህራን የጠበቁት ከእንግዶቹ አንደኛውን ነበር፣ ግር እንዳለው መድረኩ ላይ ወጣና ፖስታውን አንስቶ ተራ በተራ በስማቸው መሠረት እየተጠሩ ሲመጡ በደማቅ ፈገግታ ተሞልቶ ከልቡ አጥብቆ እየጨበጣቸው ሰጣቸው፡፡ ሲጨርስ ወደ ነበረበት ቦታ ተመልሶ ተቀመጠ፡፡

ሁለተኛ ለወጡት ራሳቸው አቶ ሁሴን አለ. ሽልማቱን ሰጡ፡፡ ሲጨርሱ "አንደኛ ለወጡት ሽልማት የምትሰጥልን ከፈረንሳይ አገር ድረስ የመጣችው እንግዳችን ካትሪን ናት" አሉ፡፡ አማርኛ ስለ ነበር አልሰማችም፡፡

" አንቺን ነው ካትሪ" ብሎ ሚልከያስ ሲነግራት ተነስታ ወጣች፡፡ እሷን የመሰለች ጣጣዋን የጨረሰች ውብ ፈረንጅ አብዛኛው ተማሪ ሆነ መምህራን አይቶው ስለማያውቁ አይናቸው እስከሚወጣ! የካትሪንም የቆዳ ቀለም እስከሚቀየር ድረስ ይመለከቷት ገቡ፡፡

ሁሉንም ከመጨበጥ ባሻገር እቅፍ እያደረገች እና እየሳመቻቸው ሰጥታ ጨረሰች፡፡ አቶ ሁሴን በአባትነት ፍቅር መጥተው አቀፏዋትና ወደ መምህራንና ተማሪዎች እየተመለከቱ መናገር ቀጠሉ...

"በእጄ ላይ አንድ ታሪካዊ ፎቶ ግራፍ አለ፡፡ ከዛሬ አስራ ስድስት ዓመት በፊት የተነሱት ፎቶ ግራፍ ነው፡፡ እነዚህ አራት ጓደኛሞች ከፍተኛ መተሳሰብ ፣ ፍቅር፣ እና በህብረት ያጠኑ ነበር፡፡ አንዱ ያወቀውን ለሌላው ያሳውቅ ነበር! አንዱ ሲያጠፋ አንደኛው ይመክረው ነበር! የሰው ልጅ ማህበራዊ እንስሳ ነው፡፡ የፈለገ እውቀት ፣ የፈለገ ጥበብ፣ የፈለገ ሀብት ቢኖረን ከማህበራዊ ሕይወት ውጪ መኖር አንችልም! በሕይወት ዘመናችን ላይ ማህበራዊ ሕይወት ግዴታ ነው! መተባበር ፣ መረዳዳት ግዴታ ነው! ጓደኛ መያዝ ግዴታችን ነው! ጓደኛ ማለት መስታወት ማለት ነው! እውነተኛ ጓደኛ ከቤተሰብ ይበልጣል! እውነተኛ ጓደኛ ለቤተሰብ እንኳን መናገር የፈራነውን ችግር የሚካፈልልን ነው! እውነተኛ ጓደኝነት መሠረቱ ጥቅም አይደለም! በንፁህ ልብ የሚመሠረት ጠንካራ ሰንሰለት ነው! እውነተኛ ጓደኝነት በገንዘብ ሊገዛ የማይችል ጠንካራ የልብ መናበብ ያለበት ግንኙነት ነው፡፡ እኔንጃ እናንተ ከጓደኞቻቹ ጋር ወደ ፊት ስንት ጊዜ እንደምትዘልቁ? አንድ ሰው ግን ለጓደኞቹ ሲል የጓደኞቹ ፍቅር አላስቀምጥ ብሎት ከፈረንሳይ ሀገር ድረስ መጥቶ ዳግም ተገናኝተዋል፡፡ እስቲ በሞቅ ያለ ጭብጨባ ተቀበሏቸው፡፡"

በእንግድነት ተቀምጠው የነበሩት ሰዎች መድረክ ላይ ወጡ፡፡ መምህር ሙሉጌታ የሚያየውን ማመን አቃተው፡፡ሚልከያስ ከፈረንሳይ ሲነሳ ሁሉንም በሕይወት

እንደሚያገኛቸው ልቡ ነግሮት ነበር:: እንዳሰበው ስለሆነ ፈጣሪውን አመሰገነ::

የሚልከያስ እንባ ቅርብ ነው:: ለደስታውም ያለቅሳል፤ ለሀዘኑም ያለቅሳል...አሁንም ሶስተኛ ጓደኛውን ሲመለከት እንባው ዝርግፍ አለ:: መኑ እና ማርያማዊትም የሱን ለቅሶ ሲመለከቱ አለቀሱ::

መምህር ሙሉጌታ እንባውን እያበሰ ሳያስበው ብድግ ብሎ መድረክ ላይ ወጣ:: ሶስቱንም ተራ በተራ ጭምቅ እያደረገ አቀፋቸው:: ተማሪዎች ... አስተማሪዎች በስፍራው የነበሩት ሌሎች ሠራተኞችም በአድናቆት እና በመገረም እየተመለከቷቸው ሞቅ ያለ ጭብጨባ ለገሷቸው::

ሳቅ

ብቻ

ሆነ...

# 14

## ቀን አስራ ስድስት...

ሐረር ሁለት ተጨማሪ ቀናት ቆይተው አዲስ አበባ ተመለሱ፡፡ ከአዲስ አበባ አንድ ቀን ቆይታ በኋላ ሙሉጌታ በስራ ምክኒያት ስላልተመቸው መኑ፣ ማርያማዊት፣ ካትሪን፣ ሚልክያስን እና ይዲድያ በፕሮግራማቸው መሠረት ባህርዳርን ... አክሱምን... ላሊበላን ... በኢትዮጵያ አየር መንገድ በመጓዝ ... በመኪና ጉዞ ደግሞ ወንዶገነትን እና አዋሳን ጎበኙ፡፡ ካትሪን እና ሚልክያስ የኢትዮጵያ ቆይታቸው በደስታ እና በሳቅ እንደተሞላ ሳያስቡት ሀያ አምስተኛው ቀን ደረሰ፡፡

ወደ ፈረንሳይ ለመመለስ ትኬት በኢትዮጵያ አየር መንገድ ከቆረጡበት ቀናት ውስጥ አምስት ተጨማሪ ቀናት ብቻ ቀራቸው፡፡

# 15

ማርያማዊት እጅግ የበዛ ሀጢያት ከነበረበት አስቀያሚ ሕይወቷ ፍፁም ሳታስበው መጥቶ ስለ አዳናት ሰው ‛አዲስ ሕይወት አዲስ ቤት' ብላ በተከራየችው መኖሪያ ቤቷ ውስጥ ሆና እያሰበች ተቀምጣለች::

እጅግ በጣም ፈጣን ውሳኔ ነው የወሰነችው:: ቤቷን ለማንም ሳታሳውቅ ወዲያው ቀየረች:: ቤቷን የቀየረችው ጓደኞቿን ላለማግኘት ነው::

ጠዋት ይሰባሰባሉ:: ስለማታ አዳራቸው ያወራሉ::

"ቪያግራ ወስዶ ነው መሰለኝ ሌሊቱን ሙሉ ሲያፈጋኝ አያድርም እንዴ... ላግባሽና ላስቀምጥሽ ብሎኝ ... ቁላዬን ካልጠባሽልኝ ብሎኝ እንቢ ብዬው ፊቴን እንዴት እንዳደረገው አያችሁ ይሄ የብዳታም ልጅ ... በቂጥሽ ወሲብ ላድርግ ብሎኝ እንቢ ስለው እንዴት እንደነከሰኝ አያችሁት ይሄ የሴት ልጅ ... ያ ቻይናዊ ተመልሶ መጣ እኮ ..."

መሰል ወሬዎችን ነው የሚያወሩት ______________________________________

______________________________________________________________

______________________________________________________________

ስለ ሕይወቷ ስታስብ ግርም ይላታል:: በአንዲት ሴኮንድ ሕይወቷ ሊጠፋበት የሚችልበት ስራ ላይ ነበር የተሰማራችው:: እውነተኛ ፍቅር፣ እውነተኛ ጋብቻ ያለ አይመስላትም:: ከወጣት እስከ ሽማግሌ... ታላላቅ ባለስልጣናት... ወይ ጉድ ያላጋጠማት ወንድ የለም:: በጣም የሚገርማት ሶስት ገጠመኝ ግን አላት:: የመጀመሪያው... ቀን ከአንድ ጣሊያናዊ ባለስልጣን ጋር ሂልተን ሆቴል ነበረች:: በዚያው ሰዓት ሞቅ ያለ ሠርግ በሆቴሉ ውስጥ ነበር:: ታዲያ በሁለተኛው ቀን ማታ አንድ ወጣት ይመጣል:: አብዛኛውን ጊዜ ከውጭ ሀገራት ሰዎች ጋር ነው የወሲብ ኪራይ የምትፈፅመው:: ታዲያ የዚያን ቀን ስራ ይጠፋና

ከዚሁ ወጣት ሀበሻ ጋር ተስማምታ ትወጣለች:: ወሲብ ለመጀመር እየተንቀዠቀዠ አልባሳቱን ሲያወልቅ ትኩር ብላ እየቸውና ደንግጣ ተመለከተችው

" ምነው ቆንጆ?"

" ከሁለት ቀን በፊት ሂልተን ያገባኸው ሙሽራ አይደለህም እንዴ?"

" ነኝ"

" ምን ተፈጠረ ታዲያ?"

" ምን አገባሽ ብር ነው አይደለም የምትፈልጊው ይኸው ብርሽ ይልቅ አውልቂ"

" አይሆንም!"

ብሩን መልሳ ሰጠችው:: በጥፊ ሞልቶባት ወጣ:: ሁለተኛው ገጠመኟዋ ደሞ አንድ ማታ የተከሰተ ነው:: አንዲት እንደሷ የምታምር ወጣት ትመጣና አንድ ከቤቱ መውጣት የማይችል ባለሀብት ጋር ልውሰድሽ በማለት ሞቅ ያለ ብር ትከፍላታለች:: መኪናዋ ውስጥ አስገብታት እያዋራቻት ላምበረት ወደሚገኘው ዘመናዊ ቪላ ቤት ውስጥ ታስገባታለች:: ሻወር እንድትወስድ ታዛታለች:: ማርያማዊት ሻወር ወስዳ ጨርሳ ስትመጣ ወጣቷ ራቁቷን አልጋው ላይ ተኝታለች:: እንዳየችያት ከአልጋው ላይ ተነስታ በፈገግታ ተሞልታ ትቀርባታለች::

" ጨረሽ የኔ ውብ ?"

ፈገግ ብላ ዝም አለች:: መጥታ ፒጃማዋን አውልቃ ታሻሻት ገባች:: ትስማትም ጀመር::

" ምን... እያደረግሽ ነው እህት ሰውየው የት አለ?"

"Oh ... God ... you have a Lovely body... Please touch me ... please..."

ማርያማዊት ወዲያው ወጣቷ ሌዚቢያን መሆኑዋን ተረዳች:: እንደምንም ተማፅናት እና አሳምናት ብሩዋን መልሳላት ከቤቷ ሮጣ አመለጠች:: ማርያማዊት እስከ ዛሬ ድረስ ከማንም ወንድ ጋር ያለ ኮንዶም ወሲብ አድርጋ አታውቅም! ብዙ ጊዜ ተመርምራለች... ከHIV ነፃ ነች... የመጨረሻው የማትረሳው ገጠመኝ ደግሞ አንድ ምሽት

እጅግ በጣም እርጋታ የተሞላበት ሰው ጋር ሂሳብ ተደራድራ ጨርሳ ከጠየቀችው በላይ እጥፍ ከፍሎዋት ቤቱ ወሰዳት:: የሚያምረው ቤቱ ውስጥ ገባች:: ቤቱን በሙሉ ቆልፎ ከጨረሰ በኋላ እየሳቀ መጣና አጠገቧ ተቀመጠ::

"ከዚህ ቤት በሕይወት ለመውጣት የምትፈልጊ ከሆነ ያለ አንዳች ጥያቄ እኔ ብቻ የምልሽን መፈፀም ነው! እንቢ የምትይ ከሆነ " አላትና ከጀርባው የነበረውን ሽጉጥ ጠረጴዛው ላይ አስቀመጠ.. ማርያማዊት ልቧ በፍርሀት ተሞላች:: ምን ማድረግ እንዳለባት እያውጠነጠነች በዝምታ ተመለከተችው...

ሰውየው አልባሳቱን አወላለቀና መሬት ላይ ራቁቱን በጀርባው ተጋደመ:: ወደ ላይ አፍጥጦ እየተመለከታት "የኔ ውብ አትፍሪ ብዙ አላስቸግርሽም! ልብሶችሽን አውልቂና እንደቆምሽ ሽንትሽን በአካላቴ ላይ አፍስሽው!! አርሽን እሪና ሰውነቴን ላይ ቀቢኝ" ከስንት ጥረት በኋላ ማርያማዊት እየዘገነናት... እየቀፈፋት የታዘዘችውን ፈፀመች:: ያዘዛትን ስትጨርስ ሰውየው ተነስቶ ሰውነቱን ታጠበ፤ በደስታ እንደተሞላ ወደ ማርያማዊት መጥቶ ' የ ኔ ውብ በጣም አመሠግናለሁ! እስከ ዛሬ ከመጡት ሴቶች ሁሉ ያንቺ ሽንት እና አር መዐዛው ልዩ ነው! አሁን ወደ ሆቴልሽ ልውሰድሽ ወይስ እዚሁ ታድሪያለሽ?'

ማርያማዊት በፍጥነት

' አመሠግናለሁ ወደ ሆቴል ብትመልሰኝ ደስ ይለኛል' አለችው:: ሰውየው በደስታ እንደ ተሞላ ማርያማዊት የፈለገችውን ፈፀመላት... ማርያማዊት ምሽቱን ሙሉ እያስታወካት አደረች... ከዚያች ቀን በኋላ የወንዶች የግል ቤታቸው መሄድ መፍራት ጀመረች... ማርያማዊት ብዙም መጠጥ አትጠጣም እንጂ የመጠጥ ሱሰኛ ብትሆን ብዙ ጉድ ያጋጥማት ነበር ...

ሰሞኑን ስልኳንም ሆነ ብላ ታክሲ ውስጥ ጥላው ስለወረደች ከማንም ጋር አልተገናኘችም:: መገናኘትም ደሞ አትፈልግም!!

አሁን አዲስ፣ ሕይወት አላማ ያለው ሕይወት ፣ ከሀጢያት የነፃ ሕይወት መኖር እንዳለባት ተሰማት:: በመሬት ላይ የምትወዳቸውን ቤተሰቦቿን አጥታለች:: አሁን ግን ተፅናናች:: ሶስት ጓደኞቿን ዳግም አግኝታለች! አሁን ብቸኛ አይደለችም!!

ወደ ኋላ የትዝታ መነፅር ወሰዳትና አምስተኛ እና ስድስተኛ ክፍል ላይ አስቀመጣት:: ምክኒያቱን ባታውቅም ሴት ልጅ ከወንድ ልጅ ቀድማ ስለፍቅር እንደምታውቅ ስምታለች:: ሴት ልጅ ፍቅር በማወቅ ከወንድ ሶስት እጥፍም እንደምትበልጥም አንብባለች ... ገና አምስተኛ ክፍል እያለች ትላልቅ የሥነ ልቦና መፅሐፍትን ታነብ ነበር:: በተለይ የሥነፆታ ሳይኮሎጂ መፅሐፍትን... የዚያ ተፅዕኖ ሳይሆን አይቀርም ገና በልጅነቷ ነበር ፍቅር ልቧን ያንኳኳው ... ከሙኑ እና ከሙሉጌታ ይበልጥ ከጓደኝነትም በተለየ ስሜት ሚልክያስን ትመለከተው ነበር::

ትህትናው ደስ ይላታል::

አሳሳቁ ደስ ይላታል::

ፀባዩ ደስ ይላታል::

ብዙ ሰዓት የመናገር ሳይሆን የማዳመጥ ችሎታውን ትወድለታለች::

'ለምንድነው ግን ብዙ የማታወራው' ትለው ነበር::

'ብዙ የሚያወራ በትንሽ ቃላት ሀሳቡን ማስረዳት የማይችል ሰው ነው' ይላት ነበር:: ከምንም በላይ አስተሳሰቡን ትወድለታለች::

'የሚያስደስትህ ነገር ምንድ ነው?' ትለው ነበር::

'ሰዎች ደስ ሲላቸው ማየት በጣም የሚያረካኝ ነገር ነው' ይላት ነበር... ከማንም በላይ የሚያበረታታት እሱ ነበር::

'ማርያማዊት እውቅ ጋዜጠኛ ትሆኚያለሽ! ማንም የልቡን መሻት ሳያገኝ ሕይወቱ አታልፍም! ስለዛሬ ሳይሆን ስለ ነገ ማሰብ ነው ያለብሽ' ዘወትር ይላት ነበር:: ይህ አባቱ ሁሌ የሚነግሩት ንግግር ነበር::

በልጅነት ንፁህ ልቧ አፈቀረችው:: እሱም በልጅነት ንፁህ ልቡ አፈቀራት! ግን አፈቃቀራቸው ለየቅል ነበር:: እሷ ኢሮስ የተባለውን ፍቅር ነው ያፈቀረችው እሱ በእህትነት በጓደኝነት ነበር የሚያፈቅራት... ለመጀመሪያ ጊዜ የፍቅር ምንነት ጥያቄ ያቀረበችለትም ለእሱ ነበር::

'ፍቅር የሚባለው ግን ምንድ ነው' 'ሰባተኛው የስሜት ሕዋስ ነው! ጊዜን የሚያሳጥርልሽ! ደስተኛ የሚያደርግሽ! ጥሩ ነገር እንድትሰሪ የሚያደርግሽ! የመኖር ጉጉትሽን የሚጨምርልሽ ነገር ነው ከአንድ የፍቅር መፅሐፍ ላይ እንዳነበብኩት' ስለ ዕድሜዋ አሰበች:: ሰላሳ ሊሞላት ሁለት ዓመት ብቻ ነው የቀራት:: ትርጉም አልባ ሀያ ስምንት ዓመታት... አሁን ግን ከሀያ ስምንት ትርጉም አልባ ዓመታት አንድ ዓመት ትርጉም ያለው ሕይወት እንደሚሻል አወቀች:: ማን ነበር ዘላለም ውሻ ሆኖ ከመኖር ለአንድ ቀንም እንኳ ቢሆን አንበሳ ሆኖ መሞት የተሻለ ነው ያለው??

ለመኖር ወሰነች:: የልጅነት ሕልሟ የማይሳካበት መንገድ እንደሌለ አሰበች:: ወደ ጋዜጠኝነት የሚያደርሳትን ትምህርቷን በመጪው ዓመት ለመጀመር ለራሷ ቃል ገባች:: ከዚያ የራሷ ጋዜጣ ይኖራታል... በተለይ አክሱም ከሚልክያስ ጋር ያወሩት አንቃጨለባት:: ይዲድያ ለመኑ፣ መሉጌታ እና ካትሪን ስለ አክሱም ሐውልቶች እያስረዳቸው ነበር... ሚልክያስ እና ማርያማዊት ለብቻቸው በቀስታ እየተከተሏቸው ነበር:: ድንገት ሚልክያስ ሳቀና "የአክሱም ሐውልትን ስትመለከቺ ምን ትዝ አለሽ?" አላት

" እኔንጃ ..." አለችው ማርያማዊት በፍቅር አይን ሚልክያስን እየተመለከተችው "ስድስተኛ ክፍል አስማማው ጫኔ...አስታወስሽው...?"

" አ! ..." አለችና በሳቅ ተንከተከተች:: ትዝ አላት:: ቁጠኛ የነበረው የታሪክ አስተማሪያቸው ስለ አክሱም ሐውልቶች እያስተማራቸው ነበር:: 'ልጆች የአክሱም ሐውልት ቅርፁን ስትመለከቱ በተለይ ጫፉ ላይ የወንድ ብልት መልክ አለው ይህ ለምን ይመስላቹዋል? ' ሲል ይጠይቃል... አስማማው በፍጥነት ሱሪውን ዝቅ አደረገና "ቁላውን" ተመለከተ... እውነትም ይመሳሰላሉ ... ተማሪው በአስማማው ድርጊት በሳቅ ተንከተከተ...

" ማታ አንድ ሀሳብ ስላንቺ እያውጠነጠንኩ መጥቶልኝ ነበር ብነግርሽ ደስ ይልሻል?"

" በጣም እንጂ!!"

" ሁለት ነገር አስቤ ነበር:: ትላንት የኛ አይደለም! ነገ ግን የኛ ነች! ከዚህ በኋላ ደስተኛ ህይወት መኖር ያለብሽ ይመስለኛል... እንደ ሀሳብ የማቀርብልሽ ዳግም ሁሉን ነገር

በቀሲታ ብታስቢ የሚሳካልሽ ይመስለኛል፣ ስለዚህ አስፈላጊ ከሆነ ወደ ፈረንሳይ ልወስድሽ እችላለሁ... ወይም ደግሞ ያን ሕልምሽን እውን ለማድረግ ለምን እንደገና ቢያንስ ለማስታወስ እንዲረዳሽ ከአስራ አንደኛ ከፍል ጀምረሽ ለመማር አትሞክሪም? በእርግጠኝነት ዩኒቨርስቲ እንደምትገቢ ውስጤ ይነግረኛል... ካልሆነ በግል ስለ ጋዜጠኝነት የሚያስተምር ኮሌጅ ካለ አትማሪም... የትኛው ሀሳብ የተሻለ ነው?"

ማርያማዊት ምንም ሳትናገር ዘላ እቅፍ አደረገችውና ሳመችው::

" በጣም ነው የማመሠግነው ሚልክያስ!! ከአስራ አንደኛ ከፍል ጀምሬ እማራለሁ! የልጅነት ህልሜን እውን አደርገዋለሁ"

"በማንኛውም ነገር አጠገብሽ ነኝ!!"

የመኖር ጉጉቷ ጨመረ:: የማታውቀው የሚያነቃቃ ስሜት መጥቶ ሰውነቷን አነቃቃው! ሕይወት ውሳኔ እንደሆነች አወቀች:: እናም ወሰነች:: ትርጉም ያለው ሕይወት ለመኖር... ዘንደኪ!! በመሬት ላይ ማንም ያለ ምክኒያት የተፈጠረ የለም! ማንም ሰው የተፃፈለት የህይወት ዕጣፋንታ የለውም! ሁሉም ሰው የራሱን የሕይወት ዕጣፋንታ ራሱ ይፅፈዋል! ራሱ ይወስነዋል!... ሕይወት የምርጫ ጉዳይ ናት! ሕይወት የውሳኔ ጉዳይ ናት! ታዲያ በሕይወት ጉዞ! በዘንደኪ! የሰው ልጅ የልብ መሻቱን ለማሳካት ሲሮጥ ፈተና... እንቅፋት... ግራመጋባት.. ይደቀንበታል... ያን ፈተና ያን እንቅፋት ያን ግራ መጋባት ... ያን ውጣ ውረድ .. ታግሎ ማሸነፍ እንዳለባት አሁን አወቀች:: ትምህርቷን ስትጨርስ ... የምታወጣው የጋዜጣዋ ርዕስ "እ... ዘንደኪ" እ-ሕይወት የሚል መሆን እንዳለበት ወሰነች::

በጣም የገረማት ግን የዛሬ አስራ ስድስት ዓመት የነበራት ስሜት አይነት አሁንም ከአስራ ስድስት ዓመት በኋላ ሚልክያስ ራሱን "ሚልክያስ እኮ ነኝ" ብሎ ካስተዋወቃት ሴኮንድ ጀምሮ ዳግም ማገርሸቱ ነው:: ስታየው የልብ ትርታዋ አመታት ፍጥነት ይጨምራል ... አጠገቡ ስላለችው ትንሽዬ ልዕልት ስታስብ ደግሞ የልብ ትርታዋ አመታት ቀዝቀዝ ይላል... ሐረር እየሄዱ ሳለ መንገድ ላይ እንደ ቀልድ ጥያቄ አነሳች::

"ካትሪን ደስ የምትል ልጅ ነች" አለችው

"በጣም ጥሩ ልጅ ናት ... አምስት ዓመት ሆነን አብረን ከቆየን፤ የአሊቃዬ ልጅ ናት" አላት

" ስንት ዓመቷ ነው?"

" 17 ናት!"

በግልፅ 'ምንህ ናት' ብላ አልጠየቀችውም ፤ ለመጠየቅም በጣም አስፈራት:: ለማስተዋል እንደሞከረችው ደሞ ፍቅር እንደ ያዛት ለማወቅ ችላለች:: ምክንያቱም ተግባሮችዋ ሁሉ ይህን የሚያሳብቁ ነበሩ:: ሚልኪያስ ግን አንዳች የተናገረው ነገር የለም.. ያወቀውም ነገር የለም...

ወደ መጣበት ፈረንሳይ ከአምስት ቀናት በኋላ የሚያመራ መሆኑን ስታስብ ደግሞ ከሰውነቷ ላይ አንዳች ነገር ይቀነሳል ወይንም አንድ አግርሽ ይቆረጣል እንደተባለች ስውነቷን የሆነ ነገር ውርር አደረጋት:: ዓይኑን በብዛት እስከሚሄድ እንኳ ማየት እንዳለባት ወስና ተቀምጣበት ከነበረው ወንበር ላይ ተነሳች:: ባርባር አያላት ...

ስለ ሕይወት ስታስብ ግን በወናው ቤት ውስጥ ማንም ባይሰማትም ረጅም ሣቅ ሳቀች... ነገ የሚኖራትን መልካም ሕይወት እያሰበች...

# 16

# ቀን ሀያ ስድስት ...

ሚልከያስ ለልምዱ ልውውጥ ከአስተዳደሩ ጋር የነበረውን አጠር ያለ ቆይታ ጨርሶ ወደ ካትሪን እያመራ ነው:: በሩ ጋር ደርሶ ሳታየው ከኋላዋ ሊያስደነግጣት አሰቦ ቀስ እያለ ... እየተራመደ... እያደባ ሳለ ከካትሪን አጠገብ የነበረው ሞባይል አንቃጨለ:: ካትሪን በፍጥነት አነሳችው::

" ቦንዡር ሱዛን"

" ቦንዡር ካትሪን"

" ማታ ደውየልሽ ተኝተሽ ነበር?"

"ምነው ሆነ እንዴ?"

" አልሆነም! የማላውቀው ፍርሀት መጥቶ ይወረኛል! ማፍቀሬን አውጥቼ ለመግለፅ ቃላት እና ድፍረት ራቀኝ! ምክኒያቱ ሚስጢር ነው የሆነብኝ ብቻ የሆነ የተለየ ስሜት ውስጥ ነኝ"

"ካትሪ መፍራት የለብሽም! ለማንኛውም መቼ ነው የምትመለሱት?"

"ከሶስት ቀናት በኋላ እንመጣለን"

" ማታ እደውላለሁ ካትሪ"...

"እመሠግናለሁ ቻው"

ሚልከያስ ሰውነቱን የሆነ ነገር ውርር አደረገው:: ተመልሶ ወጣና በጣም ረዘም ያለ አየር ስቦ ተመለሰ:: ገና ሲገባ ኮቴውን ሰምታ በፈገግታ ተሞልታ ዞር አለች::

" ተቀይሚያለሁ"

"ምነው" አላት ቀዝቀዝ ባለ አነጋገር::

"እንደዚህ ፕለኸኝ ትጠፋለህ የሚል ግምት አልነበረኝም"

"ይቅርታ ካትሪ"

" ይቅርታህን ተቀብያለሁ" አለችው::

"ማርያማዊት" ብሎ መጥራት ስለሚያቅታት 'ማርያም እያለች ነው የምትጠራት::

" ማርያም ጋር ደውላ" አለችው:: ከማርያማዊት ጋር ተስማምተዋል:: ከከባቻው ገጥሟል! ገና ስታያት ነው የወደደቻት:: ታሪኳን ስትሰማ ደሞ ይበልጥ ወደደችያት::

ምንም ሳይናገር ዝም ብሎ በሚመረምር አስተያየት የሚያምሩትን አይኖቿን ትኩር ብሎ ተመለከታት:: ውሃ ሆነች!!

" ምነው ሚኪ እንደዚህ በጣም በትኩረት አይተኸኝ አታውቅም?"

" ሱዛን ደውላ ነበር?" አላት::

" አ! ሰላም ብላሀለች ግን ለምን ጠየከኝ" መዋሸትም ማስመሰልም የማይችለው ሚልኪያስ ዝም ብሎ ተመለከታት:: ከኔ ፍቅር ይይዛታል የሚል ሀሳብ ጨርሶ አልነበረውም:: የሀቁን መጨረሻ ግን ስልክ ስታወራ ድንገት ሰማ! ምን ማድረግ እንዳለበት ግራ ገባው፡ አዕምሮው ላይ ብዙ ነገር ተመላለሰ:: የሩቁን ለማየት ሞከረ ... ምንም አልታየውም:: በእርሱና በካትሪን መሀከላቸው ያለው ጓደኝነት አሁንም ወደ ፍቅር እንዲለወጥ አይፈልግም... ካትሪንን ያደንቃታል... ካትሪንን ይወዳታል::

ለካትሪን እንደ እህትነት ያለ ልዩ ስሜት አለው:: እነዚህ ነገሮች ግን ወደ የፆታዊ ግንኙነት ሆነ ወደ ፍቅር እንዲለወጡ አይፈልግም... ልቡ ውስጥ በአሁኑ ሰዓት ለማንም የሚሆን የፍቅር ስሜት የለውም ... እስከዛሬዋ ቀን ድረስ ለመጀመሪያ ጊዜ ሳያስበው ከንፈሩን የሳመችው የልጅነት ጓደኛው ማርያማዊት ብቻ ነች፤ ትላንትም ከዘመናት በኋላ ከአስራ ስድስት ዓመታት በኋላም በአካል ሲያገኛት ልቡ ውስጥ ያለው ያ ትላንት የነበረው የንፁህ ጓደኝነት... የንፁህ እህትነት ፍቅር እንጂ የፆታዊ የተለየ ፍቅር ጨርሶ አይደለም... ካትሪንንም የሚወዳት ለሙሉ! ለሙሉጌታ፡ ለማርያማዊት ባለው የጓደኝነት ስሜት አይነት ብቻ ነው ... እስከ ዛሬዋ ቀን ድረስ ከማንም ሴት ጋር ወሲብ አላደረገም... እስከዛሬዋ ቀን

ድረስ ለማንም ሴት ልቡን አልሰጠም… ልቡን በፍቅር ያንበረከከች ሴት የለችም … ፍቅረኛ ለመያዝ ሆነ ወሲብ ለመጀመር ብዙም አይጨነቅም… አሁን ያለው ብቸኝነት! አሁን ያለው ነፃነት ተመችቶታል… በተለይ በሚቀጥሉት ዓመታት ለማሳካት ላስቀመጠው ትልቅ እቅዱ ከፍቅር ነፃ መሆኑን በጣም ይፈልገዋል… በእርግጥ ምክኒያቱን ሊረዳው ባይችልም ሰሞኑን ኢትዮጵያ ከመጣበት ቀናቶች አንድ ሁለት ቀናት ሂላሪ ትዝ ብላው ነበር… በተለይ አስማታዊ ፈገግታዋን አስታውሶ ነበር… በመሬት ላይ ማንም ሰው ከአጠገቧ እንደ ሌለ አስታውሶም ነበር… ስለካትሪን… ካትሪን ከኔ ፍቅር ይይዛታል ብሎ በጭራሽ አላሰበም፡፡ እናም በመሀከላቸው የተፈጠረው ደስ የሚል ሕይወት… ደስ የሚል መተሳሰብ… ደስ የሚል ጓደኝነት በዚህ ፍቅር የተነሳ እንዳይበላሽ ምን ማድረግ እንዳለበት ማውጠንጠን ያዘ… ለጊዜው ግን ሀሳብ አልመጣልህ አለው… ብቻ የሆነ ነገር ተጠቅሞ የካትሪንን ሀሳብ ማስቀየር እንዳለበት አዕምሮው በጣም እንቃጨለበት፡፡

ዝም ሲላት መጥታ ከአጠገቡ ተቀመጠች፡፡ በረጅሙ ተነፈሰ፡፡ አይኑዋ ላይ የቅንድቧ ፀጉር ተነቅላ አይንዋ ውስጥ ልትገባ ስለ ነበር አነሳላት፡፡

"ድንገት መጥቼ ከፍልሽ ውስጥ ልገባ ስል ከሱዛን ጋር ያወራሽውን ሰምቻለሁ"

" ም…" ብላ ዝም አለች፡፡

ደነገጠች፡፡ መሬት መሬት ማየት ጀመረች…

ሚልከያስ ከአጠገቡ የተቀመጠችውን ውብ ካትሪንን እንደማያውቃት በደንብ ተመለከታት፡፡ የመጀመሪያ ጊዜ ከዩኒቨርስቲ በከፍተኛ ማዕረግ ተመርቆ ፈረንሳይ ሀገር ሆቴላቸው ከፍት የስራ ቦታ እንዳለ ተነግሮት ለመመዝገብ ሲመጣ እንደ አጋጣሚ አባቷ ኤድዋርድ ነበር ዩኒቨርስቲው ላይ በ 'Hotel and management' ለተመረቁ 'Top Students' ሽልማት በእንግድነት ተጋብዞ የሰጠው፡፡ እንዳየው ነው ያስታወሰው፡፡ ያለ ብዙ ግርግር ነበር ስራ የጀመረው፡፡ ይህ ደግሞ የሆነው በሚልከያስ ጉብዝና ጭምር ብቻ አልነበረም፤ እንደሱው ከፍተኛ ውጤት ያላቸው ተወዳዳሪዎች በርካታ ነበሩ፡፡ አንዳንዴ ችሎታ ያለ አጋጣሚ እና ዕድል ከንቱ ነው…

"ሚስት አለህ ሚስተር ሚልከያስ?" ከአባቷ አጠገብ መለየት የማትወደው የ12 ዓመቷ ካትሪን ነበር የጠየቀችው:: እንደ ሌላው እየሳቀ መለሰላት ፤ ሲወጣ ለኤድዋርድ 'ተመችቶኛል ቅጠረው' አለችው:: ተቀጠረ:: በከፍተኛ ውጤት የተመረቀ የመጀመሪያው ወጣት የሆቴሉ ከፍተኛ አስተዳደር በመሆን ሥራ ጀመረ::

ሁለት ዓመት በምክትል አስተዳደርነት እንዳገለገለ ሆቴሉን ሲያስተዳድር የነበረው ፈረንሳያዊ ዣን ኮማስ ቱኖሬ በህመም ምክኒያት ከስራው በገዛ ፍቃዱ ለቀቀ:: ዜናውን የሰማችው የ14 ዓመቷ ካትሪን ወዲያው ለኤድዋርድ "እርግጠኛ ነኝ ተገቢው ሰው ሚልከያስ ነው" አለችው:: ኤድዋርድም ወጣቱን ሳይፈራ ትልቁን ስፍራ ሰጠው:: ካትሪን እንዳለችው ኤድዋርድ ሚልከያስን ካሰበው በላይ ጠንካራ ሰራተኛ እንደሆነ ተገነዘበ:: ኤድዋርድ ሰው ወደደ ማለት ወደደ ነው! እናም ከሚልከያስ ከሚቀርቡ አስር ሀሳቦች ስምንቱን ያለ ጥያቄ ይቀበላል! ከማንም በላይ ያምነዋል! ያዛዥና የታዛዥ... የአለቃና የሠራተኛ ... ግንኙነት ሳይሆን የጓደኝነት መንፈስ ነው በመሀከላቸው ያለው:: በዚህ ሁለቱም ደስተኛ ናቸው:: ኤድዋርድ የሴት ነገር አይሆንለትም ሚልክያስ እና ሴቶችን ሲያስብ ግን በጣም ስለሚገርመው አንድ ቀን ጠየቀው

" አንድ ግላዊ ጥያቄ ልጠይቅህ?"

" ደስተኛ ነኝ ኤድዋርድ"

" ፍቅረኛ ለምን የለህም?"

"ፍቅርና ሞት የሚያመሳስላቸው ነገር አለ፤ ሁለቱም ያለ ቀጠሮ ነው የሚመጡት ሲመጡ በደስታ እቀበላለሁ"

" ወሲብስ ለምን አትፈፅምም ራስህን ዘና ማድረግ እኮ ይጠቅማል! ወሲብ ደግሞ ለዚህ ፍቱን መድኃኒት ነው"

"እምነቴ ከጋብቻ በፊት የሚደረግን ወሲብ በጭራሽ አይፈቅድም"

"ሀሳብህን አልቃወምም ቢሆንም ሕይወት አጭርና ውብ ናት! ተደሰትባት"

"ሰዎች ደስ ሲላቸው ሳይ በእነሱ ደስታ እኔ እጥፍ እደሰታለሁ! ለኔ በማሰብ ስለሰጠኸኝ

ምክርህ ግን ከልብ አመሠግናለሁ"

ከሚልኪያስ ተወዳጅ ፀባዮች አንደኛው ለማንኛውም አሉታዊ ይሁን አዎንታዊ አስተያየት ሆነ ሀሳብ ማመስገኑ ነው:: ከሰራተኞች ማንኛውም የመሰለውን አስተያየት ያምጣ በመጀመሪያ ስሙን ይጠራል 'ስለ ሀሳብህ አመሰግናለሁ' የሚል ይሆናል... አጥር ባለ ቃል ብዙዎች እንደ ተስማሙበት ሚልኪያስ ተወዳጅ ሰው ነው:: ለውቧ ካትሪን ደግሞ የልቧ ንጉስ ነው!!

* * *

ምንም የተናገረው ነገር የለም:: ከማንም ይበልጥ ቶሎ ስሜቱን የምታነበው ካትሪን በትኩረት አጤነችው፤ የሚያውጠነጥነውን ነገር ስድስተኛ ስሜቷ ሹክ አላት... በቀስታ እጁን ያዘችው

" ሚኪ! እንድትጨነቅ በጭራሽ አልፈልግም! ምንም ይፈጠር ምንም በእርግጠኝነት የምነግርህ ነገር ቢኖር በሁለታችን መሀከል የነበረው መልካም መተሳሰብ ሆነ ጓደኝነት አይቋረጥም! አንተን የመሰለ ሰው መቼም አላገኝም! እውነቱን ተናገሪ ካልከኝ ከሱዛን ጋር በስልክ ሳወራ ድንገት ሰማህ እንጂ አንተን ማፍቀሬን በድፍረት መቼም አልነግርህም ነበር:: ይልቅ ሚኪ ሰሞኑን ሲያስጨንቀኝ ስለነበረው እና ስለደበኩህ አንድ ሚስጢር የማትቀየመኝ ከሆነ ልንገርህና ቀለል ይበለኝ! መጀመሪያ ግን ላትቀየመኝ ቃል ግባልኝ"

አሁንም ይበልጥ ግራ እያጋባችው በዝምታ ተመለከታት::

" ልንገርህ?"

" ንገሪኝ"

" መጀመሪያ ቃል ግባልኝ"

" ቃል ገባሁልሽ! አልቀየምሽም! እኔ ልሙት!!"

* * *

ሚስተር ኤድዋርድ ከማንም በላይ የሚወዳት ካትሪንን ነው:: ስድስት ዓመት ሲሆናት ብር በፈለጉ ማፍያዎች ከትምህርት ቤት ታፍና ተወስዳ አፋኞቹ የጠየቁትን ሶስት

ሚሊየን ዶላር ፓሊስ ምናምን ብሎ ግርግር ሳይፈጥር ነበር የተጠየቀውን ብር ከፍሎ ያስለቀቃት:: ስለካትሪን ሲል አድርግ ቢባል የተፈለገውን ነገር እንደሚያደርግ እርግጠኛ ነው:: የልጁን የካትሪንን ፍላጎት ከማንም በላይ የሚያውቀው ኤድዋርድ የመጀመሪያ ውብ ልጁ ካትሪን በኢትዮጵያዊው ወጣት ፍቅር እንደ ተጠመደች ለማወቅ ጠንቋይ መቀለብ አላስፈለገውም... በእርግጥ ነገሩን ቢረዳም ከዝምታ ውጪ ያደረገው አንዳች ነገር የለም! በፍቅር ምርጫዋ ሆነ በማንኛዋም ውሳኔዋ ላይ መግባት የለብኝም ሲል ወስኗል::

ከሁለት ወር በፊት ቢሮው ውስጥ ሁለቱም ተቀምጠው ነበር::

" አፍሪካ እንዲሄድ እረፍት ለምን አትሰጠውም"

" ለምን?"

" አንዳንዴ ብቻውን ሲሆን በጣም ይጨነቃል! በጣም ያውጠነጥናል! ይፀፀታል የዚህ ሁሉ ምክኒያት ደግሞ ስለ ልጅነት ጓደኞቹ በማውጠንጠን ነው !! በልጅነቱ ለጓደኞቹ የገባው ቃል ነበረው፤ እርግጠኛ ነኝ አንድ ቀን መሄድ ይፈልጋል:: ስለዚህ ያንን ቀን ደግሞ እኛ ልናሳጥርለት ይገባናል:: በዚያውም ከኔ ጋር ጥሩ ጊዜ እናሳልፋለን"

" አንቺን ደስተኛ የሚያደርግሽን ማንኛውንም ነገር አደርግልሻለሁ!! ስለዚህ ሀሳቡን አነሳለታለሁ"

" አፍሪካ ግን እንዳትለው ዝም ብለህ ለምን እረፍት አትወጣም በለው" ይህን ባወሩ በነጋታው ኤድዋርድ ሚልክያስን ሲያገኘው እረፍት ለፈለገው ጊዜ መጠየቅ ከፈለገ በፈገግታ ተሞልቶ እንዲጠይቅ ነገረው:: ሚልክያስም ወዲያው ነበር" የዓመት ፍቃድ እረፍት" ወረቀት ሞልቶ በደስታ ያስገባው ታዲያ የአንድ ወር ከሳምንት ያህል እረፍት ጠይቆ ለመውጣት ሁለት ቀናት ሲቀረው ካትሪን እና ኤድዋርድ ብቻ በሚስጢር የሚያውቁት የቅንብር ድራማ ተዘጋጀ..

* * *

ካትሪን በመጠኑ እየተጨነቀች መናገር ጀመረች...

"የሚስተር ዋላስ ብሮዘር ቤተሰቦች ሆቴላችን ሲመጡ ምን ትዝ ይልሀል?"

ጥያቄው ግራ ገባው፤ ግን መለሰላት::

"ከልጆቻቸው ጋር ነበሩ"

" ስንት"

"እርግጠኛ አይደለሁም"

"እሺ የዋላስ ልጅ ከትልቁ መዋኛ ልትገባ ስትል አንተ እዚያ ቦታ እንዴት መጣህ?"

"ኤድዋርድ ለአስቸኳይ ጉዳይ ደውሎልኝ እሱ ጋር እየሄድኩ"

" ኤድዋርድ የት ነበር?"

" መዋኛው አካባቢ"

"ከዚያ ምን ተፈጠረ?"

"የዋላስ ልጅ ከትልቁ ገንዳ ውስጥ ገብታ..." የፈለገ ተዓምር ቢፈጠር ከትልቁ ገንዳ አራት ማዕዘናት አራቱ የዋና ሻምፒዮን ሠራተኞች አይጠፉም ነበር፤ ታዲያ በዚያን ሰዓት አራቱ ዋና አሰልጣኝና የአደጋ ጊዜ ጠባቂዎች በአንድነት የት ገቡ? ሚልክያስ ይህን ሁሉ አላስተዋለም ልጅቷን በመስኮት ዘሎ ካወጣ ከሴኮንዶች በኋላ ግን የዘወትር ቦታቸው ላይ በተጠንቀቅ ቆመው ነበር::

" የሕይወት አዳኝ ዋናተኞች በዚያን ሰዓት ነበሩ?"

"እህ... አልነበሩም?"

"እንዴት አልነበሩም"

" ልጅቷን ካወጣሁ በኋላ ግን ሁሉም በስፍራቸው ነበሩ"

" እሺ 200ሺ ዶላሩን ሚስተር ዋላስ እንደሰጡህ በምን አወክ?"

"ማለት?"

"ሆቴሉን ከመልቀቃቸው በፊት በአካል አግኝታቸዋል?"

" አልተገናኘንም!"

"ሚኪዬ... እንዳትቀየመኝ ግን ስለምወድህ... ከአንተ ጋር ጥሩ ጊዜ ለማሳለፍ ስል ብቻ ያደረኩት ነው"

ካትሪን ምን እንደምታወራ ግራ ገባው:: ወደ ኢትዮጵያ ከመምጣቱ በፊት ስለ

ነበረው ጊዜ ለማስታወስ ሞከረ... የተለየ ምንም ነገር ለማግኘት አልቻለም::

"ሚኪ ሁሉ ነገር ቅንብር ነበር!!" አለችውና ትንሽ አየር ስባ ቀጠለች::

"በእኔ እና ኤድዋርድ ብቻ የሚታወቅ ቅንብር ነበር"

"ምንድነው የምታወሪው ካትሪ..." አላት ሚልክያስ ይበልጥ ግራ ተጋብቶ በትኩረት እየተመለከታት::

"ስልኩም የተደወለልህ፣ ዋናተኞቹም ያልነበሩት... ገንዳ ውስጥ የገባችውም ልጅ፣ የብር ሽልማቱም... በእኔና በኤድዋርድ የተደረገ ነበር"

እሷ በጣም የምትወድለትን ሳቅ እሱ የንዴት ይሁን የመገረም ብቻ ከት ብሎ ሳቀ:: ከወንበሩ ላይ ተነሳ:: በገረሜታ ሁለመናዋን ተመለከታት:: ምን ማለት እንዳለበት ግራ ገባው::

"ሚኪ ጓደኞችህን እንደምትረዳበት እርግጠኛ ነበርኩ:: ከሁሉ በላይ ግን ካንተ ጋር ጥሩ ጊዜ ለማሳለፍ እንጂመቸኝ ነው:: አፈቅርሀለሁ! ልቤ ውስጥ ያለው እውነታ ይሄ ነው! እወድሀለሁ! ኤድዋርድም ያውቃል፤፤ በእርግጥ ምንም የተናገረው ነገር የለም... ወደድኩህ:: ማፍቀር መቻል ራሱን የቻለ ፀጋነት እንደሆነ የነገርከኝ አንተ ነህ! መቼም መውደዴ ጥፋት አይደለም... ልቤ አድርጊ ብሎ ያዘዘኝን ከፍቅር በመነጨ ብቻ ያደረኩት ነው ካስቀየምኩህ በጣም ይቅርታ!!"

ዝምታ::

ዝምታ::

ዝምታ::

ከብዙ ዝምታ በኋላ ሚልክያስ ተናገረ::

"ካትሪን ስላደረግሽልኝ ነገር ከልብ አመሠግናለሁ! ስሜትሽንም በጣም እረዳዋለሁ ቢሆንም ያነሳሽውን የፍቅር ጥያቄ ለመቀበል በጣም ያስቸግረኛል! ምክኒያቱም ካትሪ..."

ተናግሮ ሳይጨርስ ሳያስበው ዘላ ጥምጥም አለችበት::

" ሚኪ በጭራሽ እንዳትጨናነቅ! እውነቴን ነው የምልህ ከሱዛን ጋር በስልክ ስናወራ

ባትሰማኝ ሆኖ ስሜቴን ላልነግርህም አችል ነበር:: አንተ ራስህ አኮ ነህ ፍቅር በገንዘብ አይገዛም! ፍቅር በይሉኝታ አይገዛም! ፍቅር በምክኒያት አይገዛም! ፍቅር የልብ ለልብ መናበብ ነው! አንተ ራስህ አኮ ነህ ይህን ያልከኝ አኔም ደግሞ ልክ እንደ አንተው አምነት እና ፍላጎት የምፈልገው ንፁህ ፍቅር ነው! ስለዚህ ሚኪዬ ውስጤ ስላንተ ያለውን ስሜት ከተረዳህልኝ ለኔ በጣም በቂዬ ነው! ማፍቀር ተፈጥሮአዊ መብታችን እንደሆነና ማፍቀር ሀጢያት እንዳልሆነ የነገርከኝ አንተው ነህ ሚኪዬ... በዚህ ፍቅር የተነሳ በመሀከላችን የነበረው መልካም ጓደኝነት እንደማይቀየር አኔም ተስፋ አደርጋለሁ፤ አይደለም ሚኪ??"

"አትጠራጠሪ!!" አላትና ግንባሩዋን ሳማት:: የማስታወስ ችሎታዋን አያደነቀላት:: ካትሪን በደስታ ተሞላች ... ነገን ተስፋ በማድረግ!! የሰው ልጅ ያለ ተስፋ ደግሞ ከንቱ ፍጥረት ነው... ትንሽ ቆይታ ደግሞ ሚልክያስ ከሁለት ዓመት በፊት የነገራትን አባባል አስታወሰችና ፈገግ አለች::

'ሴት ልጅ ብልህ ከሆነች ያፈቀረችውን ወንድ ከእጇ ለማስገባት በጣም ቀላል ነው' ..........................................................................................................................................

...........................................................................................................................................................................

..........................................................................................................................

ሚልክያስ በዝምታ ሁሉን ነገር ያውጠነጥን ገባ... የመጀመሪያ ጊዜ ሚስተር ሚልክያስ ሚስት አለህ ያለችውን... ለምን አታገባኝም ያለችውን... በየአጋጣሚው ሁሉ በቀልድ አነጋገር ባለቤቴ ነው የምትለውን... ፊልም አይተው ሲጨርሱ የፍቅር ከሆነ አኔና አንተም ወደፊት እንደዚህ ነን የምትለውን... ሁሉ ትዝ አለው፤ ግን ሁሉንም እንደቀልድ ነበር የሚመለከተው... በቃ ቀልድ አለ አይደለም... ከኔ ፍቅር ይይዛታል የሚል ግምት ከቶ አልነበረውም... በመጨረሻ በዩኒቨርስቲ የሁለተኛ ዓመት ተማሪ እያለ ያነበበው "something about girls" መፅሐፍ ላይ በብዛት የተፃፈው ጥቅስ አንቃጨለበት::

" የሴቶችን ፍላጎት ለማወቅ መሞከር እና በምሽት ኮከቦችን ለመቁጠር መሞከር

አንድ ናቸው ፤ ሁለቱም መጨረሻ የላቸውም … በተለይ ሴቶች መጨረሻ የሌላቸው ጉድጓድ ናቸው።

# 17

# ቀን ሀያ ዘጠኝ...

ከምሽቱ 3፡00 ነው፡፡ በአዲስ አበባው አለም አቀፍ ቦሌ አየር መንገድ ውስጥ ያለው ቅዝቃዜ እጅግ የሚያስጠላ ነው፡፡ ሰውነትን ዝፍዝፍ ያደርጋል፡፡ የመጨረሻዋ የመለያያ ሰዓት ስትደርስ የሁሉም የልብ ትርታ ጨመረ፡፡ መለያየት እንዳለባቸው ለመንገደኞች ሰዓት እንደ ደረሰ የሚያሳውቀው ድምፅ አስታወቃቸው፤ ሲመጡ የተቀበላቸው ሰው በፈገግታ ተሞልቶ መጣና ሻንጣውን ተቀብሎ አምስት ደቂቃ ብቻ እንዳላቸው ተናግሮ ሄደ፡፡

" ስልክ እንደዋወላለን... በተረፈ በቅርብ ዓመት ውስጥ አብረን እንደምንሆን ተስፋ አለኝ በርታ መኑዬ!!" ተቃቅፈው ተሳሳሙ፡፡

ማርያማዊት አይን ላይ እንባ እንዳቀረረ ያስታውቃል፡፡ ምንም ሳትናገር ጥምጥም አለችበት! ማርያማዊት እንደሚልክያስ ሁሉ የበዛ ደስታዋን ከቃላት ይልቅ በለቅሶ መግለፅ ይቀናታል... አሁን ግን የምታለቅሰው ባር ባር ስላላት ነው ... ሁለቱም ሳያስቡት ለአንድ ደቂቃ ያህል እንደዚያው ቆዩ፡፡ ውቧ ካትሪን በቪዲዮ ካሜራዋ ትቀርፃለች... በመጨረሻ አንድ ደቂቃ ሲቀር መኑንም ማርያማዊትንም የመጨረሻ የስንብት ሰላምታ ሰጥቶ ወደ ውስጥ ሊገባ ባለበት ቅፅበት ከህዝቡ መሀከል አንድ ሰው በጣም እየሮጠ እነሱ ወደነበሩበት ቦታ ቀረበ፡፡ እግራቸውን እያንቀሳቀሱ ሳለ

" ሚልክያስ ... ሚልክያስ ..." የሚል ድምጽ ሲሰማ ዞር አለ፡፡

" ሙሌ!!"

ተመልሶ መጣና ጥምጥም አለበት፡፡

" አመሠግናለሁ ሙልዬ በእውነት ከሐረር ድረስ ስራህን አቋርጠህ መምጣት አልነበረብህም"

ሰልሳ ሴኮንድ ብቻ ቀረ፡፡ ምንም ማድረግ ስለማይቻል ፍጥነት ጨምረው ከካትሪን

ጋር ወደ ውስጥ ገሰገሱ፡፡ ከአይናቸው እስከሚሰወሩ ድረስ ቆመው ከሾፑዋቸው በኋላ መኑ፣ ሙሉጌታ፣ እና ማርያማዊት ተቃቅፈው እያወሩ ከአየር መንገዱ ቅጥረግቢ ወጡ፡፡

"we will be together again"

የሚለው የብራይት ማይክ ዜማ ከፊት ለፊታቸው ካለው መኪና ውስጥ ይደመጣል፣ መኪናው አጠገብ ደርሰው ሶስቱም ሲሰሙት ረጅም ሳቅ ሳቁ፡፡

# 18

# ፈረንሳይ

# ከ

# ሁለት ሳምንት

# በኋላ...

## 18

"በጣም ግራ የገቡኝን ነገሮች ልጠይቅሽ"

"ጠይቂኝ"

" ትወጂዋለሽ"

"አፈቅረዋለሁ! መውደድ ሊጠፋ ይችላል ፍቅር ግን አይጠፋም!"

" ፍቅረኛ አለው"

" የለውም"

"እስከዛሬ ወሲብ አላደረገም?"

"አላደረገም"

" እስከ ዛሬ ከማንም ሴት ጋር አልታየም?"

"አልታየም"

"የሚገርም ሰው ነው? እንደዚህ አይነት ሰው አለ ብሎ ለማመን በጣም ያስቸግራል:: ካንቺ ጋር ፍቅር መጀመር የማይፈልገው በእድሜ ስለሚበልጥሽ ነው? አባትሽን ፈርቶ ነው? ግራ ነው የገባኝ አንቺን የመሰለች ውብ የፍቅር ጥያቄ አቅርባለት እንቢ ማለቱ አስገርሞኛል? ለምን ይመስልሻል?"

"ነፃ ሰው ነው እሱ ሀቅን እንጂ ማንንም አይፈራም! በመሀከላችን ያለው የእድሜ ልዩነት ከፍተት ይፈጥራል የሚል ግምት የለኝም! ትልቁ ችግር ሚኪዬ እኔን የሚመለከተኝ እንደ እህቱ ነው! እንደ ጓደኛው ነው!! ሚኪዬ እንደ ሌሎች ወንዶች አይደለም... የተለየ ነው ... እሱ መኖር የሚፈልገው ለራሱ ሳይሆን ለሌሎች ነው! ከራሱ ስኬት ይልቅ ሌላ ሰው ሲሳካለት የሚደሰት ነው!ሚኪ በጣም የተለየ ሰው ነው:: እኔ ደግሞ ይህን የተለየ ሰው ነው ያፈቀርኩት!!... ማፍቀሬንም እቀጥላለሁ"

"ምን መናገር እንዳለብኝ ግራ ነው የገባኝ ... ጉዳዩን ከነገርሽው በኋላ ተቀየረብሽ?"

"ውይ! በተዓምር ... ያውድሮ የማውቀው ! ትላንት የነበረን ሳቅ... ደስታ ... ሰላምታ ... አልተለወጠም... አይ ሱዛን ሚኪዬ ጋር እኮ አንድ ዓመት ብትኖሪ ከኔ በበለጠ

በፍቅር የምትያዥው በእርግጠኝነት አንቺ ትሆኚ ነበር"

"አይታወቅም እንግዲህ ... አሁን ምንድ ነው እኔ ልረዳሽ የምችለው ካትሪ?"

" አመሠግናለሁ!! ምንም ነገር የለም! ሚኪዬን የኔ የማደርግበትን ሁኔታ ብቻ በመፈለግ ተባበሪኝ!! በመጨረሻ የተረዳሁትን አንድ ትልቅ እውነታ ልንገርሽ?"

" ደስ ይለኛል!"

"ፍቅር በጣም ደስ የሚል ስሜት ነው!!"

"ምንም ጥርጥር የለውም! በተለይ እኛ ሴቶች ከፍቅር ውጪ መኖር እንደማንችል ተረድቻለሁ:: ቢሆንም የማታገኚውን ሰው እንደማታገኚው እያወቅሽ ማፍቀር ከደስታው ይልቅ ሀዘኑ የሚበዛ ይሆናል... ፍቅር ትልቅ ትርጉም የሚኖረው ያፈቀርሽውን ሰው ያንቺ ማድረግ ስትችይ ነው!!"

"ልክ ነሽ! ሚኪ እንደሚለው አንድን ሰው ልውደድ ብለሽ መውደድ ትችያለሽ አንድን ሰው ላፍቅር ብለሽ ግን አታፈቅሪም ምክኒያቱም ፍቅር መግነጢሳዊ ሀይል ነው!! ከልብ ማፍቀር ማለት የምታፈቅሪውን ሰው ማግኘት አለብሽ ማለት አይደለም! መውደድ ሰጥቶ መቀበል ነው፤ ፍቅር ግን መስጠት ብቻ ነው!!"

ሕይወትን በቀላሉ የምትመለከተው ሱዛን ለምርጥ ጓደኛዋ ካትሪን በጣም አዘነች:: ጓደኛዋ ካትሪን በሚልክያስ እንደታወረች አሁን ተገለፀላት... እንዴት መርዳት እንዳለባት ማውጠንጠን ያዘች...

* * *

ሚልክያስ የዘወትር ስራው ላይ ተሰይሟል:: ካትሪን ትምህርት ቤት ናት:: ሚስተር ኤድዋርድ ከብራዚላዊቷ ቀበጥ ሊሊያና ሳንቶስ ጋር ወደ ብራዚል ሹልክ ብሏል::

4፡10 ደቂቃ ሲል ሳትስቅም የሳቀች የምትመስለዋ ከዝነኛው ቴሪ ዳንኤል አንሪ መንደር የመጣችው ወጣት ፀሐፊው ፈጠን ፈጠን እያለች ገባች::

"እንግዳ አለ ጌታዬ"

" ችግር የለውም አስገቢያቸው"

በሩ ተከፍቶ አንድ ሰው ገባ:: እየፃፈ የነበረውን ትቶ በር በሩን እየተመለከተ ስለ ነበር የገባውን እንግዳ ሲመለከት ልቡ ስንጥቅ አለ:: ለምን እንደ ደነገጠ ግን እርግጠኛ አይደለም:: ምናልባት ስልክ ስጥታው ስላልደወለላት ይሆን አይታወቅም:: ከወንበሩ ላይ ተነሳ::

"ሄላሪ" አለ ሞቅ ባለ አነጋገር:: ተሳሳሙ:: እንድትቀመጥ ጋበዛትና ተቀመጠች::

"ስልኬ እንደጠፋብህ እርግጠኛ ነበርኩ"

"አልጠፋብኝም... ባለመደወሌ ይቅርታ ብጠይቅ ይሻለኛል... ይቅርታ"

"ችግር የለውም ስራ እንደሚበዛብህ አውቃለሁ:: አ ኢትዮጵያ ተስማምታህ እንደነበር መናገር እችላለሁ! በአንድ ወር ውስጥ ተለወጥክ እኮ!!"

" አመሠግናለሁ! አንቺም ቀላ ብለሻል" አላት በትኩረት ካያት በኋላ::

" ከብዙ ጊዜ በኋላ ሀገርህን እንዴት አገኘሀት?"

"ሁሉ ነገር ያላሰብኩት ግን ደስ የሚል ነበር::"

ኪሷ ውስጥ የነበረውን የአለማችንን ምርጥ ቾኮሌት አወጣች:: በፈገግታ ተሞልታ ጠረጴዛው ላይ ገፋ አደረገችለት:: ይቺ ውብ ኢጣሊያናዊት ቾኮሌት እንደሚወድ በምን አወቀች? ወይስ በግምት ነው ያመጣችለት?

"ቾኮሌት እንደምትወድ ተስፋ አለኝ"

"በጣም አመሠግናለሁ"

ቃላት እንዳለቁ... የሚያወሩት አርዕስት እንደጠፋባቸው... ሳያስቡት ሁለቱም ዝም ዝም አሉ:: ባለፉት ሰላሳ ምናምን ቀናት በአየር ላይ ሆናም ሆነ መሬት ላይ በነበረችባቸው ጊዜያቶች ሁሉ ያለ ፍላጎቷ የምታውጠነጥነው ስለ ሚልክያስ ነበር:: ለምን?... ማስረዳት ባልቻለችበት ሁኔታ የሆነ ነገር ስለ እሱ እንድታስብ እያስገደዳት ነበር:: የእርጋታ እና የሰላም መንፈስ ውስጡ አይታለች... ከአይኑ ላይ ቅንነት አንብባለች... በዚያ ላይ ሴቶች ሁሉ የሚመኙት አይነት ግርማ ሞገስ አለው ... ምንም ሆነ ምንም ግን ከእርሱ ከተዋወቀች ሰዓት በኋላ መሬት ላይ ለመኖር ያላት ጉጉት ከፍ ብሏል:: ስለብቸኝነት አስጠሊነት ለመጀመሪያ ጊዜ

እንድታስብ ያደረጋት እሱ ነበር::

ብቻ እሱን ካየችበት ... ካዋራችው ሰዓት ጀምሮ የሆነ ነገር ከአካላቷ ላይ ተጨምሯል... የሆነ ነገር ደግሞ ሄዷል:: ዛሬም ወስና የመጣችው ስለልጂ ትርታ ሊታጫውተው ጭምር እንጂ በውብ ሆቴል ለሁለት ቀናት ለመቀመጥ ብቻ አይደለም::

"ጊዜ ካለህ ማታ እራት አብረን ብንበላ በጣም ደስ ይለኛል"

"ዐላ? ... የት እዚህ?"

ከኤፍል ታወር በስተቀኝ 100 ሜትር ርቀት ላይ ከዋናው መንገድ ገባ ብሎ የተንጣለለ ግቢ አለ:: እጅግ በርካታ እንደሷ ያሉ ከአየር መንገድ ጋር ቅርበት ያላቸው ፓይለቶች ፣ ሆስቴሶች፣ የአየር መንገድ ሠራተኞች በብዛት የሚዝናኑበት እጅግ ውብ ከሆኑ ምርጥ መዝናኛዎች አንዱ በዝነኛው የፈረንሳይ ጦረኛ ናፖሊዮን በናፓርት የተሰየመው 'ናፖሊዮን ሬስቶራንት' ነው::

"ናፖሊዮን ሬስቶራንት" አለችው::

"በጣም ደስ ይለኛል"

"በቃ ስራህ አላስፈታህ ማታ እስከምንገናኝ መልካም ጊዜ ይሁንልህ"

ከወንበሩ ላይ ተነሳች:: እሱም ተነሳ:: ተጨባብጠው ተለያዩ:: ከቢሮው ወጣች:: የማይረሳ ፈገግታ ለግሳው...

* * *

የ Paris ከተማን በምሽት ያያት በእሳት የተያያዘ ደንን ትመስላለች:: ከቀን ይልቅ ውበቷ በጣም የሚጎላው ማታ ላይ ነው::

ሄላሪ ሁሌ ሽክ ብላ ማጌጥ ደስ ይላታል:: አልባሳትን ስትገዛ ሁልጊዜ በጥንቃቄ ነው:: በዚያ ላይ በዋጋም ወደድ የሚሉ ዕቃዎች ይማርኳታል:: አሁንም ከምሽቱ ጋር ለራት የሚሆን ልብስ ለበሰች:: ከጫማዋ ጋር የሚሄድ ጆሮ ጌጥ አደረገች:: ሮዝ ቀለም ያለው የከንፈር ቀለም ተቀባች:: ሽቶም ነሰነሰች...ዋ...ውብ ሆናለች! በውበቷ ላይ ሌላ ውበት ጨመረች...

ስለሚልከያስ መረጃ አሰባሰባለች:: ከሶስት ሳምንት በፊት ሳቂታዋ የሚልከያስ ፀሐፊ ጋር ገባች:: ብዙም ሳትቸገር ተግባባቻት::

" ለምን እራት አልጋብዝሽም"

" ደስ ይለኛል"

እራት እየበሉ በመሀከል ወደ አላማዋ ቀስ በቀስ ገባች::

" ሚስተር ሚልከያስን እኮ ከሚስታቸው ጋር አውሮፕላን ውስጥ አንድ ላይ አግንቼያቸው ነበር"

" ኧረ ባክሽ! ካትሪ ሚስቱ አይደለችም"

" ምኑ ነች?"

"የ ...." ብላ ጀመረችና ስለካትሪን እና ሚልከያስ መካከል ያለውን ግንኙነት አጫወተቻት:: ሄላሪ ምንም ሳትፈራ

" ብመኘውስ" አለቻት::

"ሚስተር ሚልከያስን"

"በጣም የወደድኩት ይመስለኛል"

"የሚሳካልሽ አይመስለኝም! ከተሳካልሽ ግን እርግጠኛ ነኝ በአለም ያለ እጅግ ምርጥ ባል ይሆንሻል... ሚስተር ሚልከያስ በጣም ወርቅ የሆነ ሰው ነው:: ሶስት ዓመት ሙሉ ከእርሱ ጋር ሠርቻለሁ አንድም ቀን አስቀይሞኝ አያውቅም" ለሄላሪ ስለሚወደው ምግብ፣ ስለሚወደው ልብስ ... ቀለም... ወሬ... ምግብ ቤት ... ሁሉንም ነገረቻት:: ቾኮሌት እንደሚወድ የነገረቻትም እሷው ናት:: ናፖሊዮን ሬስቶራንትን እንደሚወድ የነገረቻትም እሷው ናት ... ዛሬም የለበሰችው ... የከንፈር ቀለሟም ... ቀሚሷም ... ሁሉ የእርሱን ምርጫ መሠረት አድርጋ ነው::

ለመጨረሻ ጊዜ ሰዓቷን ተመለከተች:: 12:30 ደቂቃ ይላል:: ከመኝታ ቤት ወጣች:: ከታላቁ ሆቴልም ወጣች:: ብዙም ሳትሄድ ከፊት ለፊቷ አንዲት የእርሳስ ቀለም የተቀባች ታክሲ መጥታ ገጭ አለች... ሕንዳዊው ሹፌር በፈገግታ ተሞልቶ ስብርብር ባለ

አጠራር ከላይ እስከታች ቃኛትና ተናገረ:: ሙቀት ለመፍጠር ፈልጎ ነው እንጂ መኪናዋ ጎን በትልቁ ታክሲ የሚል ፅሁፍ ይነበባል...

" በንገፑር ታክሲ" አላት:: አርባ ጥርሶቹን ለማሳየት እየሞከረ:: የሰው ልጅ 32 ጥርስ አለው:: የእርሱ የጥርስ ብዛት ግን 40 ነው፤ በዚህ ራሱን የተለየ ፍጡር በማድረግ ይመለከታል:: ደስተኛም ነው::

በቀስታ በሩን ከፍታ ገባች::

"የት ላድርስሽ እመቤቴ?"

"ናፖሊዮን ሬስቶራንት"

* * *

የካትሪን ሹፌር አንድ ሴኮንድ እንኳን ሳይዘገይ ሁሌ ትምህርት ቤቷ በራፍ ላይ ይደርሳል:: መኪናዋ ውስጥ በፍጥነት ትገባለች...በመኪናዋ ከት/ቤት መጥታ የሚልክያስን አይን ሳትመለከት ከሆቴላቸው አንድ ሺ ሜትር ርቀት ላይ ባለው የተንጣለለ እጅግ ዘመናዊ ቤታቸው ሄዳ አታውቅም:: አዋርታው ስለውሎዋ በመጠኑ ነግራው የእርሱንም ጠይቃው... ቤት ታመራለች ...ታዲያ ቢሮ የለም ስትባል ህሞቷ ፍስስ ይላል:: በጣም ትበሳጫለች::

ዛሬም እንደወትሮዋ ገብታ ግንባሩ ላይ ሳመችው:: ስለ ውሎዋ አጠር አድርጋ ነገረችው:: የሱንም ጠየቀችው:: ተሰናብታው ልትወጣ ካለች በኋላ ተመልሳ መጣችና በፍቅር አይን ትመለከተው ገባች፤ ቀና ብሎ ተመለከታት::

" ሚኪ ዛሬ ትምህርት ቤት አትሄድም ስለዚህ ለምን ራቅ ያለ ስፍራ ሄደን ራት አንበላም?"

"አመሠግናለሁ ካትሪ ግን አልችልም"

"ለምን" አለች ሀዘን በተሞላበት አነጋገር::

"አንድ ሰዓት ላይ ቀጠሮ አለኝ ካትሪ"

" በቃ ስትጨርስ ደውልልኝ"

ካትሪን ቅር እያላት ወጣች:: ከካትሪን በኋላ ሚስተር ... መጣ ... ቀጥሎ ... እያለ

ሳያውቀው 12:00 ሰዓት ሆነ ቀሪውን ጊዜ ለምክትሉ ትቶ ወደ ቀጠሮው ለማምራት ከቢሮው ወጣ:: ከቢሮ ወጥቶም ላይ ታች ሲል 30 ደቂቃ ሳያውቀው ቀለጠ:: ወደ ሄላሪ ማምራት እንዳለበት ወሰነና መኪናውን አስነስቶ ተፈተለከ::

* * *

ሄላሪ ከዝነኛው ሬስቶራንት ጉብታ ብዙም ሳትቸገር ቀን በስልክ ያስያዘችውን ወንበር አገኘች:: ተቀምጣ አንድ ደቂቃም ሳይሆናት ከኋላዋ የእግር ኮቴ ሰማች:: በፈገግታ ተሞልታ... አብረቅርቃ ... ከተቀመጠችበት ወንበር ላይ ብድግ አለች::

ጠላቱ ከው ይበልና ሚልኪያስ ከው አለ:: በየሴኮንዱ ውበቷ የሚጨምር ሴት ብትኖር ሄላሪ እንደሆነች ገመተ:: ለዘመናት ተጠፋፍተው እንደተገናኙ ሰዎች ሁለቱም ሳያስቡት ተቃቀፉ... ተቀመጡ:: አካባቢውን ቃኙ:: የሚወደው አበባ ... የሚወደው ሻማ... ጠረጴዛው ላይ ሳያዝ የሚወደው መጠጥ ተቀምጧል 'ነገሩ እንዴት ነው... ሄላሪ ስለ እኔ የምታውቀው ነገር አለ? አጋጣሚ... ወይስ የሁለታችንም ምርጫ ተመሳሳይ ነው?' ራሱን ጠየቀ:: ግራገባው ... ግራ መጋባቱን ሄላሪ አነበበችበት::

" ይህን መጠጥ አባቴ በጣም ይወደዋል! እኔም እወደዋለሁ! አንተም እንደምትወደው ተስፋ አለኝ"

" እ... በጣም ደስ ይለኛል" አላት::

..............................................................................................................................

..............................................................................................................................

..........................................................................................

ለግማሽ ሰዓት የባጥ የቆጡን ሲያወሩ ቆዩ:: በመሀከል ሚልኪያስ "እሺ ሄላሪ ምን አዲስ ነገር አለ?" አላት:: ሄላሪ ከብዙ ዝምታ በኋላ ሚልኪያስን እየቃኘች...

" እንደነገርኩህ በመሬት ላይ ምንም የለኝም! የሚገርምህ ከእናቴና አባቴ ሞት በኋላ የወሰንኩት በቀጥታ ሆስቴስ ለመሆን ነበር:: አውሮፕላን ላይ ስሆን የቀረብኳቸው

ይመስለኛል:: በዚህ የተነሳ መሬት ላይ መኖር ብዙም አልወድም:: ከወር በፊት ግን መሬት ላይ ለመኖር ጉጉቴ በጣም እንዲጨምር አጋጣሚ ተፈጠረ:: አሁን የተረዳሁት ትልቅ ሀቅ አንዷት የሕይወት ገጠመኝ መላ ሕይወታችንን ልትለውጥ እንደምትችል ነው" ብላ ዝም አለች::

ስታወራ እርጋታዋ፣ የድምፅዋ ቅላጼ በጣም ይለሰልሳል:: እናም ሁሉም ብዙ እንድታወራ ይፈልጋል:: ሚልክያስም ንግግሯን እንድትቀጥል ጠየቃት::

" የምን አጋጣሚ?"

" ከአስራ አምስት ቀናት በፊት ኡራጋይ ነበርኩ:: ያረፍኩበት ሆቴል ውስጥ ተቀምጬ አንድ መፅሔት እያነበብኩ ነበር... መጽሔቱ ላይ በኡራጋይ እጅግ ከፍተኛ የዝና ጣሪያ ላይ ስለተቀመጠ ሰው ይተርካል! መፅሐፍ ቅዱስን ከሚሰብኩ እናት እና አባቱ የተወለደው ይህ ሰው በወጣትነቱ እጅግ በጣም አዋቂ፣ ትሁት፣ ሰው አክባሪ የነበረ ቢሆንም ሳያስበው በአገሪቱ በጣም ዝነኛ የነበረን ሰው በመኪና ገጭቶ ዘብጥያ ወረደ::" ብላ ትንሽ ዝም አለችና ቀጠለች:: "ለሀገሪቱ እጅግ በጣም ወሳኝ የሆነ እና ዝነኛ የሆነን ሰው በመግደሉ ... የተንጫጫውን ህዝብ ዝም ለማስባል ያልሠራው ወንጀል ላይ የፈጠራ ድራማ ተጨምሮበት 'እጅግ በአሰቃቂ ሁኔታ ገድሎት ሬሳውን አንስቶ ሀኪም ቤት ከመውሰድ ይልቅ ወንዝ ውስጥ ለመጨመር ሲጥር እጅ ከፍንጅ በመያዝ' የሚል ክስ ታክሎበት ሀያ አምስተኛው ዓመቱ መግቢያ ላይ የአስራ ስድስት ዓመት ፅኑ ፍርድ ተፈርዶበት ዘብጥያ ተወረወረ... ዘብጥያ በተወረወረ በሁለተኛው ቀን በሁለት ግብረሰዶማዊያን ተደፈረ... ሕይወት ጨለማ ሆነበት!! በጣም አስቀያሚ የሆነ ሕይወት መኖር ጀመረ:: እንደ ምንም አምስት ዓመቶች አለፉት... በዘብጥያው ውስጥ መደፈሩ ... ድብደባው ... ህመሙ ሲፈራረቅበት አንድ ምሽት ራሱን ለማጥፋት ወሰነ ... ሌሊቱን ሙሉ አውጠነጠነ ሁሉ ነገር ጨለማ መስሎ ስለታየው በውሳኔው ፀና!! እነሆ በማለዳ ተነሳ ... የተሰጠውን የእስር ቤቱን ልብስ በመቀዳደድ በገመድ መልክ አድርጎ አዘጋጀ... ገመዱን የእስር ቤቱ መስኮት ብረት ላይ ዘሎ አስገባና ገመዱን ወደ አንገቱለማስገባት ሲያመቻች ድንገት እጅግ በጣም የሚጠላት እና የሚፈራት ፍጥረት

የሆነችው አይጥ ከአልጋው ስር ብቅ አለች... የሆነ ወረቀት አስቀምጣ ስትሄድ ተመለከተ...ከብዙ ማውጠንጠን በኋላ ወረቀቱን ሄዶ ተመለከተ:: ከሆነ መፅሐፍ ላይ የተገነጠለ ገልፅ ነበር:: በወረቀቱ ላይ የተፃፈውን ሲያነበው ... 'ሕይወት አንተን በ ከፍታ ላይ ልታስቀምጥህ ስትፈልግ ፈተና ታበዛብሀለችና በምንም ተዓምር ተስፋ እንዳትቆርጥ' የሚል ነበር:: እጅግ በጣም ተገርሞ ብዛት ላለው ጊዜያት አነበበው! እጅግ በሕይወቱ የሚፈራት እና የሚጠላት አይጥ ራሱን የመግደል ሀሳቡን አስቀየረችው... ወዲያው ወሰነ ... በቀሪ ዘመናቱ በዘብጥያው ውስጥ የሚገኙትን መፅሐፍት ሁሉ እያነበበ ሳያስበው የእስር ዘመኑ አለቀና በ40 ዓመቱ ከዘብጥያ ተፈታ!! Faith or Fate የሚል እጅግ ድንቅ የሆነ በኡራጋይ የመፅሐፍ ሽያጭ ታሪክ ግንባር ቀደም የሆነ መፅሐፍ ፃፈ...በዓመቱ ይህ Faith or Fate የተሰኘው መፅሐፍ በ45 ቋንቋዎች ተተረጎመ፤ ይህ ሰው ባሁኑ ሰዓት በአለም አቀፍ ደረጃ እጅግ ተፅዕኖ ፈጣሪ ከሚባሉት ፀሐፊያን መሀከል ግንባር ቀደሙ ነው:: የመፅሔቱ አዘጋጅ የዝነኛውን ደራሲ ፅሁፍ ያጠቃለለው ከደራሲው ፅሁፍ Faith or Fate መፅሐፍ ሀሳብ በመቀንጨብ ነው:: የተቀነጨበው ሀሳብ " በሕይወት ዘመናችሁ ላይ ስኬታማ ለመሆን ሁልጊዜ ማውጠንጠን ያለባችሁ ስላጣችሁት፣ ስለማትችሉት፣ ስለድክመታችሁ... ስለ መጥፎ ገጠመኛችሁ ሳይሆን ስላላችሁ እና ሊኖራችሁ ስለሚችለው ነገር! ስለችግሩ ሳይሆን ስለ መፍትሔው ብቻ መሆን አለበት! በዚያ ላይ በሕይወታችሁ የሚፈጠረው እያንዳንዱ ጥሩ ይሁን አስጠሊታ ገጠመኝ ዋነኛ አላማው እናንተን ለመጣል እና ሰብሮ ለማስቀረት ሳይሆን ሊያጠነክራችሁ ነውና ምንም ይፈጠር ምንም ቀናውን ብቻ ተመልከቱ" የሚል ነው:: እውነቴን ነው የምልህ የዚህን ሰው ታሪክ ካነበብኩ በኋላ ራሴን ሰብሰባ ጠርቼው ከራሴ ጋር በጣም ስከራከር ነበር... ከራሴ ጋር በጣም ስወዛገብ ነበር... ትዳር የለኝም! ፍቅረኛም የለኝም! ብቸኝነትን በጣም ነበር የምወደው! ለኔ ሕይወት ማለት ነፃነት ነው! የነፃነት መገኛው ደሞ ብቸኝነት ነበር የሚመስለኝ ነገር ግን ይህ የነገርኩህ ታሪክ እና በተለይ ከወር ምናምን በፊት ስለ ሕይወቴ ቆም ብዬ በማስተዋል እንዳስብ ያደረገኝ የተለየ ሁኔታ አውሮፕላን ውስጥ ገጠመኝ! አንድ ወጣት አየሁ! በቃ የማላቀው ነገር መጥቶ ወረረኝ!

ሕይወትህን ወይም አስተሳሰብህን በድንገት ያስቀየረህ ነገር አጋጥሞህ አያውቅም ሚልክያስ?"

"በጣም ብዙ ጊዜ!"

" ፍቅር ያዘኝ ከአንድ መንገደኛ በድንገት ፍቅር ያዘኝ! አላውቅም ግን አፈቀርኩት እስከ አሁኑዋ ደቂቃ ድረስም የማስበው ስለ እሱ ነው"

ሄላሪ የመመገቢያ ሰዓት ብላ በስልክ ያስመዘገበችው ሰዓት እና ደቂቃ ስለደረሰ ከፊት ለፊታቸው በመጠኑ ወፈር ያለች ወጣት አግር ሴት በፈገግታ አሸብርቃ መጥታ ጎንበስ አለች:: ሄላሪ የሜኑውን ፎልደር አነሳችና ማንበብ ያዘች:: ሚልክያስም በተመሳሳይ ሜኑውን ማንበብ ያዘ::

ክፍሉ ውስጥ ቀዝቀዝ ያለ ሙዚቃ ይደመጣል:: ራቅ ራቅ ብለው በተቀመጡት ወንበሮች ላይ ጥንዶች በየቦታው አፍ ለአፍ ገጥመው እያወሩ ነው:: በየጠረጴዛው ላይ ያሉት ሻማዎች በሙሉ በርተዋል ... የክፍሉ ዋናው መብራት ደብዘዝ ያለ ስለ ሆነ በክፍሉ ውስጥ ያሉትን ሰዎች መልክ ለመለየት በመጠኑም አስቸጋሪ ነው:: ሁኔታውን ላስተዋለው ቀይ በቀይ በብዛት የለበሱ የሉም እንጂ የፍቅረኞች ቀን ነበር የሚመስለው::

" ዘጠኝ ቁጥር" አለች ሄላሪ አንብባ ስትጨርስ:: ሚልክያስም እየሳቀ::

" ለኔም ዘጠኝ ቁጥር" አላት:: አስተናጋጂ ፈገግታ ለግሳቸው ሄደች:: በሁኔታው ሄላሪና ሚልክያስም ተሳሳቁ:: ተመሳሳይ ምርጫ !

" የሰው ልጅ የተፈጠረው ለማፍቀር ነው! ብዙዎች ፍቅር በመላመድ ብዛት የሚፈጠር ስሜት ነው ይላሉ ለኔ ግን ያ መውደድ ነው እንጂ ፍቅር ገጠመኝ ነው የሚል እምነት አለኝ:: መንገደኛሽን አላናገርሽውም"

አነጋገሩ አዘኔታ የተሞላበት ነበር:: ከዚህ በፊት ለአንድ ቀን የሚያውቃት ሳይሆን ለዘመናት የሚያውቃት ነው የመሰለው:: በተለይ ታሪኳ ከማርያማዊት ጋር መመሳሰሉ ይበልጥ አሳዝኖታል! ሁለቱም እናት ሆነ አባት የላቸውም፤ ሄላሪ ለጥያቄው ምላሽ ሳትሰጠው ይቅርታ በመጠየቅ ወደ መፀዳጃ ቤት አመራች ... ተመልሳ ገና እንደተቀመጠች ሁለቱም

የመረጡት ጣፋጭ ምግብ መጣ:: እንደ ኢጣሊያኖች የምግብ ሰዓትን እና ሥርዓትን በማክበር በአለም ላይ የለም ማለት ይቻላል:: ይህን ሚልከያስ ስለሚያውቅ ዝም ብሎ መብላት ጀመረ:: ሄላሪም በዝምታ ታስገባ ጀመር::

ፈገግታ እየተለዋወጡ ጨረሱ:: ምግብ ሲበላ መናገር አይወድም ሚልከያስ :: የዚህ ምክኒያቱ ደግሞ ምግብ እየተመገበ ትን ብሎት የሞተ ሰው በልጅነቱ ስለተመለከተ ነው… ዕቃው ተሰበሰበ::

" በጣም አሪፍ ነበር"

" እኔም ተመችቶኛል"

ትንሽ ዝም አለች:: ሳያስበው ሰርቆ ተመለከታት:: ውብ ናት:: ውብ የሚለው ቃል ራሱ ይበቃት ይሆን?... በጣም ያስደነቀው የጀመረችለት ወሬ ነው

'ምን አይነት ግለሰብ ቢሆን ነው ያ መንገደኛ ያለችው ሰው ልቧን በድንገት ይዞባት የቀለጠው' ራሱን ጠየቀ::

እሷም ምን እያሰበ እንዳለ ሳትገምት አልቀረችም

" መንገደኛዬን አናግሬዋለሁ" አለችው

" እ...ና... ምን አለሽ?"

"ምንም"

" አልገባኝም"

"እንዴት መሰለህ" ብላ ፈገግ አለችና ንፁህ አየር ወደ ውስጥ አስገብታ አስወጣችና መናገር ቀጠለች::

"ለማውራት በቂ የሆነ አጋጣሚ አላገኘሁም፤ በዚያ ላይ ከእርሱ ጋር ድንገተኛ ፍቅር እንደያዘኝ ያወኩት ከተለየሁት ከሁለት ሳምንት በኋላ ነበር"

" አድራሻውን እንኳን አልሰጠሽም?"

" ስልክ ሰጥቶኛል" አለችና ድንገት የሆነ ነገር እንዳስታወሰች ፊቷ ይበልጥ በፈገግታ አብረቅርቆ! ተሞልቶ ኪሷ ውስጥ የነበረውን ሞባይል አወጣች::

ያዘችው::

" አሁን ልደውልለት?"

"ደውይለት"

" ምን ልበለው?"

" እንደ ወደድሽው ንገሪው... ወይም በውስጥሽ የተሰማሽን ስሜት አካፍይው" ምንም ሳትናገር አይን አይኑን እየተመለከተች ስልኳን አነሳች:: ደወለች:: ሚልክያስ ሞባይሉን ሁሌ የሚያስቀምጠው ከቀኝ ኪሱ ውስጥ ነው:: ድንገት ስልኩ ሲጮህ አወጣውና የደወለውን ሰው ማንነት ሳያይ ዝም ብሎ ' ok ' የሚለውን ተጫነው::

" ካንተ ፍቅር ይዞኛል"

የሚል ድምፅ ደረሰው:: ሙብረቅ የወደቀበት ያህል መላ አካላቱ ፍርክስክስ አለ... ልቡ ስንጥቅ አለች! እንደምንም ብሎ ተመለከታት... በፈገግታ ተሞልታ ሞባይሏን ዘግታ ጠረጴዛው ላይ አስቀመጠችው:: ታላቅ ዝምታ ሰፈነ!

ያያታል::

ታየዋለች::

በቃ ይመለከታታል!

ትመለከተዋለች !

..........................................................................................................

..........................................................................................................

..........................................................................................................

.............................................. ምን ብሎ ይጀምር? በእርግጠኝነት በሕይወቱ እንደሷ ያለች ውብ አይቶ አያውቅም! እንደሷ ማንንም ለመጀመሪያ ጊዜ አይቶ ቀልቡን የሰረቀችበት ሴት የለችም! እንደሷ እና እንደ ማርያማዊት አሳዛኝ ታሪክ ያላቸውን ሴቶች አይቶ አያውቅም... ብቻ እንዳች ምትሀት

አላት … ሰውን የሚስብ … እንዲያዝኑላት የሚያደርግ … በጣም ተነፈሰ… የልብ ምቱ ድውይታ … ድው ድው… እያለ ከሰባ ወደ 100 ተጠጋ:: ምንም ማድረግ ግን አይችልም … ምንም !! ያለው አማራጭ ማዘን ብቻ ነው… እንደ ምንም ብሎ ከንፈሮቹን አፈላቀቃቸው

" ሄላ…ሪ" አላት:: በፈገግታ ተሞልታ ተመለከተችው::

" ምን ማለት እንዳለብኝ አላውቅም… እውነቱን ለመናገር እኔም እንዳንችው ደስ የሚል ስሜት ተሰምቶኝ ነበር"

በጣም ተነፈሰና መናገር ቀጠለ::

የሄላሪ አይኖች እንዳፈጠጡ ናቸው::

" ኢትዮጵያ ውስጥ ሆኜ አንድ ሁለት ቀናት አስታውሼሽ ነበር… በተለይ የማይረሳው ፈገግታሽ ድቅን እያለ ሲያስገርመኝ ነበር… እዚህ ፓሪስ ከመጣሁ በኋላ ሁሉ ስላንቺ አስቤ ነበር ከዚያ ራሴን መዘንኩት ወይንም አንቺ የተጠቀምሺውን አገላለጽ ልጠቀምና ራሴን ስብሰባ ጠርቼ ስመለከተው በሚቀጥሉት ሶስት ዓመቶች በዚህ ሆቴል ውስጥ ተቀጥሬ እሠራለሁ:: ከዚያ አሁን ዝርዝር ጉዳዩን በግልፅ ልነግርሽ የማልችለው በአይነቱ ለየት ያለ በማታው ክፍለ ጊዜ በሳምንት ለአራት ቀናት የምማረው ት/ት አለ፤ ያን ትምህርት እንደጨረስኩ በቀጥታ ወደ ሀገሬ ኢትዮጵያ በመመለስ ትልቁን ዓላማዬን በይው የበርካቶችን ሕይወት የሚለውጥ ታላቅ ስራ ለማሳካት ከአምላክ እገዛ ጋር አደርጋለሁ:: ለዚህ ደግሞ ብዙ ሰዓት ማንበብ ፤ ብዙ ሰዓት መስራትን ፤ ብዙ ሰዓት ማውጠንጠን…. ብዙ ሰዓት ብቸኛ መሆን እፈልጋለሁ:: ፍቅር እጅግ ደስ የሚል አነቃቂ ስሜት ነው… አየሽ በሕይወቴ የተገነዘብኩት ትልቅ ቁም ነገር የፈለግሺውን ነገር ለማሳካት የሚያስፈልጉ ሶስት ወሳኝ ነገሮች አሉ

1. የምትሰሪውን ነገር ማወቅ
2. ከፍተኛ መሻት /ፍቅር/ ቁርጠኝነት ማሳየት
3. የምትሰሪውን ነገር የሚፈልገውን ነገር ለይቶ ማወቅ ብቻ ሳይሆን መስዋዕት ለመክፈል ለራስ ቃል ኪዳን መግባት ናቸው:: ከዚህ የተነሳ ፍቅርም ለመጀመር

የፍቅር ምንነትን ማወቅ፣ ፍቅር የሚፈልገውን ነገር ለሟሟላት መዘጋጀት ያስፈልጋል... እኔ ደግሞ የፍቅር ህይወት እንዲኖረኝ ብፈልግሃም ለዖታዊ ፍቅር መልካም የሆነ አመለካከት ቢኖረኝም ፍቅር የሚፈልገውን ነገር ለመክፈል አሁን ዝግጁ አይደለሁም ስለዚህ ... ስለእኔ ያለሽን ስሜት አከብረዋለሁ ለመቀበል ግን እቸገራለሁ... በእርግጠኝነት ግን መሻቱ ካለሽ ንጹህ ጓደኛሽ ለመሆን ዝግጁ ነኝ እንጂ ቅድም እንዳልኩት ለፍቅር ጥሩ የሆነ ስሜት ቢኖረኝም የፍቅር ህይወት ውስጥ ገብቶ ሀሴት ለማግኘት... ትዳር ለመያዝ ... ልጅ ለመውለድ ... ቤተሰብ ለመመስረት የመሰሉትን ትልቅ ሀላፊነት የሚፈልጉ ነገሮችን ለመከወን በጣም ዝግጁ አይደለሁም! የማልጨርሰውን ነገር መጀመር አልፈልግም! ያንቺንም ጊዜ በከንቱ ለማቃጠል በተዓምር አልሻም! ለ E.B.F.W የተባለ ልዩ ድርጅት ዝርዝር አላማውን አሁን ትምህርቱን ሳልጨርስ ልነግርሽ በማልችለው ልዩ ተልዕኮ ለማሳካት በሚቀጥሉት ስድስት ዓመቶች ቃል ገብቻለሁ! ትረጂኛለሽ ብዬ ስለገመትኩ ነው ለማንም ያልተነፈስኩትን ሚስጢር በጣም በትንሹም ቢሆን ላንቺ ሹክ ያልኩት... እንደምትረጂኝ ተስፋ አደርጋለሁ!!"

.......................................................................................................................

.......................................................................................................................

ሄላሪ ቀዝቃዛ ውሃ እንዳፈሰሱባት ፣ ዝናብ እንደመታት ወፍ ኩምሽሽ አለች.... በመሬት ላይ ለመኖር እንዳልተፈጠረች አሁን ገባት ... በራሷ እድል አዘነች!

ምንም የተናገረችው ነገር የለም!!

" በጣም ይቅርታ አድርጊልኝ ሄላሪ! አብሬሽ የፍቅር ሕይወትን ብቋደስም ደስ ይለኝ ነበር ግን ... አልችልም!!"

ፍፁም ያልጠበቀችው እንባ ከቀኝ አይኑዋ ላይ ዱብ አለ:: የሚልከያስ ልብ ባር ባር አለው:: ምን መናገር እንዳለበት ሁሉ ግራ ገባው::

ያያታል:: በዝምታ::

ታየዋለች፡፡ በዝምታ ! ከአይኗ ላይ እንባ ጠብ... ጠ... ብ... እያለ፡፡

ዝምታ፡፡

ዝምታ፡፡

ዝ...ም...ታ...፡፡

በመጨረሻ ግን እጅግ አስፈሪውን በመሀከላቸው እንደ ጨለማ አጥልቶ የነበረውን ዝምታ የገፈፈችው ሄላሪ ናት፡፡

" ምንም አይደለም! በጣም ነው የማመሰግንህ፡፡ የብዙዎችን ሕይወት የሚለውጠው አላማህ እንደሚሳካልህ ተስፋ አደርጋለሁ!ከአጠገብህ በመሆን ማገዝ ብችል እንዴት ደስ ባለኝ ነበር" አለች ተስፋ መቁረጥን ባዘለ የድምፅ ቃና፡፡

ጨበጠችው፡፡

ጨበጣት፡፡

*           *           *

መጫዎወት ያለባቸውን ያህል ተጨዋውተው ሊለያዩ ሲሉ ቀድማው ድንገት ብድግ አለች፡፡ ሳያስበው በጠረጴዛው ላይ ጎንበስ ብላ ግጥም አድርጋ ከንፈሩን ሳመችው፡፡ እምጿ...

በሁኔታው ሚልክያስ ቢደነግጥም ደስ ብሎታል! ደግማ ብትስመው ሁሉ ደስተኛ ነው! ለካ የሚጣፍጥ ከንፈርም አለ ወይስ የተቀባችው የከንፈር ቀለም ይሆን?... እርግጠኛ አይደለም፡፡

" በጣም ይቅርታ ! አንዳንዴ ራሴን መቆጣጠር አልችልም"

"ምንም አይደለም"

ከወንበሩ ተነሳ፡፡ እያወሩ ወጡ፡፡ መኪናው ውስጥ ገቡ፡፡ ሆቴሉ በራፍ ላይ አወረዳትና መኪናዋን ወደ ቀኝ ይጋልባት ጀመረ፡፡

*           *           *

ሄላሪ በቀስታ እየተራመደች ከራሷ ጋር ታወራለች፡፡ ከህሊና ዋ ጋር!

'እና ምን ወሰንሽ'

'ግራ ገብቶኛል'

'ከሚልክያስ እኮ ፍቅር ይዞሻል በዚያ ላይ እንደሚልክያስ ትህትና ያለው እርጋታ የተሞላበት ... ጨዋ ...ቅን ልብ ያለው ለሰው አዛኝ የሆነ ወንድ ማግኘት አስቸጋሪ ነው'

'እና '

'እንዴ ምን እና አለው'

' አልገባኝም'

' ጠበቅ አድርጊው አንድን ነገር ከልብ የምትፈልጊው ከሆነ ያንቺ ማድረግ ትችያለሽ! በዚያ ላይ ሚልክያስ ልቡ ስስ ስለሆነ ያንቺው ማድረግ አያቅትሽም

' እንዴት'

'ምን እንዴት አለው? ሚልክያስ እኮ ፍቅረኛ የለችውም! ነፃ ወጣት ነው! በዚያ ላይ አልወድሽም ወይም ልወድሽ አልችልም አላለሽም!!... ስድስት ዓመት ብቻዬን መሆን እፈልጋለሁ ነው ያለው... ስለዚህ ስድስቱን ዓመት መጠበቅ ነው... ስድስት ዓመት ምን አላት... ስለዚህ ይልቅ ፈጠን በማለት ሚልክያስን እስከ ስድስት ዓመት እንደ ምትጠብቂው ንገሪው! ስለ ፍቅር ስትይ አላማውን እስከ ሚያሳካ እንደ ምትጠብቂው አስረጂው'

'ስድስት ዓመት ሙሉ መጠበቅ የምችል ይመስልሻል! በጣም ብዙ እኮ ነው'

'ከልብሽ የምታፈቅሪው ከሆነ በፍቅር ውስጥ የማይቻል ነገር ጨርሶ የለም! ፍቅር ተራራውን መሬት የማድረግ ከፍተኛ ኃይል ይሰጥሻል! ፍቅር በታላቅ ወኔ! በሞራል! በጥንካሬ! በተስፋ ... ይሞላሻል! በዚያ ላይ ሚልክያስ እኮ ያለሽ አልወድሽም አይደለም! አብሬሽ የፍቅር ሕይወትን ብቋደስ ደስ ይለኝ ነበር ነው... ይህ ማለት እኮ ከስድስት ዓመት በኋላ የምትጠብቂኝ ከሆነ ያንቺው ለመሆን ዝግጁ ነኝ! ደስተኛ ነኝ! እኔም እወድሻለሁ! አፈቅርሻለሁ! አንቺ የተፈጠርሽው ለኔ ነው ፤ እኔም የተፈጠርኩት ላንቺ ነው! ማለቱ ነው'

' እውነትሽን ነው?'

'እውነቴን ነው '

' ሰድስት ዓመቱን በትዕግስት ልጠብቀው?'

' በእርግጠኝነት! ምክኒያቱም አንቺ የተፈጠርሽው መሬት ላይ ነው:: የምትኖሪውም መሬት ላይ ነው:: መጨረሻሽም መሬት ላይ ነው!! በለሱን የጠበቀ ፍሬውን ይበላል ሲባል አልሰማሽም? እውነተኛ አፍቃሪ ተስፋ አይቆርጥም! ፍቅር ይታገሳል! ስለዚህ ከስድስት ዓመት በኋላ የደስታ ሕይወት ለመኖር ሚልከያስ አላማውን እስከሚያሳካ በትዕግስት እንደምትጠብቂው ንገሪው!! አስረጂው!! ቶሎ ተስፋ መቁረጥ የተሸናፊነት ምልክት ነው!! ስለዚህ አሁኑኑ ደውይለት ... የፍቅርሽን ብዛት ምን ያህል እንደሆነ አስረጂው!!'

' አመሠግናለሁ'

'እኔም ምክሬን በመስማትሽ ከልብ በጣም አመሠግናለሁ '

ሄላሪ በደስታ ሳቀች::

የነገውን በማሰብ ከት ብላ ሳቀች::

# 19

ሚልከያስ ድንገት መኪናዋን የመንገዱን ጠርዝ አስይዞ አቆማት... በረጅሙ ተነፈሰ... ከሀሊናው ጋር ይነታረክ ገባ ... ስለካትሪን የፍቅር ጥያቄ አውጠነጠነ... ስለ ሄላሪ የፍቅር ጥያቄ አውጠነጠነ... በዝምታ ለግማሽ ሰዓት ያህል ከመኪናው ውስጥ እንደ ተቀመጠ ስለ ፍቅር እና ከዓመቶች በኋላ ስላቀደው ታላቅ ህልሙ አውጠነጠነ... ምንም የተለየ ነገር ሊመጣለት ሆነ ሊታየው አልቻለም።።

'አታመንታ -ማመንታት ትልቅ የውድቀት መነሻ ነው!! እንዳንተ ትልቅ ራዕይ እና አላማ ያለው ሰው ፊት ለፊት እንጂ ወደ ኋላ አይመለከትም!! ባንተ ሕይወት ውስጥ ዓላማህን ከማሳካትህ በፊት ለፍቅር ሆነ ለሴት የሚሆን ቦታ የለም! ሚልከያስ በቃ በውሳኔህ የፀና ሰው ሁን!! በዚያ ላይ ላንተ የሚያስፈልግህ እንደ ሄላሪ ያለች ሽቅርቅር... ቅርብ አሳቢ ... በትላልቅ ውድ ሆቴሎች ብቻ የምትዝናና... አይነት ሴት ሳትሆን እንደ አንተ ለግላዊ ህይወት ሳይሆን የበርካቶችን ሕይወት ለመለወጥ ትልቅ ጥረት እና ህልም ያላት! ሩቅ አሳቢ! ባለ ትልቅ ተስፋ! የቀለም ቀንድ የሆነች የተለየች ሴት መሆን አለባት... ያቺን ደግሞ አንድ ቀን ታገኛታለህ... ብዙዎች ትላልቅ ሀሳብ እና ራዕይ ያላቸው ሀሳባቸውን ሳይጨርሱ ከመንገድ የቀሩት ፍቅር ... ትዳር ... ቤተሰብ... ወዘተ በሚል ማህበራዊ ቅብርጥሶ ተጠላልፈው ነው።። ስለዚህ ሚልከያስ ጠንከር በል ወደ ኋላ አትመልከት! አሸናፊዎች ምንግዜም እንቅፋት ሲገጥማቸው ተራምደውት ያልፋሉ! እንደ አንተ ትልቅ የተለየ ህልም እና ራዕይ ያላቸው ወንዶች ቆራጥ መሆን አለባቸው በዚያ ላይ በግልፅ እንደ ተነገረህ እና አምነህበት እንደ ገባህበት ለፍቅር ሆነ ለሴት ቦታ መስጠት የለብህም! ቀጥለው በሚመጡት ስድስት ዓመቶች ትልቁን ሀላፊነትህን እስከምትጨርስ ድረስ በአንተ ሕይወት ውስጥ ለግላዊ ሕይወት ! ለግላዊ ደስታ! ለግላዊ ሀሴት! ለግላዊ ስሜት የሚሆን ቦታ የለም... አስታውስ በዓለም ላይ ለታላቅ

አላማ ታላቁ ሚስጢራዊ ድርጅት የሆነው E.B.F.W ታላቁን ተልዕኮውን በዓለም ላይ ለማሳካት ከ124 ሀገራት በከፍተኛ ሚስጢር ከመረጣቸው 200 ወጣቶች አንደኛው አንተ ነህ!! ይህን ከቶ አትርሳ! በዚህ ዓለም ላይ ታላቅ ለውጥ ለማምጣት ከሚሠራው ልዩ ድርጅት የሚሰጠውን እና የጀመርከውን ልዩ ትምህርት ተምረህ ሳትጨርስ! አገልግሎት ሳትሰጥ ... ቃል የገባኸውን ብታጥፍ...'

ሚልኪያስ ለ E.B.F.W ከሁለት ዓመት በፊት የመግቢያ ፈተናውን በከፍተኛ ውጤት በማምጣት ሲያልፍ በታላቅ ፈገግታ እና ወኔ ተሞልቶ የፈፀመው ቃለ-መሀላ አንቃጨለበት... ቃሉን መጠበቅ እንዳለበት 100% ወሰነ:: መኪናዋን አስነስቶ ወደ ፊት ያከንፋት ጀመር::

# 20

## ድህረ-ታሪክ -እንደማስታወሻ

ሕይወት ቀጥላለች… የሚልክያስ … ማርያማዊት… መኑ… ሙሉጌታ… ሄላሪ … ካትሪን… ታሪክ መጨረሻው ምን ሆነ… ከ1998-2006 ያለው ታሪክ ምን ይመስላል? …በሕይወት ጉዞ ከአምስት ደቂቃ በኋላ ምን ሊፈጠር እንደሚችል በእርግጠኝነት መናገር የሚችል ከቶ አለ ይሆን?… ለማንኛውም አ… ዘንደኪ አላለቀም… ክፍል ሁለት ይቀጥላል … እስከዚያው ውድ ተደራሲያን የምንሰነባበተው በምርቃት አንድ እና በምርቃት ሁለት ይሆናል … ቸር ንባብ።

# ምርቃት

# 1

ስለ ጓደኝነት ምን ተባለ?

በጣም በጥቂቱ ...

A Friend is one who knows us, but loves us anyway.

Jermome Cummings

Only your real friends tell you when your face is dirty.

Sicilian

What is a friend? I will tell you ... it is someone with whom you dare to be yourself.

Frank crane

A good friend remembers what we were and sees what we can be.

(unknown)

A real friend is one who walks in when the rest of the world walks out.

Walter Winchell.

The only way to have a friend is to be one.

Reiph waldo Emerson

A mirror reflects a man's face, but what he is really like is shown by the kind of friends he chooses.

Proverbs 27:19

A friends loves at all times.

Proverbs 17:17

Every gift from a friend is a wish for your happiness.

Richard Bach

A friend heart the song in my heart and sings it to me when my memory fails.

(unknown)

Friendship doubles your joys, and divides your sorrows.

Love is temporary ... but friends are forever.

Kelly wheeler

Walking with a friend in the dark is better than walking alone in the light.

Helen keller

A friend in need is a friend indeed.

Latin proverb.

Friends are one soul in two bodies.

Aristotle

Reprove your friends in secret, praise them in public.

Unknown

One friend in a life time is much, two are many , three are hardly possible.

Henry Adams.

እግዚአብሔር ከጓደኞቼ ጠብቀኝ እኔ ራሴን ከጠላቶቼ እከላከላለሁ::

(ማርሻልዲ ቪላርስ)

- አድልህ የተሳካ እንዲሆን ጓደኛ ያስፈልግሀል በጣም የተሳካልህ እንድትሆን ደግሞ ጠላት ያስፈልግሀል (ሲድኒ ሽልደን)
- ለሁሉም ሰው ደግ ሁን ግን ጓደኛ ምረጥ (አስከራተስ)

- ጓደኛህን እስከተወሰነ ደረጃ ድረስ ውደደው ምን አልባት አንድ ቀን ጠላት ሊሆን ይችላልና (ያልታወቀ)
- የሴት ጓደኛ ካለችህ ሚስጢር ከቶ አትንገራት (ሄነሪ ዋላርን)
- ጓደኛ በአትክልት ቦታ የሚበቅል ውብ አበባ ነው::
- ብዙ ጓደኛ ያለው ሰው አንድም የልብ ጓደኛ የለውም::
- የእኔ ውድ ጓደኛ የማነበውን መፃፍ የሚሰጠኝ ሰው ነው :: (አብርሃም ሊንከን)
- ጥሩ ጓደኛ ከእንቅልፍ ቀስቅሶ የሚጋብዝ ነው::
- ጓደኛ ያለ አቅምህ አትያዝ የተጣላህ እንደሆነ የጠርሙስና የብረት ግጭት እንዳይሆን::
- በጓደኝነት ላይ ከተመሰረተ ቢዝነስ ይልቅ በቢዝነስ ላይ የተመሰረተ ጓደኝነት ይሻላል::

  (ደንዲ ፎካፌለር)
- እውነተኛ ጓደኞች ያሏቸው ሀብታሞች ናቸው

  (ቶማስ ኤፍ)
- አንድ ታማኝ ጓደኛ የ10ሺ ዘመዶች ያህል ዋጋ አለው::
- እውነተኛ ጓደኛ ጓደኛ ብቻ ሳይሆን የተሟላ እድል ነው::
- ጓደኛ ከመምረጥህ በፊት ልቡ ውስጥ ምን እንዳለ አጥና ::
- እውነተኛ ጓደኛ የማይጠፋ ብርሃን የማይቀልጥ ሻማ ነው::

## አደገኛ ሁኔታ ላይ የወደቀ ጓደኝነት እንዴት ሊታደስ ይችላል?

ከ Reader's digest June 1999

- ኩራትን ያስወግዱ ... ራስ ወዳድ አይሁኑ
- ተበድለው እንኳን ቢሆን ይቅርታ ይጠይቁ
- ነገሮችን ከጓደኛዎ ዕይታ አንጻር ይመልከቱ
- ጓደኝነት እንደሚቀየር ይመኑ... ለምሳሌ ፍላጎታችንና አኗኗራችን ሲለወጥ ጓደኝነትም ይለወጣል
- ብዙ ጓደኞች ቢኖርዎትና አንዱ /ዷ ወይም ሌላው/ዋ በአንድ ወቅት እንደ አኗኗራቸው ጓደኝነታቸውን ቢቀይሩ ምንም አይገረሙ በጸጋ ተቀበሉት
- አንዳንድ ጊዜ ጓደኛ መፍጠር ቀላል ይመስላል፤ ከባዱ ነገር ሁሉንም ግንኙነቶች በሚያውከው ተፈጥሯዊ የሕይወት ውጣ ውረድ የተነሳ ትስስሩ እንዳይላላ ማድረግ ላይ ነው፡፡ ስለዚህ ጓደኝነትን እንደ ክብርና ስጦታ ቆጥረው ለማበልጸግና ለማለምለም ይትጉ፡፡

## ሀገራትስ ስለ ጓደኝነት ምን አሉ?

### አርመን

- ጓደኛ እራስህን ሲያይ ጠላት እግርህን ያያል
- ከጓደኛህ ጋር አብረህ ብላ ግን አብኸው ንግድ አትዋል
- እንከን የሌለው ጓደኛ የሚፈልግ ምንግዜም ጓደኛ አያገኝም
- ጓደኝነት በአፍ ብቻ አይወለድም
- ጓደኛህ ማር ቢሆን እንኳ አትላሰው

### አፍጋኒስታን

- ከሞኝ ጓደኞች ጋር ሰላም ከመፍጠር ይልቅ ከብልህ ጠላት ጋር ጦርነት መግጠም ይቀላል

### አልባኒያ

- ጓደኛውን ለማስደሰት መነኩሴ ሚስት ያገባል
- ከጓደኛህ ቤት ከሆንክ መጥፎ ጊዜ ሁሉ ይረሳል

## ካሜሮን

- እውነተኛ ጓደኛ ከወንድም ይበልጣል

## ቼክ ሪፐብሊክ

- በቀልድ ብዙ ጓደኝነት ጠፍቷል በቀልድ ግን የተገኘ የለም፡፡
- እራስህን በአጥር ሳይሆን በጓደኞችህ ተከላከል

## ዴንማርክ

- የጓደኛ ቤት መንገድ ምን ጊዜም እሩቅ አይደለም

## ግብፅ

- ጓደኝነት ደስታን እጥፍ ያደርጋል፣ ሐዘንን ይገምሳል
- ከጓደኛ ጋር የተካፈሉት ሽንኩርት እንደ በግ ጥብስ ይጣፍጣል
- ጓደኛህን ለጓደኛህ የምታማ ከሆነ ጓደኛ አይኖርህም!

## ፊንላንድ

- በቦርሳህ ወርቅና ብር ከሚኖርህ ይልቅ ስትጓዝ ጓደኛ ይኑርህ
- በጓደኞችህ ከመታለል ይልቅ ጓደኞችህን መጠርጠር የበለጠ የሚያሳፍር ነው
- ጓደኝነት ክንፍ የሌለው ፍቅር ነው
- በጓደኝነት ጎዳና ሳር አይብቀልበት
- የታላቅ ሰው ጓደኝነት እንደ ቁጥቋጦ ጥላው ቶሎ ይጠፋል
- ጓደኛ የሌላት ሴት ልጅ ፅጌሬዳ እንደሌለበት ፀደይ ናት
- ለጓደኛው የሚያበድር ሁለት ጊዜ ያጣል

## ጋቦን

- መጥፎ ጓደኞች ጥሩ ጓደኞች እንዳይኖሩህ ይከለክሉሃል

## ሐዋይ

- ጓደኝነት በየጊዜው ውሃ መጠጣት እንዳለበት አትክልት ነው

## ግሪክ

- የተሳካለት ብዙ ጓደኞች አሉት
- ራስ ወዳድ እና ውሸታም የማንም ጓደኛ ሊሆን አይችልም
- ጓደኛ እና እውነተኛ ጓደኛ የብርሃን እና የጨለማ ያክል ልዩነት አላቸው::
- በገንዘብ ከመጣ ጓደኝነት ብቸኝነት ይበልጣል

## ዕብራይስጥ

- ጓደኛህ ጓደኛ አለው የጓደኛህ ጓደኛም ሌላ ጓደኛ አለው ስለዚህ ዝም ማለትን ተማር
- ሁለት ጓደኞች ሲለያዩ የያንዳንዳቸውን ሚስጢር ቆልፈው መክፈቻውን መወርወር አለባቸው
- ሰውን ጓደኛ ከማድረግህ በፊት ጨው አብረኸው ብላ
- ችግር ባጋጠመህ ጊዜ ጓደኞችህ እነማን እንደሆኑ እወቅ

## ህንድ

- ጓደኛህ አህያ ከሆነ ከእርግጫ በስተቀር ሌላ ነገር አትጠብቅ
- ጓደኛ ግጥም ነው

## ኢራን

- ጥሩ ጓደኞች እስካሉኝ ድረስ እሻሻላሁ

## አይቮሪኮስት

- ጓደኛ ላብ ይጠርጋል እንጂ ደም አይጠርግም

## ኢራቅ

- ጓደኞችህ እነማን እንደሆኑ ንገረኝ አንተ ማን እንደሆንክ እነግርሃለሁ

## አየርላንድ

- የጓደኛ ዓይን ጥሩ መስታወት ነው

## ጣሊያን

- የቆዩ ጓደኞች ሁልጊዜ አዲስ ናቸው
- ከሙቶ ዘመዶች አንድ እውነተኛ ጓደኛ ይሻላል
- የጓደኛህን ሙገሳም ይሁን የጠላትን ንቀት አትመን
- ለጓደኛህ አሳማ ለጠላትህ ኮክ ስጥ
- የቄስ ጓደኛ እምነቱን፣ የሃኪም ጓደኛ ጤንነቱን፣ የጠበቃ ጓደኛ ሀብቱን ያጣል

## ጃማይካ

- ጓደኛ በሚያስፈልግህ ጊዜ ጓደኛ አብጅ
- ጓደኞችህ እነማን እንደሆኑ ማወቅ ከፈለክ መንገድ ዳር እንደሰከረ ሰው መስለህ ተኛ

## ጃፓን

- ከጓደኛ ጋር ምንም መንገድ ረጅም አይደለም

## ኬኒያ

- በጓደኛህ ጣራ መሳቅ ትችላለህ ግን በመኝታው አትሳቅ

## ማዳጋስካር

- ጓደኝነትህ እንደ ድንጋይ አይሁን ከተሰበረ አይጠገንምና፤ ነገር ግን እንደ ብረት ይሁን ከተሰበረ ይጠገናል

## ናይጀሪያ

- እውነተኛ ጓደኞችህን በሁለት እጅህ ያዝ

## ራሺያ

- ጓደኛ ማበጀት የማይሻ የራሱ ጠላት ነው
- አንድ ሺህ ጓደኛ ጥቂት ነው አንድ ጠላት ብዙ ነው
- ከተኩላ ጋር ጓደኛ ሁን ግን መጥረቢያህን አዘጋጅ

## ሴኔጋል

- ከደደብ ጓደኛ ብልህ ጠላት ይሻላል
- እውነተኛ ጓደኞችህ ብቻ ናቸው ፊትህ መቆሸሹን የሚነግሩህ

## ሶማሊያ

- ጓደኛ አልባነት በእውነትም ድህነት ነው

## ስፔን

- የሁሉም ጓደኛ የሆነና የማንም ጓደኛ ያልሆነ አንድ ነው
- የታረቅከውን ጓደኛና ዲያቢሎስን ተጠንቀቅ
- ለጓደኛህ ውሸት ንገረው ምስጢርነቱን ከጠበቀ እውነቱን ንገረው
- ጓደኛ ሲኖር ጥሩ ነው ገሀነብ እንኳ
- ጓደኛ የሌለበት ህይወት ምስክር የሌለበት ሞት ነው

## ስዊድን

- ጓደኛህን በቀን ምረጥ!

## ታጂኪስታን

- ጓደኛህ ሌላ ጓደኞች ካሉት ምስጢር አትንገረው

## ማሊ

- እውነተኛ ጓደኛ በአጋጣሚ የሚፈጠር ሳይሆን የእግዚአብሔር ስጦታ ነው
- ከጠላት ጋር ከመሳቅ ከጓደኛ ጋር ማልቀስ የተሻለ ነው

## ብራዚል

- እውነተኛ ጓደኛ ግማሽ እግዚአብሔር ነው::
- ለጓደኛ ስጦታን ሰጥቶ ሌላ ስጦታ መጠበቅ ጥቅም ፈላጊነት ነው::

# ምርቃት
# 2

# 4 ለ0

# (እውነተኛ ታሪክ)

ይህ የምነግራችሁ ታሪክ እውነተኛ ነው፡፡ የፈጠራ ታሪክ እንዳይመስላችሁ... ከየት መጀመር... እንዴት መጀመር... እንዳለብኝ አላውቅም... ምን መፃፍ እንዳለብኝ ራሱ አላውቅም... ለምን እንደምፅፍም እርግጠኛ አይደለሁም... ብቻ ሆነ ... ተፈፀመ... ለምን ተፈፀመ?... አላውቅም፡፡ ግራ ተጋብቻለሁ ... ተጨንቄያለሁ... ምን ማድረግ እንዳለብኝ ተምታቶብኛል... አሁን እኔ ጋር ሁሉ ነገር ተረት ነው ሁሉ ነገር ጨለማ ነው... አሁን እኔ ለነገ መጨነቅ ትቻለሁ... ውይ ግራ ተጋብቻለሁ ነው እኮ እያልኳችሁ ያለሁት ... ለመሆኑ ጤነኛ ነኝ... አላውቅም... እንዴት እንደማስረዳችሁ ነው ግራ የገባኝ ...ድብልቅልቅ ያለ ስሜት ውስጥ ነኝ ያለሁት ... አሁን ስለምንም ነገር አይጨንቀኝም ... ኡፍ...

ምንድነው ያስጨነቀህ? ስለምንስ ግራተጋባህ? ስለምንስ ልብህ በሀዘን ተሞላ? ስለምንስ ትካዜህ በዛ... ስለ ምንስ በጭንቀት ተወጠርክ? ስለምንስ አዕምሮህ ተናወጠ... ልትሉኝ እንደምትችሉ እገምታለሁ...

አሁን አንዲት መጠጥ ቤት ውስጥ ነኝ እየጠጣሁ ነው ... ሲጋራዬንም በላይ በላዩ እያቦነንኩ ነው አሁን የኔ ምርጥ ጓደኛ መጠጥ እና ሲጋራ ሆነዋል ...ይህ ሁሉ የሆነው በጓደኞቼ ነው... ጓደኞቼ አራት ናቸው...

♡ ዳንኤል

♡ ህሊና

♡ በረደድ

♡ መሀመድ

ከማን እንደምጀምር እንዴት እንደምጀምር አላውቅም... አንድ ደራሲ ነገር ባገኝ ከልጅነት እስከ ዛሬዋ ያለውን ታሪኬን ፍርጥርጥ አድርጌ ብነግረው በእርግጠኝነት የኔ ታሪክ ምርጥ ድርሰት አልያም ፊልም ይወጣዋል... ግን የማውቀው ደራሲ የለም... ብቻ ውስጤ የታመቀው የእሳት ነበልባል ቢያንስ እንዲቀንስልኝ ራሴ የቻልኩትን ያህል ልተንፍስላችሁ...

ምክንያቱም አሁን ተጨንቄያለሁ... ግራ ተጋብቻለሁ.... ሰሞኑን የማስበው ራሴን

እንዴት መግደል እንዳለብኝ ነው… እስቲ የቻልኩትን በጣም በትንሹ ልተንፍስላችሁ … ከዳኒ ልጀምር

ዳ

ን

ኤል…

አይ ዳኒ … ዳኒ በጣም ሚስኪን ሰው ነው … ለሰው በጣም የሚጨነቅ ሰው ነው… ይሉኝታ በጣም የሚያጠቃው ሰው ነው… ከዘጠነኛ ክፍል እስከ ዩኒቨርስቲ አብረን ተምረናል… ዳኒ ከሁላችንም የሀብታም ልጅ የሆነው እርሱ ነው … ዳኒ ይስቃል … ዳኒ መሣቅ ይወዳል … አይዳኒ በጣም ሚስኪን ሰው ነው … ዳኒ ምክር መቀበል እንጂ መምከር አይወድም … ዳኒ ለራሱ ሳይሆን ለሌሎች የሚኖር ሚስኪን ሰው ነው… ዳኒ ገንዘብ ላይ ግን በጣም ገብጋባ ሰው ነው… ዳኒን እንደፈለጋችሁት መንዳት የምትችሉት ሰው ነው… በጣም ሚስኪን ገራገር ሰው ነው … በይሉኝታ በጣም የታጠረ ሰው ነው… ዳኒ ጠይም አጭር ሰው ነው… ወፍራም ቢጤም ነው … ፍንጭት ጥርስ አለው ትልቅ ጆሮ አለው.. ዳኒ ከዚህ በላይ ታሪክ የለውም.. ከሁለት ወራት በኋላ ግን ሲያገባ ሽርጉድ እያለ ነበር… ሚስት ሊያገባ እቅድ ላይ ነበር …

በ

ረ

ደ

ድ

በረደድ… በሬ እንለዋለን … በሬ ለሁሉ ነገር ፈጣን ነው … ቀልቃላ ነው … በሬ ምንንም ሆነ ማንንም አይፈራም … ይሉኝታ የሚባል ጨርሶ የለውም … በሬ በጣም ባለጌ ነው … በሬ የሳቃችን ጎተራ ነው … በሬ የቀልድ መፅሐፍትን ያነባል … ፊልም እያሳደደ ያያል… በሬ ሴት መብዳት በጣም ይወዳል … በሬ ምንም የሚፈራው ነገር የለም … በሬ እግዜርን ራሱ አይፈራም 'እግዜር ቢኖርም ባይኖርም የራሱ ጉዳይ ነው! እኔ ምን አገባኝ

ከሞትኩ በኋላ አይጨንቀኝም! ስለማላውቀው ገነት ሆነ ሲኦል መጨነቅ አልፈልግም ይላል... ከበሬ ጋር የተዋወቅነው ዘጠነኛ ክፍል ስገባ ነበር ... ራሱ ነው መጥቶ የተዋወቀኝ

" ማነው ስምህ" አለኝ

" ኤፍሬም"

" እህ ጥሩ ስም ነው! በረደድ እባላለሁ... ከፈለክ ጓደኛ መሆን እንችላለን"

" ደስ ይለኛል" አልኩት

በሬ ነው ከዳንኤልም ... ከህሊናም ... ከመሀመድም ጋር ያስተዋወቀኝ ... በሬ አስተማሪ ክፍል ሲቀር ያስቀናል ... የብልግና ቀልዶችን ብቻ ይነግረናል ... በሬን ሴቶች በጣም ይወዱታል ... ስፍስፍ ይሉለታል... እኔም እንደበሬ ለመሆን አስቤ ነበር፤ ነገር ግን አልተሳካልኝም ... በሬ ከሺ በላይ የብልግና ቀልዶች ነግሮናል... ቢያንስ ሶስቱን ብቻ ላካፍላችሁ...

አህያና ጅብ ፣

" አንድ ጊዜ አህያና ጅብ ሊባዱ ተራራ ላይ ወጡ:: ዕጣ ሲጣጣሉ መጀመሪያ የመብዳት ተራውን ጅብ ደረሰው ... ጅብ እየተደሰተ አህያ ቂጥ ውስጥ አነስ ያለችውን ቁላውን ገባ ወጣ ... ወጣ... ገባ... እያደረገ ጨረሰ:: ከዚያላችሁ የአህያ ተራ ደረሰና ጅብ በተራው ለአህያ ቂጡን አፈነደደለት... አህያ ያንን ግዙፍ ረጅም ቁላውን የጅብ ቂጥ ውስጥ ቀረቀረለት አህያው

'አንተ ግማታም አህያ እኔ እኮ የበዳሁህ በቁላዬ ነው አንተ የምትበዳኝ በእግርህ ነው እንዴ?' በማለት ተናግሮ ሞተ:: ይባላል... አያስቅም' ይልና እኛ ሳንስቅ ራሱ ከትብሎ ይስቃል ... ከዚያ ሁላችንንም እየተመለከተ "ከዚህ የምንማረው አቅምን ማወቅን ነው" ይለናል::

## አህያና ሴት

" አንድ ጊዜ አንዲት የ17 ዓመት ድንግል ሴት ልጅ ከእናቷ ጋር አትክልት ገበያ ሄደው ሳለ ልጅቷ አህያው ረጅም ቁላውን አህያዋ ቂጥ ውስጥ ሲከተው ትመለከትና በጉጉት

`ወይ! ምነው ለኔ ባደረገው` ትላለች:: እናቷ የተናገረችውን ሰምተው `ምኑን ነው የኔ ልጅ` ይሏታል ልጅቷ አይና የአህያው ቁላ ላይ እንደተተከለ - ለእናቷ በምልክት ታሳያታለች ፤ እናቷ አህያው ረጅም ቁላውን ገባ ወጣ ... ገባ ... ወጣ... ሲያደርግ ተመለከቱት:: መረቀነች:: ወዲያው ልጇን በሀይለኛ ጥፊ ሞላችባት... ልጅቷ ደንግጣ

`ምነው እማ?` ስትላት `ገብጋባ! ምን አባሽ ነው ለኔ ባደረገው የምትይው? ምነው ለእናቴ ባደረገው አትይም` አለቻት ... አያስቅም ... ይልና ከዚያ ሁላችንንም እየተመለከተ "ከዚህ የምንማረው ሴቶች ቁላ ምን ያክል እንደሚወዱ ነው" ይለናል::

## ሰውየውና በግ

"አንድ ሰውዬ በግ የመብዳት ሱስ ተጠናውቶታል:: እናም ማታ ማታ እየተደበቀ ጎረቤቱ በረት እየሄደ በጎቹን ይበዳበታል....አንድ ምሽትም ራቁቱን በጨለማ በረቱ ውስጥ በመግባት እንዷን በግ እየበዳ ሳለ ሳይታሰብ የበጎቹ ባለቤት የሆነው 150 ኪሎ የሚመዝነው ሰው በረቱ ውስጥ ይመጣል... ሰውየው ደንግጦ ከበጎቹ መሀከል እንደበግ በመሆን ተንበርክኮ ይቀመጣል... የበጎቹ ባለቤት ለካ ራሱ በግ የመብዳት ሱስ ያለበት ሰው ነው ... ከበጎቹ መሀከል በጨለማው በረት ቤት ቂጣቸውን እየዳበሰ ... እያማረጠ.. ሰውየው ጋር ሲደርስ እየተደነቀ

`ደግሞ ይቺ ምን አይነት ለየት ያለች በግ ናት! ላት ደግሞ የላትም እንዴ?` በማለት ቂጧን ይዳብስና ተንበርክኮ... ሰውየውን በቂጡ ላከበት ... ሰውየው እሪ ሲል ጮኸ ... አያስቅም ... ያስቃል" ከዚያ ሁላችንንም እየተመለከተ `ከዚህ የምንማረው እበዳለሁ ሲሉ መበዳትም እንዳለ ነው` ይለናል...

በሬ ከፍተኛ የፊልም ፍቅር አለው! ለትወና ከፍተኛ ጉጉት አለው ... ዩኒቨርስቲ ገብቶ የተመረቀው በትያትሪካል አርት ነው ... በከፍተኛ ውጤት ነበር የተመረቀው .. በሬ የኢንግሊዝኛ ፊልም ይወዳል... በሬ የህንድ ፊልም ይወዳል ... ያየውን ፊልም ይተርክልናል ... ደግሞ አቤት የትረካ ብቃቱ ... አቤት መተረክ መቻሉ! አቤት የሚያደርገው የሰውነት እንቅስቃሴ ... ከበሬ ጋር እጅግ ድንቅ የሚባሉ ፊልሞችን አይተናል ... እስቲ እናተም ተመልከቷቸው ... Tad pole... proof of life ... one the line

ዋው በጣም ምርጥ አስገራሚ የፍቅር ታሪክ! መኪና ውስጥ ለአምስት ደቂቃ አብሮዋት ከተቀመጠች ውብ ወጣት ፍቅር ይይዘዋል... አሷን ለማግኘት ... Man on fire... the last American Virgin ... the Animal ... Nine months በጣም አስቂኝ ፊልም በተለይ አርጉዝ ለሆነች ወጣት ... የዘጠኝ ወር ጣጣ... የዕርጉዝ ምኞት ... Kung power ... First knight... the hot click .. Anger management ... some one like you ...French kiss ...hide and seek ... caplella ዋው በጣም አስደሳች የሆነ የፍቅር ፊልም ሶስት ጊዜ ነው ያየሁት ... Zion... Guru.. A Guy think ... blood sport ... Taal... American out laws... God must be creasy part 1,2,3,4...5 ... Kirshna ... the Quest... the Hasshoor... love does not cost a thing ... lagan ድንቅ እውነተኛ ታሪክ .... City of Angles... kal hand ... Mr bones... Rapid fire ... akele hum Akelel tum ዋው በሕይወቴ ለመጀመሪያ ጊዜ ያለቀስኩበት ፊልም ኧረ በጣም ብዙ ናቸው ... የወሲብ ፊልሞች ራሱ እናይ ነበር ... በሬ ... የመጀመሪያ ምርጥ ፊልሙን ከሁለት ወራት በኋላ ለመስራት 20 ሺ ብር ቀብድ ተቀብሎ ነበር... ለማንኛውም ስለ በሬ እዚህ ላይ ላቁም...

መ

ሀ

መ

ድ

T... ዘናጭ ነው ... ውብ ነው ... ንግግር አዋቂ ነው... ፈጣን ጭንቅላት አለው ... በጣም ተንኮለኛ ነው... ሴቶችን በጣም ይጠላልም... በጣም ይወዳልም... ቁንጠኛ ነው... የእንግሊዝኛ ብቃቱ የትየለሌ ነው:: አባባል ይወዳል ... ተንኮል መስራት ይወዳል ... አንድ ጊዜ ሠርግ ቤት ሄደን የሀብታሞች ሠርግ ነው ... ለዚያውም ሳንጠራ ነው ... ጥብስቅ አድርገን በልተን ወጣን ... ስንወጣ በጣም ፈዘዘ

ምንድነው አልማዝት

• የሚጠመንበውን ተመሬስታችሁ አለኝ ተመለስቶታችሁ:: ሀመር መኪና ነበር ። ትዝታ ቀን በመር መኪና መመሪያ አይታርጊም፤ ሀመር መንዳት አይታርጊም የለሀመሬ በሆ መኪናዎን የሠርግ ቤቱ በር ላይ አቆመ:: መሀመድ እየርጠ ሄደና

• ጂጂ እንከጠብቃት መኪናዋን አለው:: ሰውየው

• እንቱ ሳትፈልግ የተወለደቺ ሴታል ጊዜ ከዚህ ጥፋ!" በማለት በቁርጥም ተናገርበው:: መሀመድ ተጋፋሪ::

• እዚያ ሠርቶቹን በዶማት እመልሳለው"

አሮችና በዶማት ተባወረ:: ከአምሳት ደቂቃ በኋላ ተመልሶ መጣ:: የእኝ እንግዳት ቤቱ ደረሰሩ:: መኪናው ጋር ሄደና የሀመሩን በር መክፈቻ እጁን ውስጡን የያዘውን ነበር ሄደው::

• ምንድ ነው? አልማዝት በርቀት ሆኗ::

• አር ነው!! አሬን አርጄ መኪና በር መክፈቻውን ቀየሁት!! እኔን አይደለም ሴታል ደብና ለውጤው አለበሚገባው ድረስ ያንን የቁጡን እያወሩን ሩቀ ተቀምጠን መበቅነው:: በሩን ለመክፈት እጁን አስገባ ... በግራ መጋለት እጁን ተመለከተው ... ሸተተው...

• ሰውሬን እዚህ ሴታሎቹ አይበ ቀውጢ አደረገው:: እናና መሀመድ በጣቅ ፈረሰን ... መሀመዱ ለሰሌቶች ብዙ የነርሽ አርሱ ነው ... በርካታ ሴቶችን እየፎገረ በድንቡ ... በተለይ ቅሬርሱ እያለንም ሬጃቸው ነው የሚባለው እትትት ይላቸዋል... በጣም ከሚገርሙኝ ነር ሴቶች ለምን ወሬን ወገኑ እንደሚወዱ ነው ያስታችቀል ...እንደሚወዱቸው ይነግራቸዋል እትትት ... ይላቸዋል... ይለዩቸዋል... ያሠወርሳቸዋል... የመጀመሪያ ዓመት ተማሪ እያለን እናቴት ሬጅ ተቀውቆ በጋታው ከአደናቂ ጋር መጣች... በእነሱ ቤት ለስሉት ነበር ... ለሁለት ቅርጥም ለያይርጉት ...

• በጣም አለኝ

• እሺ አልማዝት

"ባከህ ያቺኛዋ ደረቅ ነገር ናት ጓደኛዋ ታሻፍዳለች ስለዚህ አንድ ፈበር ስራልኝ"

"ምን" አልኩት

" ለአንድ ቀን ብቻ አብረኸት ዋል"

"ምን ማለት ነው?"

" እሱን ከጉዳዩ በኋላ እነግርሃለሁ" ያለኝን አደረኩለት:: ከሳምንት በኋላ

እየሳቀ

"እመሠግናለሁ" አለኝ

" አልገባኝም? ለምን"

" እሷን ለጓደኛዬ ኤፍሬም ነው ያጣበስኳት እንጂ እኔ ፍቅር የያዘኝ ካንቺ ነው አልኩልህና ከአንተ ጋር ተቀምጣ አሳየዋትና ወስጄ በዳዋት እኮ ... ሁለቱንም በዳዋቸው .. ለሴቶች መራራት የለብህም ... አንድ አምስ ያስከፋ ዘጠኝ አምስ ይሸሸዋል ይላል ጋሼ .. እውነቴን እኮ ነው እንዴ አንዷ ሸፍድ ብላ ብዳኝ እያለች እንቢ ብዬ ከዚያ እኔ መብዳት አምሮኝ ዘጠኝ ሴቶችን ብጠይቅ ሁሉም የወር አበባ ላይ ነኝ አላሉኝም... ያንተም ሚስት የምታሻፍድ ከሆነ መብዳቴ አይቀርም" ... መሀመድ ፍቅር ያዘኝ ሲል ሰምቼው አላውቅም .. ሴቶች ግን ከንፍ ይሉለታል... መሀመድ አሲምቶት አይደለም ... አሲምቶት ማለት ሴቶችን በጣም የሚጠጋቸው ፡ የሚቃለዳቸው፣ የሚያዋራቸው ግን የማይበዳቸው ... ለጨረቢብ መጠየቅ የሚፈራቸው አይነት ወንድ ማለት ነው... መሀመድ ምህረት የለውም ... ይቀርባቸዋል ይጠግራቸዋል... ይበዳቸዋል... ይለያቸዋል:: አንድ ጊዜ ከ አንዲት ሴት ጋር ፍቅር ያዘኝ ቀጠርኳት :: የተቃጠርንበት ሆቴል ውስጥ ሶስት ጓደኞቿን ይዛ መጣች... የሚበላ ... የሚጠጣ አዘዙ... በቂ ገንዘብ ኪሴ ውስጥ ስላልነበረኝ ለመሀመድ ደወልኩለት

" ጉድ ሆንኩልህ" አልኩት

" ምነው?"

"በእናትህ ሶስት ጓደኞቿን ይዛ መጣች! በቂ ገንዘብ የለኝም ብር ይዘህ ናልኝ::"

"ሶስት ጓደኞቿን"

"እም"

"እዩ የኔ ሚስኪን የምትወድህ ሴት ብትሆን ብቻዋን ነበር የምትመጣው ይቺ ሙድ ልትይዝብህ ስለሆነ ቀስ ብለህ ሹልክ ብለህ ና የራሳቸው ጉዳይ ነው" አለኝ እንዳለኝ አደረኩ ... መሀመድ ጠንካራ ሠራተኛ ነው! መሀመድ ስራ አይንቅም! ሥራ ያከብራል... መሀመድ በቅርቡ የራሱን ንግድ ሊጀምር እየተዘጋጀ ነበር ...

ሀ

ሊ

ና

ሀሊና ቀይ ውብ ናት ... ያደገችው ያለ እናት በአባት ስለሆነ ይመስለኛል... የወንድነት ባህሪ በብዛት ይንፀባረቅባታል... ሀሊና ሳቅ ትወዳለች! ቀልድ ትወዳለች! ወሬ ትወዳለች... ዋው ከመሀከላትን እንደ ሀሊና አንባቢ የለም! በጣም ታነባለች... ሀሊና ፍርሀት የሚባል የለባትም... ሲበዛ ግልፅ ናት ... ሲበዛ የመሰላትን ትናገራለች... ይሉኝታ የሚባል ጨርሶ የለባትም... ለኔም፣ለዳኒም፣ ለመሀመድም፣ ለበሬውም ሁለት ሁለት ሴቶችን አስበድታለች ... ሀሊና የ15 ዓመት ልጅ እያለች ከሰፈሯ ልጆች ጋር መባዳት ጀምራ ነበር... ያልቀመሳት ሰው የለም! የህዝብ ሽንት ቤት ነበረች... ሀሊና ተጦሶለች ሬኔን ገዛላት ... መጠጥ ትጠጣለች... ሀሊናና በሬው ካሉ በመሀከላችን ሳቅ ብቻ ነው... ትረባ ብቻ ነው ... ደስታ ብቻ ነው ... ቅልጥ ያደርጉታል ... ሁለቱም ዳንስ የሚያክላቸው የለም! ሁለቱም በሙዚቃ ፍቅር ክንፍ ብለዋል ... ሀሊና እንደ መሀመድ ሁሉ በወንዶች ሙድ መያዝ ያስደስታታል ... ከወንዶች ብር እየፈለጠች እኛን ታዝናናለች ... ወንዶች ሲያለቅሱ ማየት እርካታዋን ከፍ ያደርገዋል... አባቷን በጣም ትጠላቸዋለች... ዋው የሀሊና ፀጉር ርዝመት ድንቅ ነው... ያላት ዳሌ ግዙፍ ነው ... ወንዶች ሁሉ ይሻፍዱባታል

" ወይኔ ጓደኛዬ ባትሆኚ እኮ በጣም ነበር የምበዳሽ" ይላታል መሀመድ

" እኔም እበዳህ ነበር" ትለዋለች እየሳቀች።

ሀሊና መደባበቅ የሚባል ነገር የለባትም… የመሰላትን ሳትፈራ ነው የምትናገረው… ሀሊና ዝነኛ ሰው የማግባት ከፍተኛ ፍላጎት አላት… ታዋቂ ለመሆን ከፍተኛ ጉጉት አላት… ሀሊና ከአንድ ወንድ ፍቅር የሚይዛት ቢበዛ ለ15 ቀናት ብቻ ነው… ከዚያ ትፈነግለዋለች… ለወሲብ የተመቻትን ወንድ ከመጠየቅ ወደ ኋላ ብላ አታውቅም! እንቢ ያላትም ወንድ እስከዛሬ ድረስ የለም…ሀሊና ቀጠሮ በማክበር የሚወዳደራት የለም! በጣም ቁምነገረኛ ናት በጣም አትበሳጭም! ሙዚቃ ትወዳለች መፅሐፍት በጣም ይማርኳታል… ደራሲ ባል እንዲኖራት ሁሌ ታልማለች … ሀሊና እንዳሰበችው አንድ ዝነኛ ሰው ጠብሳ ለመገናኘት የሚቀጥለውን ወር በጉጉት እየጠበቀች ነበር …

እኔ

ኤ

ፍ

ሬ

ም

ብዙም አላምርም ብዙም አላስጠላም! ጥሩ ቁመና አለኝ… ጥሩ ፈገግታ አለኝ … በተለይ ሳቁ እና አረማመዴ ያምራሉ … ብዙዎች ይማረኩበታል … በሚቀጥለው ሳምንት ሀያ ዘጠነኛ ዓመቴን እደፍናለሁ!!

መሳቅ ! መጫወት! መጠጣት! መብዳት እወዳለሁ… ሥራ ላይም ቀልድ አላውቅም! ከልቤ እሠራለሁ … ሰዓት አከብራለሁ! ስራዬን አከብራለሁ… ታታሪ ሰራተኛ ነኝ ከሀሊና… ከዳንኤል … መሀመድ እና በረደድ ጋር ባንድ ዩኒቨርስቲ ነው የተማርነው … የተመረቅነውም … ግን ሁላችንም የተማርነው የተለያየ ትምህርት ነበር… አቤት ዩኒቨርስቲውን በአንድ እግራችን አቁመነው ነበር… ተጫጭሰን ነው የተመረቅነው … ፈታ ብለን ነው የዩኒቨርስቲን ሕይወት የቋጨነው … ከልብ እየተዝናናን ነበር የተማርነው ታዲያ ሞኝ አልነበርንም በትምህርታችንም ላይ ጠንካራ ተማሪዎች ነበርን… ከልብ እናነባለን …

… ከልብ እናጠናለን … ምርጥ ውጤት በማምጣት ነው የተመረቅነው … በብልሃት ነበር የምንቀሳቀሰው… በተለይ ቅዳሜ የጭስታችን ቀን ናት… ቅዳሜ ምርጥ ቀናችን ናት… ቅዳሜ የኛ በዓል ናት… ከዩኒቨርስቲ በኋላ ራሱ ቅዳሜ በዓላችን እንደሆነች ቀጥላለች…

ከሀሊና…

ከመሀመድ…

ከዳንኤል…

ከበረደድ…

በጣም ብዙ ነገር ተምሬያለሁ … ብዙ የተለያዩ ነገሮችን ቀስሜያለሁ… የሕይወት ምንነትን አሳይተውኛል … ስለ ሕይወት እንድገነዘብ አድርገውኛል ደስተኛ አድርገውኛል … ቀለል ያለ ሕይወት እንድኖር አድርገውኛል…

## ዛሬ ላይ

ተጨንቄያለሁ … ሁሉ ነገር ግራ ገብቶኛል የምወደው ስራ አስጠልቶኛል … ሕይወት አስጠልታኛለች … አሁን ደስታ ካጠገቤ ርቃለች አሁን በሀዘን ተሞልቻለሁ … አሁን ለመኖር ሳይሆን ራሴን ለማጥፋት እየተመኘው ነው … እንዴት ብዬ ውስጤ ያለውን የእሳት ነበልባል እንደማስረዳችሁ ነው የቸገረኝ … ውስጤ እርር… ቅጥል ንድድ … ብሷል… ውስጤ በከፍተኛ ሀዘን ተሞልቷል … አሁን አይዞህ የሚለኝ ጓደኛ የለኝም… አሁን የሚያስቀኝ ጓደኛ የለኝም … አሁን የሚመከረኝ ጓደኛ የለኝም … አሁን … ብቸኛ ነኝ… አሁን ባዶነኝ … አሁን ከንቱ ነኝ…

## ሀሳብ

ማታ ከስራ ስመለስ ነበር ያሰብኩት፡፡ ወጪ ሰራሁኝ፡፡ በሀሳቤ ፀንቼ ስልክ ለመደወል አቀድኩ… መደወል ጀመርኩ

" ሀሎ ሀሊና"

" አቤት"

ነገርኳት :: በደስታ ተስማማች::

" ሀሎ ዳኒ"

"አቤት"

ነገርኩት:: በደስታ ተስማማ::

"ሀሎ በሬ"

"አቤት"

ነገርኩት :: በደስታ ተስማማ ... መሀመድም በደስታ ተስማማ::

በነጋታው ከባንክ ሀያ ሺ ብር አወጣሁ:: የአባቴን መኪና ለሳምንት ተቀ

ሁላችንም በተስማማንበት ሰዓት ላይ ሜክሲኮ ተገናኘን :: መኪናዋ ጉዞዋን ጀመረች

አዲስ አበባ

↓

ዝዋይ

↓

ሻሸመኔ

↓

ወንዶ

↓

ያቤሎ

↓

ሜጋ

↓

ሞያሌ

↓

መኪናዋን እያሳበድኳት የማሽከረከራት እኔ ነኝ... መኪና ስነዳ ማከነፍ በጣም ደስ ይለኛል... በፍጥነት መንዳት ሀሴት ይሰጠኛል ... እስከ አዋሳ ሁሉ ነገር መልካም ነበር ... ወንዶ ስንደርስም መልካም ነበር ... ያቤሎ ላይ የሆነውን በእርግጥ አላስታውስም... በዚያ ላይ መጠጥ እየጠጣን ነበር ... እየጠጣሁ ነበር የምነዳው ... በቃ የማስታውሰው ነገር ቢኖር እንዴት እንደሆነ ባላውቅም ከሁለት ቀናት በኋላ ስነቃ ሆስፒታል አልጋ ላይ ተኝቼ ነበር... መጠነኛ ጉዳት ደርሶብኛል... እኔ አለሁ... መሀመድ ... ሀሊና.. ዳኒ... በሬ ... ግን የሉም ... ሞተዋል!! ገድያቸዋለሁ... እኔ ሹፌር ሆኜ ለዚያውም ከፊት ወንበር ተቀምጬ እንዴት እንደተረፍኩ ግራ ገብቶኛል... ምናልባት የተረፍኩት ራሴን አንቄ እንድገድል ይሆናል ...

በቃ ሙቼም ሳትረዱኝ አይቀርም የተፈጠረው ነገር ይሄ ነው ... የተፈጠረው ከስተት ይሄ ነው... የአራት ውድ ጓደኞቼ ሕይወት በእኔ እጅ ላይ ጠፍቷል ... ገድያቸዋለሁ... አሁን ግራ ገብቶኛል ... አሁን ተጨንቄያለሁ ... ምን ማድረግ እንዳለብኝ አላውቅም ... እንቅልፍ የለኝም ... ትዝታ ... ፀፀት... ሊገለኝ ነው... በሀሳብ ናውዤያለሁ... በጭንቀት ጨሻለሁ... በፀፀት ህሊናዬ ዞሯል ... በደለኝነት እየፈለጠኝ ነው ... ሁሉ ነገር አስጠልቶኛል ... ለምን ከሞት ጓደኞቼን ጥዬ እንደተረፍኩ ግራ ተጋብቻለሁ... የጓደኞቼን ቤተሰቦች ለማየት ፈርቻለሁ... በጣም ተጨንቄያለሁ... ምንድነው ማድረግ ያለብኝ?

ሀ. ራሴን ማጥፋት

ለ. ከኢትዮጵያ መጥፋት

ሐ. ወደ ፈጣሪ መመለስ

መ. በፀፀት... በትዝታ ... መኖር

ሠ. ሌላ ሀሳብ ________________

መልስ ______________________________ ምክኒያት ______________

________________________________________________________________

________________________________________________________________

________________________________________________________________

እኔ ማሰብ ራሱ አቅቶኛል... አባካችሁ አርዱኝ ... የትኛው ይሻለኛል... ምንስ ማድረግ ነው ያለብኝ? ... አዲስ አበባ፣ ፒያሳ... ቶታል ፊት ለፊት ያለችው መጠጥ ቤት ውስጥ አለሁኝ_ ከርቀት እኔን መለየት አያስቸግራችሁም ! በርካታ የመጠጥ ብርጭቆዎች እና በላይ በላዩ ላይ ሲጋራ የሚለኩስ ሰው ካያችሁ እኔ ነኝ! እኔ የአራት የጓደኞቼን ነብስ የበላሁ ኤፍሬም ነኝ_ ቡቃ ከዚህ በላይ ልነግራችሁ ... ከዚህ በላይ ላካፍላችሁ የምምክረው ጉዳይ የለም_ አልችልም!! የሰው ልጅ እንዴት እንደሚኖር እንጂ እንዴት እንደሚሞት አያውቅም... በርናርድ ሾው እንዲህ ይላል 'በዓለማችን ውስጥ የሰውን ልጅ ለሀዘን የሚዳርጉት ሁለት ነገሮች አሉ:: አንዱ በልቡ የሚመኘውን አለማግኘቱ ሲሆን ሌላው ደግሞ ያንን የተመኘውን አግኝቶ ማጣቱ ነው'